# የእግዚአብሔር ፍቅር
# የእኛ ህይወት

## ክፍል አንድ

በጃኪ.ይ ኦሼክ

### የክርስቶስ ስቃይ፤ ሞት እና ትንሳኤ ታሪኮች
### ከማቴዎስ ፤ ከማርቆስ፤ ከሉቃስ እና የዮሐንስ መፅሀፍት የተወሰዱ ታሪኮች

**ትምህርት 1:  ሆሳዕና በአርያም — ንጉሱ ኢየሱስ**
**ትምህርት 2:  እኔ እሆንን? —ከአራቱ ወንጌላት የተውጣጡ ንባቦች**
**ትምህርት 3:  እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ — የኢየሱስ የመጨረሻው ትምህርት**
**ትምህርት 4:  ውሰዱ እና ብሉ*…ውሰዱ እና ጠጡ* — አዲሱ ኪዳን**
**ትምህርት 5:  እኔ ነኝ — ፀሎት፤ መታሰር ፤ ክስ፤ ክህደት**
**ትምህርት 6:  ስቀሉት! — በጲላጦስ ተፈረደበት**
**ትምህርት 7: አባት ሆይ ይቅር በላቸው — ታላቅ ፍቅር**

**"…አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።"**
***መዝሙር* 119:11**

በቴንዝፓምር ፐብሊሽንግ የተዘጋጀ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው ©2015 በክሮስኮኔክት ሚኒስትሪ

ይህንን ጥናት ያለ አዘጋጁ የፅሁፍ ፈቃድ ማንኛውንም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማባዛት ሆነ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል።

በጥናቱ ውስጥ የጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1962 ዓ.ም. እትም የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው።

## መቅድም

ቀሪውን ህይወታችሁን መልክ የሚያስይዘውን የአስገራሚውን ጉዞ ግስጋሴ ቀጥላችኋል፡፡ይህ ጉዟችሁ ልዩ ነው፤ ለትምህርቱ ያላችሁን ጉጉት እና ፍላጎት መፅሐፍ ቅዱስ የሚባለውን የእግዚአብሄር ቃል የመረዳታችሁን ልክ በከፊል ይወስነዋል ፡፡ይህን ጥናት ለማጥናት ያላችሁ መሰጠትም እግዚአብሄር በቃሉ ውስጥ ለልባችሁ በመናገር ህይወታችሁን የሚያበለፅግበትን ተስፋ የያዘ ነው፡፡

ይህን ጥናት ስታጠኑ ለጥናታችሁ የሚረዷችሁን የሚከተሉትን የመርጃ መሳሪያዎች እንድትይዙ ትበረታታላችሁ፡፡

1. “የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ህይወት” — ክፍል ሁለት የሚለውን የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ጥራዝ

2. የአዲሱን መደበኛ ትርጉም መፅሀፍ ቅዱስ ፡ አዲስ መፅሀፍ ቅዱስ የምትገዙ ከሆነ የሚከተሉትን ነገሮች ቢኖሩት መልካም ነው፡፡

ሀ. ማጣቀሻ ጥቅሶች በምእራፎቹ አካፋይ መካከል ወደታች የተፃፉበት

ለ. በጀርባው የቃል ማውጫ ያለው

ሐ. መሰረታዊ የሆኑ ካርታዎችን የያዘ

3. እስኪብርቶ ወይንም እርሳስ

4. በፎቶ መጠን የተቆራረጡ ካርዶች

በተራ ቁጥር ሁለት ላይ የተዘረዘሩን ሶስቱን ነገሮች ካሟላችሁ ጥናታችሁን በአግባቡ እና በተሳካ ሁኔታ ማጥናት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስን የምታነቡት ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ በቅድሚያ ማጥናት ያለባችሁ ክፍል መፅሐፍን ቅዱስን መመርመር የሚለውን የጥናት ክፍል ነው፡፡ይህ የጥናት ክፍል ብቁ የመፅሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች የሚያደርጋችሁ እና መፅሐፍ ቅዱስን በብቃት ማጥናት በሚያስችላችሁ መንገድ የተዘጋጁ መፅሐፍ ቅዱስን መመርመር የሚያስችሉ መሳሪያዎችን የያዘ ነው፡፡ በተጨማሪም ደግሞ ይህ ጥናት “የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ህይወት” - ክፍል ሁለት የሚለውን ቀጣዩን የጥናት ክፍል ለማጥናት ስለሚረዳ እንድታጠኑት እንመክራለን፡፡

መፅሐፍ ቅዱሳችሁ ላይ ምልክት ማድረግ ሊከብዳችሁ አይገባም ምክንያቱም የእናንተ መፅሐፍ ቅዱስ ስለሆነ፡፡ እላዩ ላይ በማስመር ፣ በምልክት ማድረጊያ ማርከር ምልክት አድርጉበት፣ አክብቡበት፣ የራሳችሁ መፅሐፍ አድርጉት፡፡ ማስታወሻ ወይንም ፣ታብሌት (ሞባይላችሁን) ጥያቄዎችን ፣ሀሳቦችን፣ትምህርቱን በአጠቃላይ ለመከታተል መጠቀም ትችላላችሁ፡፡

እነዚህ ማጥኛዎች የተዘጋጁት መፅሀፍ ቅዱስን በግላችሁ ማጥናት እንድትችሉ ተደርገው ነው፡፡ስለዚህ ያለምንንም ወይንም በመጠኑ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ልታጠኗቸው ትችላላችሁ ማለት ነው፡፡በተጨማሪም አዳዲስ መረጃዎችን ልታገኙ እንዲሁም አዲስ መረዳቶችን እንዲሁም አስቸጋሪ

የሆኑ መልስ የሚሹ ጥያቄዎችን ልታገኙ ትችላላችሁ። ይህንን ጥናት ስታጠኑ እንደተለመደው ጓደኞቻችሁን ወደዚህ ጥናት መጋበዝ እንዳትዘነጉ።

በጥናታችሁ ደስታን እንድታገኙ እንመኛለን።እግዚአብሄር በቃሉ ሲናገራችሁ ልባችሁ የሚቀበል ይሆን ዘንድም እንዲሁ። በእነዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች እግዚአብሄር በልጁ በጌታችን በእየሱስ ክርስቶስ የገለጠውን ታላቅ ፍቅር እንድትረዱ ያድርጋችሁ።

## መግቢያ

በክሮስ ኮኔክት የሚዘጋጁ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የሚያመላክቱ ሲሆን በተለይም ደግሞ የእርሱን ህይወት፡- የእርሱን መከራ፤ ሞት እና ትንሳኤን የሚያሳዩ ናቸው፡፡ በአጭሩ ይህ ታሪክ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው፤ በእርሱ አማካኝነት የሰው ልጆች በሙሉ ህይወት እንዲኖራቸው ሲል የራሱን ህይወት ለአባቱ ፈቃድ አሳልፎ ስለሰጠው ስለ ኢየሱስ የሚናገር ነው፡፡ ይህ ታሪክ እውነተኛ ታሪክ ነው፡፡ ይህ ታሪክ ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር እራሱ ያዘጋጀው ታላቅ የምስራች ወይንም ወንጌል ነው፡፡  የዚህ ታላቅ የምስራች  ጥናትን በተሟላ መልኩ ማጥናት የምንችለው የጥናቱን ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት ስናጠና ነው፡፡ ምንም እንኳን ጥናቶቹ በሁለት ክፍሎች ተከፋፍለው ቢቀርቡም መጠናት ያለባቸው ግን እንደአንድ ክፍል ነው፡፡

ኢየሱስ ወደ ኢሩሳሌም ሲገባ ሰዎች ሆሳዕና እያሉ ሲጨፍሩ ነበር፤ ይህ ደግሞ የሚያሳያን እርሱ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በግርማ ሞገስ እንደ ነበር ነው፡፡ ከዚያም እርሱን ለመግደል ሰዎች ሲያሴሩ፤ ከራሱ ደቀመዛሙርት ጋር ስለበላው የመጨረሻው እራት፤ ስለተናገራቸው የማፅናኛ ቃላት እና ተስፋ እንመለከታለን፡፡ ወደ ጌተሰኒ የአትክልት ስፍራ እንከተለው እና ከዚያም በጣር ውስጥ ሆኖ ሲፀልይ እና በክፉ ሰዎች እጅ ተላልፎ ሲሰጥ እንመለከታለን፡፡

እርሱ ለሐና እና ለቀያፋ ተላልፎ ሲሰጥ፤ ቀጥሎም ለጲላጦስ ከዚያም ለሄሮድስ ተላልፎ ሲሰጥ እና በመጨረሻም ለጲላጦስ ተመልሶ ተላልፎ ሲሰጥ ሁኔታውን እየተከታተልን እንመለከታለን፡፡ በእርሱ ጉዳይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማናቸውም አያውቁም፡፡ አይሁዳውያን እንዲሞት ይፈልጋሉ ነገር ግን አልገደሉትም፡፡ ሮማውያን በበኩላቸው በእርሱ ላይ ምንም ዓይነት ጥፋትን አላገኙበትም፤ ከዚህም የተነሳ የሚሞትበት ምክንያት አልታያቸውም፡፡ የአይሁድ ንጉስ ስለተባለው ስለዚህ ሰው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማናቸውም አላወቁም ነበር፡፡

በመጨረሻም የህዝቡ ግፊት እና የጲላጦስ ደካማ ባህሪይ ኢየሱስ እና ሁለቱ ወንበዴዎች ወደሚሰውበት ወደ ቀራኒዮ ወደ ሚደረገው ረጅም ጉዞ ይመራናል፡፡  ህዝቡ በእየሱስ ላይ ተሳለቁበት፤ጮሁበት ከዚያም አላገጡበት፡፡ ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዴዎች እንኳን የመናገር መብት ነበራቸው፡፡  ኢየሱስ ለወዳጆቹ፤ ለአባቱ እና ለእኛ የተናገራቸውን አጫጭር አረፍተ ነገሮችን እንሰማለን፡፡ ከራሱ ርህራሄ የተነሳ ለሁሉም ሰዎች ፍቅርን እና ምህረትን ሰጠ፡፡  በመጨረሻ ላይም "ተፈፀመ" ብሎ የመጨረሻው

ትንፋሽ ሲተነፍስ እንመለከተዋለን፡፡ በሁሉም ስፍራ እና በሁሉም ጊዜ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የእርሱ ስራ መፈፀሙን እንዲያውቁ ይፈልጋል፡፡

ሰንበት ከመግባቱ በፊት የእርሱ ቀብር በፍጥነት ተከናወነ፡፡ የእግዚአብሔር አብ ማረጋገጫ ማህተም ያረፈበት ታላቅ የምድር መናወጥ በሳምንቱ መጀመሪያ ቀን ሆነ፡፡ ይህም የመሬት መናወጥ "ምህረት ተደርጓል!" የሚል ነው፡፡ የእርሱ ትንሳኤ ለአለም የአወጀው አዋጅ እርሱ ከሞት እንደተነሳ እኛም ከሞት እንደምንነሳ ነው፡፡ እኛ በእርሱ ከመቃብር እስራት ነፃ የወጣን እና አዲስ ህይወት የተሰጠን ነን፡፡

ኢየሱስ ከትንሳኤው በኂላ ኢየሱስ በምድራዊው አገልግሎቱ ለአገለገሉት ለበርካታ ሴቶች ተገልጧል፡፡ እርሱ ለጴጥሮስ፤ ለመግደላዊት ማሪያም፤ በኤማሁስ መንገድ ለሚጓዙት መንገደኞች እና አይሁድን ፈርተው በር ዘግተው ለተደበቁ ደቀመዛሙርቱ ተገለጠላቸው፡፡ ለእነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ሰላምን ሰጣቸው… የእርሱን ራዕይ ፤ የእርሱን እቅድ ሰጣቸው ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር አብ በልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለአለም የገለጠውን ፍቅር ማወጅ የሚያስችላቸውን ኃይል መቀበል እንዲችሉ አዘጋጃቸው፡፡

እነዚህ ታሪኮች ከረጅም ዓመታት በፊት መከናወናቸውን ማመን ብቻ ምንም ዓይነት ጥቅም የለውም፡፡ ከሁሉም በላይ እነዚህ ታሪኮች እውነተኛ እንደሆኑ ዲያብሎስም ያውቃል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ምዕራፍ 20:30 ላይ የሚነግረን ነገር ኢየሱስ በመፅሐፍ ያልተመዘገቡ በርካታ ተዓምራዊ ምልክቶችን በደቀመዛሙርቱ ፊት በጣም እንዳደረገ ነው፡፡ ነገር ግን ዮሐንስ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 31 ላይ የሚነግረን ነገር ወንጌሉን የፃፈበት ዓላማ፡ "ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል፡፡ አዎን! በእርግጥም የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ህይወት ነው!

# ትምህርት አንድ

# ሆሳዕና በአርያም!

## ማርቆስ 11:1-11 — ንጉሱ ኢየሱስ

---

**የትምህርት አንድ ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 1: ማርቆስ 11:1-11

- ኢየሱስ እና ነቢያቶች
- ኢየሱስ ወደ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ
- ማሰላሰል: ንጉሱ ኢየሱስ
- ሆሳዕና! አድን!

## መግቢያ

ሰዎች የኢየሱስ ህይወትን አልተረዱም ነበር፡፡ ሰዎቹ የፈለጉት ንጉስ እነርሱን ከሮማውያን የቅኝ አገዛዝ ነፃ የሚያወጣ ነው፡፡ እነርሱ የፈለጉት ንጉስ ስለፍትህ እና ርህራሄ የሚናገር፣ ከጨቋኞቻቸው ነፃ የሚያወጣቸውን ነው፡፡ በሰዎች ልብ እና ህይወት ላይ መንገስ የሚፈልገውን ንጉሱን ኢየሱስን ማወቅ ተሳናቸው፡፡ እርሱ የእግዚአብሔር መንግስት ንጉስ ነው፡፡ ይልቁንም ሰዎቹ ጊዚያዊ ፍላጎታቸው አሳውሯቸው ታላቁን ፍላጎታቸውን ያም የመሲሁን፣ የክርስቶስን ተስፋ ማየት ተሳናቸው፡፡

ኢየሱስ በአህያዋ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም ገባ፡፡ እርሱ ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት ሳምንት በተለምደ ቅዱስ ሳምንት ተብሎ ይታወቃል፡፡ በአህያዋ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ የተጓዘበት እሁድ በቤተ ክርስቲያን ሆሳዕና በመባል ይታወቃል፡፡ ብዙ አብያተ ክርሰቲያናት ልጆችን የዘንባባ ዝንጣፊ በማስያዝ የአምልኮ ፕሮግራማቸውን ያከናውናሉ፡፡ በእለቱ የተከናወነውን ዝርዝር ሁኔታ እና የህዝቡን ደስታ በዝርዝር አንመለከትም ነገር ግን አንድ የምናስተውለው ነገር ይህ “ሆሳዕና በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው” የተባለለት ሰው ከጥቂት ቀናት በኋላ በመስቀል ላይ በሚስማሮች የሚቸነከር መሆኑን ነው፡፡

## ትምህርት I

**ምዕራፍ 1**

### ትምህርት

*የእግዚአብሔር ፍለጋ የእኛ ተልዕኮ* በሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ኢየሱስ እርሱን ለሚከተሉት ደቀመዛሙርቱ ለማስተማሪያነት የተጠቀማቸውን ምሳሌዎችን ተመልክተናል፡፡ እንደገናም ኢየሱስ ሐብታሞችን እና የተማሩትን ፣ ድሆችን እና በሰዎች የተገለሉትን እንዲሁም ቀራጮችን እና ኃጢአተኞችን ሁሉ በርህራሄ ሲነበኛቸው እንመለከታለን፡፡ የኢየሱስ አገልግሎት ነፃ እና ይቅር የተባለ ህይወትን በሙላት መኖር የሚፈልጉ ሰዎችን የሳበ ነበር (ዮሐንስ 10:10)፡፡

ኢየሱስ የኖረው ህይወት እና የፈውስ አገልግሎቱን የተወጣበት መንገድ ነቢያት የተናገሩት ትንቢት ፍፃሜ ነበር፡፡ ህይወቱ እና አገልግሎቱ እርሱ በእግዚአብሔር ቃል የተገባው መሲሁ (በእብራይስት)፣ የተቀባው፤ ክርስቶስ (ግሪክ) እርሱ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ አልፎ አልፎ የወንጌላት ፀሃፊዎች "በነቢያት እንደተነገረው" ወይንም "ትንቢቱ ተፈፀመ" የሚሉትን ሃረጎች ይጠቀማሉ፡፡ ነቢዩ ኢሳያስ በኢሳ 61:1 ላይ የፃፈው ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ትንቢት የሚነግረን በእግዚአብሔር የተቀባው ስለሚያደርገው በነገር ነው፡፡ በጌታ የተቀባው የሚያደርገው…

- ________________________________________
- ________________________________________
- ________________________________________
- ________________________________________

1. መጥምቁ ዮሐንስ በወህኒ ቤት በነበረበት ወቅት ደቀመዛሙርቱን ወደ ኢየሱስ እርሱ (ኢየሱስ) የተቀባው ፤መሲሁ መሆኑን ለማረጋገጥ ላከ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ማቴዎስ 11:3 ምን ይለናል? እነርሱም ኢየሱስን ምን ጠየቁት?

   ________________________________________

   ________________________________________

2. የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር ቁጥር 4 እና 5?

   ________________________________________

   ________________________________________

3. በቁጥር 5 ላይ ኢየሱስ ከቢሉይ ኪዳን ነቢያት ኢሳያስን ይጠቅሳል፡፡ መፅሐፍ ቅዱሳችሁ ተጓዳኝ ጥቅሶች ማውጫ ካለው ቁጥር 5 ከኢሳያስ 35:4-6 እና ማቴዎስ15:31

ተጨማሪ ሃሳቦችን ይዟል። እነዚህ ጥቅሶች ስለኢየሱስ የተቀባው፤ መሲሁ እርሱ ስለመሆኑ ምን ይነግረናል?

______________________________________________

4. በሌላ ጊዜ ኢየሱስ በናዝሬት ከተማ በሚገኝ ምኩራብ ተገኝቶ ከትንቢተ ኢሳያስ አንድ ክፍል አንብቦ ነበር። ሉቃስ 4:16-21 ተመልከቱ። እነዚህን ቃላት ታውቋቸው ነበር? ከትንቢተ ኢሳያስ የትኛውን ክፍል ነው ያነበበው? ________________

በዚህ ጥናት አስተምሮ መሰረት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው ስለአዲሱ መንገድ ከማስተማር ወይንም ህሙማንን ከመፈወስ ወይንም ዲዳውን ከመፈወስ ወይንም ሽባውን ከመፈወስ እና የእውሩን ዓይን ከመፈወስ በአለፈ ለታላቅ ዓላማ ነው። እርሱ እንደ ሰው መጣ፤ እንደማንኛችንም በምድር ላይ ኖረ፤ የሴይጣንን ፈተና ተቋቁሞ ፀና፤ የፈሪሳውያንን እና የፃህፍትን ተንኮልን ተቋቋመ። በጠላቶቹ በደረሰበት መከራ እና ማላገጥ ተሰቃየ፤ በመጨረሻም በማስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ። የኢየሱስ ታላቁ ዓላማ እስከ ሞት ድረስ በመታዘዝ የአባቱን ፈቃድ መፈፀም ነበር (ማቴዎስ 26:39)።

1. የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ ምንድነው (1ጢሞቴዎስ 2:4)?

   ______________________________________________

2. የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ እንዴት ነው የሚፈፀመው (ማቴዎስ 20:17-19)?

   ______________________________________________

3. ለጢሞቴዎስ በፃፈው መልዕክቱ ቅዱስ ጳውሎስ የሚነግረን ነገር ምንድነው (1 ጢሞቴዎስ 1:15)?

   ______________________________________________

4. ማርቆስ 2:17 እና ዮሐንስ 3:17 ተመልከቱ:

   ______________________________________________

## <u>ምዕራፍ 2</u>

**የቤት ሥራ** : ማርቆስ 11:1-10 አንብቡት። ለጥናታችን እንዲረዳን ቅዱስ ማርቆስ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በክብር የገባበትን ታሪክ የፃፈውን እናተኩራለን። ታሪኩ በሶስቱ ወንጌላትም ውስጥ ተመዝግቧል።

- ማቴዎስ 21:1-11
- ሉቃስ 19:29-38
- ዮሐንስ 12:12-15

እነዚህን ጥቅሶች ለጥናታችን እንዲረዳን በተጨማሪነት እንመለከታቸዋለን።

መልመጃ:

1. ኢየሱስ ወዴት እሄደ ነበር (ማርቆስ 11:1)?

   ______________________________________________

   ሌሎች ሁለት ከተማዎች ተጠቅሰዋል: __________________________ እና ____________________:: ምናልባትም ቤተ ፋጌን በካርታ ላይ ላትመለከቷት ትችላላችሁ (ቤተ ፋጌ የምትገኘው በኢየሩሳሌም እና በኢያሪኮ መካከል ነው) ይሁን እንጂ ከኢየሩሳሌም ደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በ3.2. ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘውን ቢታኒያን ልትመለከቱ ትችላላች:: ይህች ከተማ ከቀደመው ጥናታችሁ እንደምታስታውሱት የማሪያም፤ የማርታ እና የአልዓዛር ቤት የሚገኝበት ነው::

2. ለሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ የሰጣቸው ትዕዛዝ ምንድነው (ቁጥር 2)?

   ______________________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________________

3. ምናልባት ጥያቄ ቢጠየቁ ምን ብለው መልስ መስጠት አለባቸው (ቁጥር 3)?

   ______________________________________________________________________________

4. ታሪኩ የሚቀጥለው ኢየሱስ እንደተናገራቸው (ቁጥር 4-6):

   ሀ. እነርሱ ምን አገኙ?

   ______________________________________________________________

   ለ. ምን አደረጉ?

   ______________________________________________________________

   ሐ. ምን ተጠየቁ?

   ___________________________________________________________

   መ. እንዴት ነው ምላሽ የሰጡት?

   ___________________________________________________________

5. ማንም ያልተቀመጠባትን የአህያ ውርጭላ ወደ ኢየሱስ አመጡ:: ቀጥሎ ምን ሆነ (ቁጥር 7)?

   ሀ.____________________________________________________________________

   ለ.____________________________________________________________________

6. ብዙ ሰዎች ምን አደረጉ (ቁጥር 8-10)?

   ሀ. እነርሱ የአነጠፉት

   ______________________________________________________________________

   ለ. እነርሱ የአነጠፉት

   ______________________________________________________________________

ሐ. እነርሱ የጮሁት

________________________________________________

________________________________________________

7. እንደ ቅዱስ ማርቆስ ዘገባ ኢየሱስ  ወዴት ነው የሄደው (ቁጥር 11)

________________________________________________

**<u>ምዕራፍ 3</u>**

**ማሰላሰል**

1. እንደምናስተውሰው የብሉይ ኪዳን ነቢያት በእግዚአብሔር ስለተቀባው ስለመሲሁ ስለክርስቶስ አስቀድመው የተናገሩት ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ኢየሱስ የስብከት፤ የማስተማር እና ህሙማንን የመፈወስ አገልግሎቱን ያከናውን ነበር፡፡  ማቴዎስ በማቴዎስ 21:5 የሚነግረን ይህ ኢየሱስ በአህያ ውርንጭላ ሆኖ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረገው ጉዞ ስለእርሱ የተነገረው ትንቢት ፍፃሜ እንደሆነ ነው፡፡ በዘካሪያስ 9:9 ላይ ነቢዩ የሚነግረን ነገር ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

2. ኢየሱስ ለሁለቱ ደቀ መዛሙርት የተናገረው ነገር ማንም ያልተቀመጠባትን ውርንጭላ እንዲያመጡለት ነበር (ቁጥር 2) ፡፡ በቁጥር 7 ላይ እንደምንመለከተው የአህያውን ውርንጭላ ወደ ኢየሱስ አመጡ ልብሳቸውንም አንጥፈውበት እርሱም ተቀመጠባት፡፡ ይህ ነገር ወደ አዕምሮአችሁ የሚያመጣው ነገር አለ?  ለምን የአህያ ውርንጭላን መረጠ?  እንደ ነቢዩ አባባል ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው እንደንጉስ ሆኖ ነው፡፡ “ንጉስሽ ….. ይመጣል፡፡” በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ የሚመጣ ንጉስ ምን ዓይነት ንጉስ ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ወይንም በጥንት ዘመን ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተሰራ ፊልም አንድ የጦር መሪ አሸንፎ ከጦር ሜዳ በሰረገላ ላይ ተቀምጦ በብዙ ክብር ታጅቦ ሲመለስ ተመልክታችሁ ታውቃላችሁ ? በዚህ ላይ የእናንተ አስተያየት ምንድነው…

________________________________________________

3. ኢየሱስ በትላልቅ ፈጣን የጦር ሰረገላዎች ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ቢገባ ኖሮ ነቢዩ ምን ስለመሲሁ ዓይነት ነቢይ እንደሆነ ይናገር ነበር? ብሎ መጠየቁ ተገቢ ነው፡፡ ነቢዩ ዘካሪያስ የሚነግረን ንጉስ ከእንደዚህ ዓይነቱ ነገስታት ይለያል፡፡   ስለዚህ ንጉስ ለመግለፅ ነቢዩ ዘካሪያስ የተጠቀመው ቃላት ምንድናቸው?

________________________________________

4. ኢየሱስ ማንም ያልተቀመጠባትን ውርጭላ ጠየቀ፡፡ ከዚህ የምንማረው ነገር ይህች ያልተገራች ትሁት እንስሳ ትሁት ሆኖ ለአባቱ ፈቃድ ለተገዛ ንጉስ ተገዛች፡፡ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም

የገባበት የመጨረሻው ጉዞ ሲሆን በዚህን ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው እንደ ንጉስ በብዙ ክብር እና በብዙ ሰው ታጅቦ ነው። ህዝቡም በታላቅ ድምፅ "በጌታ ስም የሚመጣ ንጉስ የተባረከ ነው" (ሉቃስ 19:38) ፤ " የእስራኤል ንጉስ" (ዮሐንስ 12:13)፤ "የዳዊት ልጅ" (ማቴዎስ 21:9)፤ "በጌታችን ስም የምትመጣ የአባታችን መንግስት የተባረከች ናት" (ማርቆስ 11:10) እያሉ ይጮሁ ነበር። በዚህ ላይ የእናንተ አስተያየት ምንድነው:

______________________________________________________________________________

5. በማርቆስ 11:9 ላይ ህዝቡ "ሆሳዕና!" እያሉ ይጪሁ ነበር። *ማስታወሻ : እናንተ የምታነቡት መፅሐፍ ቅዱስ ሆሳዕና የሚለውን ቃል ትርጉም ይሰጥ ይሆናል። ሆሳዕና የሚለው ቃል በእብራይስት ቋንቋ ሲሆን ትርጉሙም "አድን !" ማለት ሲሆን እርሱም የውዳሴ መግለጫ ቃል ነው።* ህዝቡ "ሆሳዕና !" እያሉ ይጮሁ ነበር። እነርሱ ኢየሱስን የቆጠሩት ከጨቋኙ የሮማውያን አገዛዝ ነፃ የሚያወጣቸው የፖለቲካ መሪ ነው። በህዝቡ መካከል የሚገኙ ሰዎች ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሳ ፤ ህሙማንን ሲፈውስ፤ ዓይነ ስውሩን ዓይኑን ሲከፍት እና ሺባውን ፈውሶት መሄድ ሲጀምር የተመለከቱ ወይንም የሰሙ ናቸው። ሰዎቹ እነርሱን ከሞት እና ከበሽታ የሚያድናቸውን ንጉስ ይፈልጋሉ። የእነርሱን ፍላጎት እና ምኞት የሚያሟላላቸውን ንጉስ ይፈልጋሉ። ሰላምን የሚያመጣን ንጉስ ይፈልጋሉ። እናንተ ብትሆኑ ምን ዓይነት ንጉስን ትፈልጋላችሁ?______________________________________________________________

______________________________________________________________________________

6. አንድ ተጨማሪ ነገር እንመልከት፡: በሉቃስ 19:38ለ ውስጥ እንደተጠቀሰው ህዝቡ በታላቅ ድምፅ እና በውዳሴ ድምፅ "በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር" እያሉ ይጮሁ ነበር። እንደምታስታወሱት ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ተመሳሳይ ቃላት በመላዕክትም ተብለው ነበር። ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን (ሉቃስ 2:14)?

______________________________________________________________________________

7. አንድ የገና መዝሙር እንደዚህ ይላል "ኑ እና ንጉሳችንን እና አዳኛችንን በግርግም ውስጥ ተመልከቱት"። ሰብዓ ሰገል ወደ ኢየሩሳሌም በመጡ ጊዜ "የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው (ማቴዎስ 2:2)? ብለው ጠየቁ። ነቢያት መሲሁ እንደ ንጉስ እንደሚመጣ አውቀዋል (ዘካሪያስ 9:9) ። ጲላጦስ እንኳን ፅፎ በመስቀሉ አናት ላይ የሰቀለው ፅሁፍ "የአይሁድ ንጉስ የናዝሬቱ ኢየሱስ" (ዮሐንስ 19:19) የሚል ነው። ከልደቱ እስከ ሞቱ ኢየሱስ ይፈለግ ነበር፤ ተመልኳል፤ እንደንጉስም ተሰውቷል። እርሱ የአይሁድ ንጉስ ተብሏል። ይህንን ጉዳይ አሰላስሉ እና አስተያየታችሁን ፃፉ:

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 4

**የትግበራ ጥያቄዎች**:

1. ዓይኖቻችሁን ጨፍኑ እና የሚከተሉትን በአዕምሮአችሁ አሰላስሉ።

   ሀ. እናንተ የቤታችሁን በር ከፍታችሁ ስትመለከቱ ኢየሱስ በበርካታ ሰዎች ታጅቦ፤ ሰዎቹ ደግሞ የዘንባባ ቅጠል ይዘው "ሆሳዕና" "ሆሳዕና" እያሉ በደስታ እየዘመሩ በሰፈራችሁ ቢያልፉ እነርሱን ትቀላቀላላችሁ? ለምንድነው ሰዎቹን የምትቀላቀሉት? የማትቀላቀሏቸው ከሆነስ ለምን?

   ______________________________________________

   ለ. እርሱ ማን እንደሆነ ስትገነዘቡ እርሱ ንጉሴ ነው እያላችሁ ልብሳችሁን በአህያዋ ላይ ስታነጥፉ እስቲ ራሳችሁን ትመለከታላችሁ ? ለምንድነው ይህንን የምታደርጉት? ካላደረጋችሁትስ ለምን?

   ______________________________________________

   ሐ. ንጉስ ካላችሁ ሰላማችሁን ከወሰደባችሁ ነገር አርነት እንደሚያወጣችሁ ተስፋ ታደርጋላችሁ? መልሳችሁ አዎን ከሆነ ለምን? ተስፋ የማታደርጉ ከሆነ ደግሞ ለምን?

   ______________________________________________

2. ኢየሱስ የመጣው ለአባቱ ፈቃድ የተገዛ ጨዋ እና ፃዲቅ ንጉስ ሆኖ ነው። ለእግዚአብሔር ፈቃድ ያለኝ የእኔስ የመሰጠት ደረጃው ምን ያህል ነው? ለንጉሴ ፤ ለነገስታት ንጉስ ስልጣን መገዛት ያቃተኝ ጊዜ መቼ ነው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

**ፀሎት**

ኢየሱስ ሆይ አንተ ወደ ኢየሩሳሌም የመጣኸው ጨዋ እና ትሁት ንጉስ ሆነህ ነው። ህዝቡ ለአንተ ክብር የሰጠው አንተ እነርሱን ከሮማውያ ጭቆና ነፃ እንደምታወጣቸው ስለአመኑ ነው። አንተ ግን ወደ እዚህ ምድር የመጣኸው ለታላቅ ዓላማ ነው። ከሰማያዊው አባታችን ጋር ያለንን ግንኙነት ያበላሸውን እኛን ባሪያ አድርጎ ከገዛው ጨቋኝ ኃጢአት ቀንበር ነፃ ልታወጣን ነው የመጣኸው። አንተ የራስህን ፈቃድ ለአባትህ ፈቃድ አስገዝተሃል። አንተ ወደዚህ ምድር የመጣኸው አንተ የተቀባኸው፤ አዳኛችን መሲሁ ክርስቶስ እንደሆንክ ጥንት በነቢያት የተነገረው ቃል እንዲፈፅ ነው። ለዚህም ምስጋናዬን እና ውዳሴዬን አቀርባለሁኝ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት ሁለት

# እኔ እሆንን ?

## ከአራቱ ወንጌላት የተውጣጡ ምንባቦች
## ማቴዎስ፤ ማርቆስ፤ ሉቃስ ፤ እና ዮሐንስ

---

**የትምህርት 2 ቅኝት**

**ቅኝት**

*መግቢያ*

ትምህርት 2: ከአራቱ ወንጌላት የተውጣጡ ምንባቦች

- ኢየሱስን ለመግደል የተደረገ ሴራ
- የይሁዳ ሃሳብ ተገለጠ
- ሴራው ተጋለጠ
- የእግዚአብሔር ፍፁም የሆነ ጊዜ
- ይሁዳ ሄደ

### መግቢያ

በትምህርት ትምህርት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተገልጠዋል፡፡ ነገሮቹ መሆን እንዳለባቸው አይደሉም፡፡ ሁሉም ነገር መልካም አይደለም፡፡ ኢየሱስ በችግር ውስጥ ነው፤ መንፈሱ ነውጥ ውስጥ ነው፡፡ ሊደግሉት ለሚፈልጉ ሰዎች ተላልፎ እንደሚሰጥ ሰዓቱ እንደደረሰ አውቋል፡፡ እናንተ በእርሱ ቦታ ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?

ኢየሱስን ተመልከቱ፤ ከእርሱም ተማሩ፡፡ እርሱ አገልግሎቱን ሲጀምር ደቀ መዛሙርቱን " ተከተሉኝ ፤ ሰውን የምታደምዱ አደርጋችኋለሁ" ያለውን ቃል አስታውሱ፡፡ ከእርሱ ጋር የፋሲካን እራት ለመመብላት ወደ አዳራሽ እንደገባችሁ አድርጋችሁ እስቲ አንድ ጊዜ አስቡ፡፡ የእናንተ ጓደኞች በዚያ ስፍራ ከእናንተ ጋር ናቸው፡፡ ቀኑን በሙሉ ደክሟችሁ ስለዋለ ውሃ አሙቃ እግራችሁን ስለምታጥብ ልጃገረድ እያሰባችሁ ሊሆን ይችላል…

በአዳራሹ ውስጥ ኢየሱስን የሚከዳው ማን እንደሆነ ሰው እየንተንጫጫ እንዳለ አድምጡት፡፡ እኔ ባልሆንኩኝ ! ያ ሰው ማን እንደሆነ ለማወቅ በአዳራሹ ውስጥ እያማተራችሁ ነው…

ጥናታችሁን ስትቀጥሉ ኢየሱስ ያደረገውን ሁሉ ያደረገው ለእኔ እናንተ እንደሆነ አስቡ፡፡

# ትምህርት 2

**ምዕራፍ 1**

***መግቢያ***

በቤተ ክርስቲያን ካሌንደር መሰረት ከትንሳኤ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ በሚገኘው እሁድ ማለትም ሆሳዕና ተብሎ በሚጠራው እሁድ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያናት ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በክብር የገባበት ታሪክ ይነበባል፡፡ ህፃናት የዘንባባ ዝንጣፊ ይዘው "ሆሳዕና! በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው! ሆሳዕና በአርያም !" እያሉ ይዘምራሉ፡፡

ወዲያውኑ ግን ሁኔታዎቹ ይቀያየራሉ፡፡ ምንድነው የሚሆነው? ከሆሳዕና እሁድ ቀጥሎ የኢየሱስ መከራ የሚጀምርበት ነው፡፡ ኢየሱስን ለመግደል የሚደረገው ሴራ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ እስቲ ታሪኩን መመልከታችንን እንቀጥል…

**የቤት ሥራ** : ዮሐንስ 11:45-53 አንብቡት፡፡ ኢየሱስ አልዓዛርን ከሞት አስነስቶታል (ቁጥርs 38-43)፡፡

***መልመጃ***:

1. ኢየሱስ ለአደረገው ነገር የተወሰኑ አይሁዶች የሰጡት ምላሽ እንዴት ነበር (ቁጥር 45)?

   ____________________________________________________

2. ሌሎቹ አይሁዶችስ እንዴት ነው ምላሽ የሰጡት (ቁጥር 46)?

   ____________________________________________________

3. ሊቀ ካህናቱ እና ፈሪሳዊያኑስ ምን አደረጉ (ቁጥር 47 ሀ)?

   ____________________________________________________

4. እነርሱን ያሳሰባቸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 47ለ-48)?

   ሀ.____________________________________________________

   ለ.____________________________________________________

   ኢየሱስ ብዙ ተዓምራዊ ምልክቶችን ያደርግ ነበር፡፡ እርሱን እንዴት ሊያስቆሙት ይችላሉ?

5. ሊቀ ካህኑ ቀያፋ የተናገረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 49-50)?

   ____________________________________________________

6. በቁጥር 51 መሰረት ቀያፋ የተናገረው ትንቢት (ቁጥር 51-52)? እርሱም:

ሀ. ኢየሱስ

________________________________________________

ለ. ለህዝቡ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን

________________________________________________

ሐ. የእግዚአብሔርን ልጆች

________________________________________________

7. ሳንህድሪን የሚባለው የአይሁድ ጉባኤ ውሳኔ ምን ነበር (ቁጥር 53)?

________________________________________________________

8. ኢየሱስ ያደረገው ጥንቃቄ ምን ነበር (ቁጥር 54)?

________________________________________________________

9. በመፅሐፍ ቅዱሳችሁ የመጨረሻ ላይ ካርታ ካለ ኤፍሬምን ምልክት አድርጉበት። ይህች ከተማ የምትገኘው ከኢየሩሳሌም ከተማ በስተሰሜን በኩል በግምት 19 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው።
10. በኢየሩሳሌም የአሁድ ፋሲካ በዓል የሚከበርበት ጊዜ ደረሰ። ለምን ይመስላችኋል በርካታ ሰዎች ኢየሱስን የፈለጉት (ቁጥር 56)?

________________________________________________________

11. የሊቀ ካህኑ እና የፈሪሳውያን ትዕዛዝ ምን ነበር?

________________________________________________________

**ማሰላሰል**

ኢየሱስ በርካታ ተዓምራዊ ምልክቶችን እያደረገ እንደሚገኝ የወቅቱ የሃይማኖት መሪዎቹ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር (ዮሐንስ 11:47ለ) ይሁን እንጂ የተለያየ ትዕዛዛትን በመስጠት እና ህጎችን በማውጣት ሊያስቆሙት አልቻሉም። ተዓምራዊ ምልክቶቹን ቢመለከቱም ኢየሱስን መሲህ፣ ክርስቶስ ነው ብለው መቀበል አልቻሉም ነበር። እነርሱ እርሱን የማስቆም አቅም አልነበራቸውም፣ ይሁን እንጂ እርሱን የሆነ ነገር አድርገው ካላስቆሙት ሰዎች ሁሉ በእርሱ ያምኑና በሰዎች ላይ ያላቸውን ተፅዕኖ እንደሚያጡ ያውቁ ነበር። በአይሁድ ማህበረሰብ ላይ ያላቸውን ክብር ማጣት ብቻ ሳይሆን ለህጉ ያላቸው መታዘዝም ያበቃለታል እያሉም ያስባሉ። ከዚህም የተነሳ ሮማውያ ቤተ መቅደሳቸውን እና አገራቸውንም እንዳይወስዱባቸው ይፈሩ ነበር።

**<u>ምዕራፍ 2</u>**

**የቤት *ሥራ*** : ዮሐንስ 12:1-11 አንብቡት።

**መልመጃ**:

ሀ. ከፋሲካ በዓል ስድስት ቀናት ቀደም ብሎ ለኢየሱስ ክበር የእራት ግብዣ ተዘጋጅቶ ነበር (ቁጥር 2)። ኢየሱስን የት ነው የምናገኘው (ቁጥር 1)?

________________________________________________________________

*ማስታወሻ:* ማርቆስ 14:3 የሚነግረን እነርሱ በማን ቤት እንደሆኑ ነው

________________________________________________________________

ሀ. ማርታ ምን እያደረገች ነው?

__________________________________________________________

ለ. አልዓዛር ምን እያደረገ ነው?

__________________________________________________________

ሐ. ማርያምስ ምን እያደረገች ነው (ዮሐንስ 12:3)?

__________________________________________________________________

***ማስታወሻ:*** የናርዶስ ሽቱ አስከሬንን ለመቀባት የሚጠቀሙበት ነው። ማሪያም በኢየሱስ እራስ ላይ ያፈሰሰችው የዚህ ውድ ሽቱ ሽታ በእርሱ መከራ እና ሞት ጊዜ ሁሉ የሚቆይ ነው። እርሷ ይህንን ሽቱ በኢየሱስ ላይ ያፈሰሰችው እርሱን ወይንም የእርሱን አካል ለቀብር እያዘጋጀችው ነው።

1. ስለ አስቆርቱ ይሁዳ የምንማረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 4-6)?

ሀ. ለምድነው ይሁዳ የማርያም ተግባር የተቃወመው?

__________________________________________

ለ. የናርዶስ ሽቱው ዋጋ ምን ያህል ነው?

__________________________________________________

ሐ. በይሁዳ ልብ ውስጥ ያለው እውነተኛ ፍላጎቱ ምን ነበር?

__________________________________________________________________

መ.እርሱ እንደ ገንዘብ ያዥነቱ ምን ያደርግ ነበር?

__________________________________________________________________

2. ለይሁዳ የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 7-8)?

_______________________________________________________________________

3. ይህ በእንዲህ እያለ እንደ ቁጥር 9 በአይሁዶች ዘንድ ምን እየሆነ ነው?

_______________________________________________________________________

4. እነርሱም ኢየሱስ ለማየት እና ______________________________ (ቁጥር 9)።

5. እንዴት አድርገው ነው ሊቀ ካህናቱ እቅዳቸውን ያሻሻሉት (ቁጥር 10)?

______________________________________________

6. በቁጥር 11 መሰረት አልዓዛር ምን ዓይነት ችግር ፈጠረ (ቁጥር 11)?

______________________________________________

**ማሰላሰል**

ዮሐንስ 12 ውስጥ ባሉት ቁጥሮች የይሁዳ በልቡ ውስጥ የተሰወረው ሃሳብ ተገለጠ። ማሪያም ያደረገችውን ተቃወመ። ተቃውሞውን የገለጠው ደግሞ የአንድ ዓመት ደመወዟን ያህል የሚያወጣውን ውድ ሽቱ በኢየሱስ እግር ላይ በማፍሰስ አባከነች በማለት ነበር። ይሁዳ የተናገረው ሽቱው ተሸጦ ገንዘቡ ለድሆች መሰጠት እንዳለበት ነው። ነገር ግን ቁጥር 6 ይሁዳ ማን እንደሆነ አጋለጠው። እርሱ ለድሆች ግድ አልነበረውም። ግልፅ በሆነ ቋንቋ ይሁዳ ሌባ እንደሆነ ተነግሮናል። ገንዘብ ያለበት ቦርሳ ይይዝ ስለነበር ከሚይዘው ገንዘብ ውስጥ ለግሉ የፈለገውን ያህል ይጠቀም ነበር። ይሁዳ ጠማማ ሰው፤ ሌባም ነበር። ኢየሱስ ለምድነው ይህንን ሰው የታገሰው? ለምንድነው ይሁዳን ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አድርጎ የጠራው? ለሶስት ዓመታት ይሁዳ ከኢየሱስ ጋር ነበር፤ የእርሱን ትምህርቶች ሰምቷል፤ የተለያዩ ሰዎችን እንዴት እንደሚያስተናግዳቸውም አይቷል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ ነገር በይሁዳ ህይወት እና ባህሪይ ላይ ያመጡት ምንም ዓይነት ተፅዕኖ አልነበርም።

1. ኢየሱስ ይሁዳን ያከበረበትን መንገድ አስረዱ

______________________________________________

______________________________________________

2. ስለሌቦች እና ጠማማ ሰዎች ያላችሁ አስተሳሰብ ምንድነው:

______________________________________________

______________________________________________

3. ከህይወታችሁ ውስጥ የማትፈልጉትን ነገር እየሰራ ያስቸገራችሁ እና ተለውጦ እንደ ኢየሱስ እንዲሆን የምትፈልጉት የቱን ነው?

______________________________________________

______________________________________________

<u>**ምዕራፍ 3**</u>

**የቤት ሥራ** : ማቴዎስ 26:1-5 አንብቡት። የሴይጣን ሴራ ተጋለጠ…

**መልመጃ**:

1. ለፋሲካ በዓል ስንት ቀን ቀረው (ቁጥር 2)?

______________________________________________

2. ኢየሱስን ለመግደል ስለተደረገው ሴራ ከቁጥር 4 ምን እንማራለን?

_______________________________

3. እነርሱ የፈሩት ነገር ምንድነው (ቁጥር 5)?

___________________________________________________

**የቤት ሥራ** : ማቴዎስ 26:14-16 አንብቡት።

**መልመጃ**: (ማርቆስ 14:10-11 ተመልከቱት)

1. አስቆሮቱ ይሁዳ ወዴት ነው የሄደው (ቁጥር 14)?

   ________________________________________________

2. ሰዎቹን የጠየቃቸው ነገር ምድነው (ቁጥር 15)?

   _____________________________________________________

3. ስለክፍያው የተስማሙት ነገር ምንድነው?

   ____________________________________________

4. ይሁዳ ምን እንዲሰራ ነው የተቀጠረው (ቁጥር 16)?

   ________________________________________________

**የቤት ሥራ** : ሉቃስ 22:1-6 አንብቡት።

**መልመጃ**

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 22 ላይ የምናነበው አብዛኛው ነገር ክለሳ ነው ይሁን እንጂ ከእነዚህ ቁጥሮች አንድ ወይንም ሁለት አዳዲስ ሃሳቦችን ታገኛላችሁ።

1. ቁጥር 2 የሚያስታውሰን ነገር ሴረኞቹ እና አመፀኞቹ የፈሩት ነገር

   _______________________________________________________________________

2. በቁጥር 3 ላይ የተነገረን አንድ አስቀያሚ እውነታ ምንድነው?

   _______________________________________

   በቁጥር 4 ላይ የምንመለከተው ነገር ይሁዳ ኢየሱስን እንዴት መክዳት እንዳለበት በተደረገው ውይይት ላይ ተሳታፊ ነበር። ክፍሉ የሚነግረን ነገር ይሁዳ ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንዲሰጣቸው___________________________________________________ ጋር ተነጋገረ። በቁጥር 5 መሰረት የሰዎቹ ስሜት ምን ይመስል ነበር 5?

   ______________________________________________________________________

3. በዚያ ክፍል ውስጥ የተሰባሰቡት ሰዎች ፤ ሊቀ ካህናቱ እና የቤተ መቅደሱ ሃላፊዎች ይሁዳን ያሳማኑት ነገር ኢየሱስን ክዶት አሳልፎ ቢሰጣቸው ገንዘብ እንደሚያገኝ ነው። ይህም ገንዘብ

ሰላሳ ትናንሽ የብር ማዕድኖችን ነው (ማቴዎስ 26:15)! ይሁዳ ይህንኑ ለማድረግ የሚጠብቀው ምን ዓይነት የተመቻቸ ጊዜን ነው (ሉቃስ 22:6)?

______________________________________________________________________

***የቤት ሥራ*** : ዮሐንስ 13:1-2 አንብቡት። የእግዚአብሔር የማዳን እቅድ ተገለጠ…

***መልመጃ***:

"ሰዓቱ እንደደረሰ ተነግሮናል (ቁጥር 1)…" በኢየሱስ በኩል የእግዚአብሔር አብ ፈቃድ የሚከናወንበት ሰዓት ደረሰ። "ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ________________አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ________________ የወደዳቸውን እስከ ________________ወደዳቸው።

1. አሁን ደግሞ እራት እየበሉ ነው (ቁጥር 2)። በዚህን ጊዜ የስምኦን ልጅ በአስቆሮቱ ይሁዳ ላይ ምን ሆነ?

   ______________________________________________________________________

2. በሉቃስ 22:3 ላይ "ሴይጣን በይሁዳ ውስጥ ገባ" ። በዮሐንስ 13:2 ላይ ስለሴራው እንመለከታለን። ሴይጣንም የይሁዳን ሃሳብ እና ተግባርን አጣዳፈው። ይሁዳም እንዴት አድርጎ ጌታውን እንደሚከዳው አሴረ።

***<u>ምዕራፍ 4</u>***

***ማስታወስ***

*የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ሀይወት* በሚለው የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት መግቢያ ላይ ይህ ታሪክ እጅግ በጣም አስደናቂ የፍቅር ታሪክ እንደሆነ ተመልክተናል። በዮሐንስ 13:1 ላይ ደግሞ ኢየሱስ የእርሱን ሙሉውን ፍቅር የሚገልጥበት ትክክለኛው ሰዓት እንደደረሰ እንዳወቀ ተፅፏል። የሰው ዘር በሙሉ ሞት ይገባቸዋል። እኔ እና እናንተ በመስቀል ላይ በሚስማር ተቸንክረን ልንሰቀል እና ልንሞት ይገባናል። እኔ እና እናንተ መሞት ብቻ ሳይሆን ለዘላለም በሲኦል ውስጥ ልንሰቃይ ይገባናል። ኢየሱስ መስዋዕት የሆነልን ይህንን ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር እቅድ ነው። የእርሱ መከራ እና ሞት እርሱ ስለፈፀመው ጥፋት ወይንም በደል ወይንም ኃጢአት አልነበረም ነገር ግን እርሱ የከፈለው ዋጋ ስለ እኛ ኃጢአት እና እኛ መክፍል የማችለውን ነው የከፈለልን። እርሱ የተቀጣው ቅጣት፤ እርሱ የተሰቃየው ስቃይ፤እርሱ የሞተው ሞት ለእርሱ የሚገባው አልነበረም። ኃጢአት እግዚአብሔር እኛን በፈጠረበት (ዘፍጥረት 1) ሁኔታ በእግዚአብሔር ፊት ብቁ እንዳንሆን አደረገን። ሮሜ 5:6 እና 8 ስለ እግዚአብሔር ጊዜ፤ የእኛ ሁኔታ እና ስለእርሱ ፍቅር ያለውን እውነታ ይገልጣል። ጊዜ ውሰዱና ሮሜ 5:6 እና 8 በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፅፋችሁ በቃላችሁ በደንብ ለመያዝ ሞክሩ። ስለእናንተ ድነት እግዚአብሔር ያለውን እቅድ እያሰባችሁ እነዚህን ጥያቄዎችን አሰላስሏቸው:

1. እኔ አቅም በሌለኝ ጊዜ ለምንድነው የእግዚአብሔር ፍፁም ሰዓት የደረሰው?

2. ለምድነው የእግዚአብሔር ፍቅር በእኔ መንፈሳዊ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተው?
3. እኔ ኃጢአተኛ እና በኃጢአቴ ሙት ሆኜ እያለሁ ለምንድነው እርሱ ዘላለማዊ ፍቅሩን ለእኔ ያሳየኝ?

እነዚህን ጥየቄዎች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው እና እግዚአብሔር ለእናንተ ያሳየውን ፍቅር እያሰላሰላችሁ አመስግኑት። እርሱ ባያድነን ኖሮ እኛ ራሳችንን ማዳን የማንችል አቅመቢስ ሰዎች ነበር (ኤፌሶን 2:8-9) ። እኔ እና እናንተ በመተላለፋችን እና በኃጢአታችን ሙታኖች ነበርን (ኤፌሶን 2:1)።

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ፤ እኔ አቅመ ቢስ ሆኜ እያለሁ አንተ ግን ለእኔ ያሳየኸውን ታላቅ ፍቅርህን ሳስበው የምናገረው ነገር የለኝም እንዲያው ዝም ብዬ ስምህን አወድሰዋለሁኝ። እኔ በመተላለፌ እና በኃጢአት ሙት እያለሁኝ ወደደኸን ስለውለታህ የምከፍልህ ነገር የለኝም እንዲያው ዝም ብዬ አመሰግንህአለሁኝ። ለእኔ መልካም ላልሆንኩኝ ሰው እንደሞትክልኝ ሳስበው እንዲያው ዝም ብዬ በጉልበቴ ተንበርክኬ አመሰግንሃለሁኝ፤ ከአንተ ምህረት የተነሳ እኔ ምስኪን ፤ ችጋረኛ እና ኃጢአተኛው ሰው እነሆ ድኛለሁኝ።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**መግቢያ**

በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከተው ነገር የከሃዲው ሰው ተግባር ነገሮቹ እንዲሆኑ እንዳላደረገው ነው። ኢየሱስ ህይወቱን የሚሰጠው እንደ አባቱ ፈቃድ እና ለአባቱ በመታዘዝ እንጂ በክፉ ሰዎች ሴራ ተሸንፎ አይደለም።

**የቤት ሥራ**: ዮሐንስ 13:21-30 አንብቡት።

- ሊሆን ባለው ነገር ኢየሱስ የተደነቀ ይመስላችኋል?
- ኢየሱስ በአወቀው ነገር ይሁዳ ተደንቆ ይሆንን?

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ __________________________ታወከ ______________________ (ቁጥር 21)። ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ነገር ምንድነው: "እውነት፤ እውነት እላችኋለሁ______________________________________________________።"
2. ይህንን ሲሰሙ ደቀመዛሙርቱ ምን አደረጉ (ቁጥር 22)?

   ____________________________________
3. ቁጥር 23 የሚነግረን ነገር "ኢየሱስ ስለሚወድደው ደቀመዝሙር" ነው። ይህ ደቀመዝሙር ወንጌል ፀሃፊው ዮሐንስ ሲሆን የመጨረሻውን እራት ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በበላ ጊዜ

ወደ ኢየሱስ ደረት የተጠጋው ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ስምዖን ጴጥሮስ ምን አደረገ (ቁጥር 24)?

______________________________________________________________

4. ዮሐንስ ኢየሱስን የጠየቀው ነገር ምንድነው (ቁጥር 25)?

   ____________________________________________

5. ኢየሱስ ለዮሐንስ የነገረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 26)?

   ____________________________________________

6. ኢየሱስ ዳቦን ቆርሶ በጎድጓዳ ሳህን ውስጥ በሚገኘው ማባያ አጥቅሶ ለይሁዳ ሰጠው (ይህ ልማድ ለከበረ እንግዳ ብቻ የሚደረግ ነው) ይሁዳም ተቀበለው፡፡ በቁጥር 27 ላይ ይሁዳ እንደተቀበለው ምን ሆነ ይለናል____________________________________________________
7. ከዚህን ጊዜ በኋላ የይሁዳ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በሴይጣን የሚነዳው ሁለንተናዊ ማንነቱ በሴይጣን ቁጥጥር ስር ሆነ፡፡
8. በዚህን ነገር ኢየሱስ ተደንቆ ይሆንን? ለይሁዳ የተናገራቸው የመጨረሻዎቹ ቃላት ምንድናቸው (ቁጥር 27)?

   ____________________________________________________________

9. ደቀ መዛሙርቱ ሙሉ በሙሉ ግራ ተጋተዋል፡፡ ነገር ግን ከተቀመጡት ስለምን ይህንን ኢየሱስ ለይሁዳ ____________________ ማንም አላወቀም፡፡ ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ይሁዳን የተናገረው ነገር ምንድነው ብለው አሰቡ (ቁጥር 29)?

   ____________________________________________________________

10. በስተመጨረሻ የተነገረን ነገር ምንድነው (ቁጥር 30)?

    ____________________________________________…ሌሊትም ነበረ፡፡

<u>**ምዕራፍ 5**</u>

**ማሰላሰል**

ከኢየሱስ ጋር ለእራት ከተቀመጡት ደቀ መዛሙርት መካከል እራሳችሁን እንደ አንዱ አድርጋችሁ እስቲ አስቡት? ኢየሱስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ነበረ፡፡ ምግቡ ተዘጋጅቶ በማዕድ ላይ ቀርቧል፡፡ ኢየሱስ እስከተናገረበት ጊዜ ድረስ ሁሉም ነገር ሁልጊዜ ለፋሲካ በዓል እንደሚደረገው ዓይነት አመታዊ የበዓል መስተንግዶን ይመስላል፡፡ እርሱ የተናገረውን ለማመን ይከብዳችኋል፡፡ ከእኛ አንዱ? እርሱን ይከዳል? እኛ ሁላችን ይህንን ሶስት ዓመት አብረነው ነበርን፡፡ እኛ ሁላችን ከእርሱ ጋር ሆነን ብዙ ቦታ ተጉዘናል፡፡ እኛ ሁላችን እርሱ ተዓምራትን ሲያደርግ እና ከፈሪሳውያን እና ከህግ መምህራን ጋር ሲከራከር አይተነዋል፡፡ እኛ ሁላችን ከእርሱ ጋር ሆነን በሰርጉ ቤት ነበርን እንዲሁም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሲመግብ አብረነው ነበር፡፡ እኛ ሁላችን ወዳጆቹ ነን አሁን ግን እርሱ የሚናገረን ከእኛ ውስጥ አንዱ እንደሚከዳው ነው?

አንተ/ቺ እና ሌላው ደቀ መዛሙርት ስትነጋገሩ ያስታወሳችሁት ነገር በእነዚህ ሶስት ዓመታት ውስጥ ኢየሱስ በተደጋጋሚ የተናገረው ነገር እርሱን ሰዎች እንደሚከዱት፤ መከራ እንደሚደርስበት፤ በሽማግሌዎች፤ በሊቀ ካህናት እና በህግ መምህራን ወደ ውጭ እንደሚጣል እና እንደሚገደል ከዚያም በኋላ በሶስተኛው ቀን ከሙታን እንደሚነሳ ነው (ማቴዎስ 16:21 ፤ ማርቆስ 8:31-32 ፤ ሉቃስ 9:22 ፤ እና ዮሐንስ 12:32-33) ። ነገር ግን በእነዚያን ወቅቶች ከእናንተ አንዱ ይከዳኛል ብሊ አልተናገንም ነበር (ማቴዎስ 20:18) ።

አሁን ግን ለይሁዳ የሆነ ነገር እየነገረው ነው፤ ያንንም ቶሎ እንዲያደርገው (ዮሐንስ 13:27ለ)። ይሁዳ ደግሞ እራት ከሚበሉበት ቦታ ጥሎ እየሄደ ነው። እርሱ የፋሲካን እራት ትቶ እየሄደ ነው። ምን እየሆነ እንደሆነ ሊገባችሁ አልቻለም ግን ዝም ብሎ ይገርማችኋል። ጊዜው ደግሞ መሽቷል። አሁን ጊዜው ሌሊት ነው (ዮሐንስ 13:30) ። ይሁዳ ሄዷል። የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

___

### ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት ውስጥ የተረዳነው ነገር ኢየሱስ ለአባቱ ፈቃድ እንደተሰጠ እና የሰው ልጆችን ለማዳን ሲል የሚሰቃይበት እና የሚሞትበት ጊዜ እንደደረሰ እንዳወቀ ነው። በሆሳዕና እሁድ እለት ኢየሱስ እንደ እስራኤል ንጉስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም የገባበት ታሪክ የተጠናቀቀው ይሁዳ ከካህናት አለቆች እና ከሽማግሌዎች እንዲሁም ከህግ መምህራን እና ከቤተ መቅደስ ጠባቂዎች ጋር በኢየሱስ ዙሪያ ህዝብ በማይበዛበት ወቅት ኢየሱስ ለማሰር በአደረጉት ስብሰባ ነው። ይሁዳ ሳለሳ የብር ሳንቲሞችን ተቀብሎ ተስማሚ ጊዜ ሲያገኝ ኢየሱስ አሳልፎ እንደሚሰጣቸው በመስማማት ተለይቶአቸው ሄደ።

### ትግበራ

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ከእነርሱ አንዱ እንደሚከዳው ሲናገር ሁሉም የጠየቁት ጥያቄ ተመሳሳይ ነበር፤ "እኔ እሆንን ?" የሚል። ኢየሱስ እርሱን የሚከዳው ይሁዳ እንደሆነ አውቆ ይሁዳ ሊያደርግ ያለውን በቶሎ እንዲያደርግ ሳከው። "እኔ እሆንን ?" ብለን ራሳችንን ሳንጠይቅ ወደ ይሁዳ ጣታችንን መቀሰር አንችልም። ስለክህደት ማሰብ ከባድ ነው?

1. እኔ የከዳሁት ሰው አለ ወይ? ማንን ነው የከዳሁት? የእኔ እርምጃ ያስከተለው ነገር ምንድነው?

   ___

   ___

2. እኔ በራሴ የክህደት ሰለባ ነኝን? እኔን ማነው የከዳኝ? ምን ሆነ? በዚያን ጊዜ የደረሰብኝ ነገር እና የእኔ ስሜት እንዴት ነበር?

   ___

3. እኔን የከዳኝን ሰው እንዴት ነው ምላሽ የምሰጠው?

______________________________________________

4. ኢየሱስ በፍፁም እኔን ከድቶኝ አያውቅም ነገር ግን እኔ ከድቼው ይሆንን ኢየሱስ? ሁኔታዎቹስ እንዴት ነበሩ?

______________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ እኔም አንተን እንዳልከዳሁ አድርጌ ራሴን ከቆጠርኩኝ እየዋሸሁኝ ነኝ፡፡ በሌሎች ዘንድ በአንተ ላይ የፈፀምኩት በደል ካልተናዘዝኩኝ የራሴን ዝና ብቻ የማሳድድ ሰው ነኝ ማለት ነው፡፡ ትክክለኛውን ነገር ከማድረግ ይልቅ አለመታዘዝን መርጫለሁኝ፡፡ አንተን ከማወቅና ለአንተ ከመገዛት ይልቅ ለሃብት እና ንብረት ቅድሚያ የምሰጥ ሰው ነኝ፡፡ የእኔ አካሄድ ምንም እንኳን ትክክል ባይሆንም ግን አንተ ግን ፀጋህን አላቋረጥከብኝም ስለዘህ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ፡፡ አንተ እኔን ክደህ አታውቅም፡፡ አንተ አዳኜ እና የተበገሸኘኝ ነህ፡፡

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# እርስ በእርሳችሁ ተዋደዱ

## ዮሐንስ 13-17 — የኢየሱስ የመጨረሻው ትምህርት

---

**የትምህርት 3 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 3: ዮሐንስ 13-17

- ኢየሱስ፤ አገልጋዩ
- የኢየሱስ ትምህርት
- እኔ
- የኢየሱስ የሊቀ ካህኑ ፀሎት

## መግቢያ

በአገልግሎቱ ሁሉ ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት ያስተምር ነበር። ሰው አጥማጅ እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። የህይወቱ መጨረሻ የሆነው መከራው እና የመሞቱ ጊዜ እስከሚደርስበት ጊዜ ሁሉ ያስተምራቸው ነበር። ኢየሱስ በሚቀጥለው ታሪክ ውስጥ በምሳሌ አስተማራቸው። ይህንን ትምህርት ስታጠኑ ኢየሱስ ሲያስተምራቸው ምን እንደሚል በጥንቃቄ እያስተዋላችሁ አድምጡ። "ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፤ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አልላከውምና" ዮሐንስ 3:17 የሚለውን ጥቅስ አሰላስሉት።

የዮሐንስ ወንጌል ከምዕራፍ 13 እስከ 17 ያለው በኢየሱስ ትምህርቶች የተሞላ ነው። ትምህርቶቹን ስታነቡ ቃላቶቹን ልብ በሏቸው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ሲናገር እናንተም አድምጧቸው። ለእነርሱ የተናገራቸው ነገር ሁሉ ለእኔ እና ለእናንተም እየተናገረን ነው። ከእርሱ ተማሩ!

እንደ ሊቀ ካህንነቱ ኢየሱስ የፀለየው ፀሎት ከራሱ ደቀ መዛሙርት ጋር የፀለየው ነው። በዚህ In tየእርሱ ፀሎት ኢየሱስ ለራሱ፤ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት እና ለእኛም ፀለየ። አባቱን የጠየቀው ነገር ምንድነው። እናንተም የምትፀልዩት ፀሎት ልክ እንደ እርሱ ፀሎት የእርሱ ደቀ መዛሙርት ለሆኑት፤ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሊሆኑ ላሉት እና የጠፉትን ለማዳን ለወንጌል ማዳረስ በመላው ዓለም ለሚሰማሩ ሰዎች ሁሉ ይሁን።

## ትምህርት 3

***ምዕራፍ 1***

***መግቢያ***

በመጨረሻው ሳምንት ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በክብር ከገባ በኋላ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ለመሸጥ አሴረ ፣ ለፋሲካ እራት ዝግጅት ተደረገ፣ በመጨረሻው የፋሲካ የእራት እለት ኢየሱሰ ደቀ መዛሙርቱን ወደ አንድነት አመጣቸው፣ ኢየሱስ ለአለፉት ሶስት አመታት አብረውት ከነበሩት ታማኝ እና በጣም ይቀርቡት ከነበሩት ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር የፀጥታ ጊዜ እያሳለፈ ነው፡፡ ይህንን ዓለም ትቶ ወደ ወደ አባቱ የሚሄድበት ጊዜ እንደደረሰ ኢየሱስ አውቋል (ማቴዎስ 26:18)፡፡ እርሱ ተላልፎ ሊሰጥ እና ሊሰዋ ነው፡፡ ሞት በደጅ ነው፡፡ አሁን ኢየሱስ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖጆቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ (ዮሐ 13:1) እንደወደዳቸው ማሳየት ሊጀምር ነው፡፡

የምትወድዷቸውን ጓደኞቻችሁን ለእነርሱ ያላችሁን ፍቅር እንዲያውቁላችሁ ስትፈልጉ ምንድነው የምታደርጉት? ኢየሱስ አሁን ብዙ ጊዜ የለውም፡፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ሰዓታት ውስጥ ደቀ መዝሙሩ አሳልፎ ይሰጠዋል ፣ ተከታዮቹ ይክዱታል ፣ ጠላቶቹ ይቀልዱበታል ፡ ያላግጡበታል እንዲሁም ደግሞ ይገረፋል፡፡ እርሱ ይሰቃያል፣ የመጨረሻውን እስትንፋስ ተንፍሶ ህይወቱን አሳልፎ እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ ለሰዓታት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ይሰቃያል፡፡ የእርሱ ስቃይ እና ሞት የእርሱን ፍቅር ምንነት የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እናንተ ያላችሁበት ሁኔታ አጣዳፊ ቢሆን እና የጊዜ እጥረት ቢገጥማችሁ ለምትወዷቸው ሰዎች ያላችሁን ፍቅር ለመግለፅ ምንድነው የምታደርጉት?

**የቤት *ሥራ*** : በትምህርት 2 ውስጥ ለጥናታችን መሰረት እንዲሆነን በዮሐንስ ወንጌል ከ13-17 ያሉትን ምዕራፎችን እንጠቀማለን፡፡ የዚህ ምዕራፍ ክፍሎች በሶስት ወንጌላት ውስጥ ተመዝግበዋል፡፡ ትምህርታችንን ለማጠናከር ተጨማሪ መረጃዎችንም እንጠቀማለን፡፡

እስቲ እንጀምር! ዮሐንስ 13:1-17 አንብቡት፡፡

- አውዱ ምን ነበር?
- ኢየሱስ ምን አደረገ?
- የስምኦን ጴጥሮስ ችግር ምን ነበር?
- የኢየሱስ ትምህርት ምን ነበር?

**መልመጃ** :

1. በቁጥር 2-3 ውስጥ በርካታ ነገሮች በአንድ ጊዜ የሆኑ ይመስላል፡፡

   ሀ.________________________________________

   ለ.________________________________________

   ሐ.________________________________________

2. ኢየሱስ እና አብረውት የነበሩት ሰዎች ለአንድ ቀን በእግራቸው ከሄዱ በኋላ እግራቸውን መታጠብ ፈለጉ፡፡ ያደረጉት ሸበጥ ጫማ እግራቸው እንዳይቆሽሽ መከላከል አልቻለም ነበር፡፡ እግርን ማጠብ ደግሞ የቤት አገልጋይ ወይንም የባሪያ ተግባር ነው፡፡ በዚያ ስፍራ ለእራት የተሰባሰቡት ሁሉ የሆነ ሰው መጥቶ እግራቸውን እንዲያጥብላቸው ይፈልጉና ይጠብቁ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እግራቸውን ገና አልታጠቡም ነበር፡፡ በዚያ ስፍራ እንደተለመደው የእንግዶቹን እግር የሚያጥብ ባሪያ አልነበረም፡፡ እንደባሪያ ሆኖ በዚያን ስፍራ ኢየሱስ ምን አደረገ (ቁጥር 4-5)?

   ሀ.________________________________________

   ለ.________________________________________

   ሐ.________________________________________

   ከዚያ በኋላ እርሱ:

   መ.________________________________________

   ሠ.________________________________________

   ረ.________________________________________

3. ኢየሱስ ወደ ስምኦን ጴጥሮስ እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ሁሉም ነገር መልካም ይመስል ነበር፡፡ ጴጥሮስ ምን ጠየቀ (ቁጥር 6)?

   ________________________________________

4. የኢየሱስ መልስ ምን ነበር (ቁጥር 7)?

   ________________________________________

5. ጴጥሮስ ምን ብሎ ተናገረ (ቁጥር 8)?

   ________________________________

   የኢየሱስ መልስ ምን ነበር?

   ________________________________

6. ስምኦን ጴጥሮስ የተሻለ ሃሳብ እንዳለው አድርጎ አሰበ (ቁጥር 9)፡፡ የእርሱ ሃሳብ ምን ነበር?

   ________________________________________

7. ኢየሱስ ምን መለሰ (ቁጥር 10):

   ________________________________________

**ክፍል 2**

### ትምህርት

ኢየሱስ የእርሱ ደቀ መዛሙርትን እግር እያጠበ ስለ ሰውነት እጥበት አስፈላጊነት እየተናገረ ነው። ከዚያም ስለ ልበ መናገር ጀመረ፤ አያይዞም በዚያ ለተሰባሰቡት ሰዎች የእነርሱ ልቦች ንፁህ እንደሆነ ተናገረ። ነገር ግን በዚያ የነበሩት ሰዎች የሁሉም ልብ ንፁህ እንዳልሆነ አክሎ ገለፀ። በቁጥር 11 ላይ ኢየሱስ ሁላችሁም ንፁሐን አይደላችሁም ሲል ስለማን እየተናገረ ነው________________________ (ሉቃስ 22:4)። ልቡ ንፁህ አይደለም የተባለው ስለአሳልፎ ስለሚሰጠው ሰው መናገሩ ነው።

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ እግራቸውን አጥቦ ከጨረሰ በኋላ ምን አደረገ (ቁጥር 12)?

   ________________________________________________________________

2. የእርሱን ደቀ መዛሙርት ምን ጠየቃቸው ?

   ________________________________________________

3. ከዚያም ምን አለ (ቁጥር 13)? "እናንተ____________________ ትሉኛላችሁ፤ _______________፤ መልካም _______________።"

4. ቀጥሎም " እንግዲህ እኔ _______________ስሆን _______________ካጠብሁ እናንተ ደግሞ _______________ትተጣጠቡ _______________ (ቁጥር 14)" ብሎ ተናገራቸው።

5. ቁጥር 15 እና 16 ላይ ደግሞ እርሱ " እኔ _______________እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ _______________ሰጥቻችኋለሁና። እውነት፤እውነት _______________ባሪያ _______________አይበልጥም። _______________ ከላከው አይበልጥም።" አላቸው።

6. ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት እግር ማጠቡ ደቀ መዛሙርቱ እርስ በእርሳቸው እግራቸውን እንዲተጣጠቡ የሚኖረው አስፈላጊነት፤ምሳሌት እና የሚያስተላልፈው ትምህርት ምንድነው (ቁጥር 17)?

   ________________________________________________________________

### ማሰላሰል

ሀ. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ያስተማረው በምሳሌ ነው። እስቲ ራሳችሁን በዚያን ምሽት ለእራት ከተቀመጡት ሰዎች መካከል አድርጋችሁ አስቡት። የቤቱ አገልጋዮች ወይንም ባሪያዎች መጥተው እግሮቻችሁን እንዲያጥቡ መጠበቅ ምን ዓይነት ስሜትን ይፈጥራል?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ለ. በአዕምሮአችሁ ምን ይመላለሳል?

______________________________________________________________

ሐ. የሆነ ነገር ያደረጋችሁ ይመስላችኋል? የግብዣው አስተናጋጆችን እየጠራችሁ የምትጠይቁት ነገር ይኖራል? ከሁሉ በላይ እናንተ እንግዶች ናችሁ፤ ሁሉም ሰው ትኩረትን ይሻል...

______________________________________________________________

______________________________________________________________

1. ነገር ግን የእንግዶችን እግር የሚያጥብ አገልጋይ ሆነ ባሪያ በቦታው የለም። ቀጥሎ ምን ይሆናል? ከዚያም ወዲያውኑ ኢየሱስ የእናንተ ጌታ እና መምህር ከተቀመጠበት ማዕድ ተነስቶ ከላይ የደረበውን ልብስ አወለቀ። ፎጣን አንስቶ በወገቡ ላይ ጠመጠመና ውሃን በማስታጠቢያ ላይ ጨመረ። ኢየሱስ እያደረገ ያለውን ነገር ማመን አቅቷችሁ ዝም ብላችኋል። የእያንዳንዱን ሰው እግር እያጠበ ወገቡ ላይ በጠመጠመው ፎጣ ያደራርቅ ጀመር። አሁን ይህንን ስትመለከቱ ምን ታስባላችሁ?

______________________________________________________________

2. ሁኔታው የሚከበድ ነው። ምን ይሰማችኋል? የበደለኝነት ስሜት? ግን እኮ እናንተ አይደላችሁም ይህንን ማድረግ የሚጠበቅባችሁ። ይህንን ማድረግ የባሪያ ተግባር ነው! ኢየሱስ እንደ ባሪያ ሲያደርግ ስትመለከቱ ምን ተሰማችሁ? የሚገርመው ነገር እርሱ እያደረገ ያለው ነገር እናንተ ያላደጋችሁትን ነው?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. አሁን ቀጣዩ እናንተ ናችሁ። እርሱ እግራችሁን ሊያጥብ ነው! ዝም ብላችሁ ኢየሱስ እግራችሁን እንዲያጥብ ትፈቅዳላችሁ? ወይም እንደ ጴጥሮስ ተከራክራችሁ በስተመጨረሻ ኢየሱስ እግራችሁን እንዲያጥብ ትፈቅዳላችሁ? ምን ዓይነት እርምጃን የምትወስዱ ይመስላችኋል?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

4. ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት እግር አጥቦ ጨረሰ። እርሱ ከመሰቃየቱ እና ከመሞቱ በፊት ይህንን ሁኔታ ለምን ያህል ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የሚያስታውሱ ይመስላችል? እርሱ የሰጣቸው ምሳሌ በፍፁም የሚረሳ አይደለም። እርሱ የነገራቸው ነገር: እኔ ለእናንተ እንዳደረገግሁ እናንተም አድርጉ የሚል ነው። እኔ እግሮቻችሁን እንዳጠብሁ እናንተም አንዳችሁ ሌላኛችሁን እግር እጠቡ። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ያሳየው ምሳሌ ለእነርሱ ምን ማለት ነው ?

______________________________________________________________

5. ሌሎችን የሚያገለግሉ ሰዎች እንደሚባረኩ ኢየሱስ ቃል ገብቷል። ደቀ መዛሙርት እንዴት አድርገው ነው የኢየሱስ ምሳሌ እና የእርሱን ትምህርት የተከተሉት?

______________________________________________

**ምዕራፍ 3**

**ትምህርት**

በዮሐንስ ወንጌል 13-17 ያሉት ምዕራፎች የተሞሉት ኢየሱስን ለሶስት አመታት የተከተሉ እና በሁሉም ስፍራ ከእርሱ ጋር የተመላለሱ ሰዎችን በአስተማረው ትምህርቶች ነው። እርሱም ከእነርሱ አንዱ አሳልፎ እንደሚሰጠው እና ጴጥሮስ ደግሞ እንደሚከዳው ተናገረ። በዚህ ዜና ደቀ መዛሙርቱ በጣም ተረብሸዋል። ከዚያም ኢየሱስ ጨምሮ እንዲህ አላቸው፤ ምንም እንኳን እርሱ ወደ ሚሄድበት ለመሄድ ቢፈልጉም ሊከተሉት እንደማይችሉ ተናገራቸው። ኢየሱስ የተናገራቸውን ነገር ሊረዱ አልቻሉም፤ነገር ግን ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ እንዲረበሹ አላደረገም። በማበረታቻ ቃል አፅናናቸው። ዮሐንስ 14:2-3 አስተውላችሁ አንብቡት። እርሱ ምን ብሎ ተናገራቸው? "ልባችሁ አይታወክ ______________ እመኑ፤ ______________ እመኑ። ______________ ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኳችሁ ነበር። ______________________ አዘጋጅላችሁ ዘንድ ______________። ሄጄም ስፍራ ባዘጋጀሁላችሁ ፤______________________________________________ ______________________________________________።"

**ማስታወስ**

ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት የተናገረው የማፅናኛ የተስፋ ቃላት ለእኛም ናቸው። በተለይም በችግር እና በመከራ ሰዓት እንዲሁም በጥርጣሬ እና በጭንቀት ጊዜ ያፅናኑናል። ዮሐንስ 14:6 ፃፉት፤

______________________________________________

______________________________________________

እነዚህ ቃላት ዋስትናን ይሰጧችኋል። ኢየሱስ "እኔ መንገድ ነኝ..." ሲል ፤ የሰዎችን አትኩሮት፤ፈቃድ እና ልብ ሊገዙ የሚፈልጉ የተለያየ ፍልስፍናዎች ፤ትምህርት እና የሰው ጥበብ በበዛበት በዚህ ዘመን ለእናንተ ይህ የኢየሱስ አባባል ምን ትርጉም ይሰጣችኋል?

______________________________________________

______________________________________________

ኢየሱስ "እኔ እአውነት ነኝ" አለ። በዙሪያዬ ያሉ ነገሮች እውነት የሚባል ነገር የለም እያሉ ሲያውጁ ይህ የኢየሱስ ቃል ለእኔ ምን ትርጉም አለው?

______________________________________________

ኢየሱስ እንደገና "እኔ ህይወት ነኝ" አለ። ኢየሱስ እኔ ህይወት እንዲኖረኝ የተትረፈረፈ ህይወትን ይሰጠኛል (ዮሐንስ 10:10) ማለት በዙሪያዬ በተለያየ ኃጢአት እና አመፅ የተሞሉ ሰዎች በበዙበት ለእኔ የኢየሱስ ቃል ምን ትርጉሙ ይሰጠኛል (ኤፌሶን 2:1)?

___________________________________________________________________________

ይህንን ጥቅስ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው እና ሶስቱን ቃላት አሰላስሏቸው፡ መንገድ፤እውነት፤ህይወት። ኢየሱስ ወደ እግዚአብሔር አብ የሚወስድ መንገድ ነው። ኢየሱስ ብቸኛው እውነት ነው። ኢየሱስ በዚህ እና በሙመጣው ዓለም ህይወት ነው!

## ትምህርት

በዮሐንስ 15 ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት የወይን ግንድን እና ቅርንጫፉን በመጠቀም በምሳሌ ያስተምራቸው። በቁጥር 5 ላይ እርሱ "እኔ ____________________ነኝ፤እናንተ ________________ ናችሁ። በእርሱ የሆነ ሁሉ ፍሬ እንደሚያፈራ የተስፋ ቃል ገባላቸው። ከዚያ የተናገራቸው ነገር፤

"______________________________________________________________________::"

## ማስታወስ

In ዮሐንስ 15:12-13 ኢየሱስ "እኔ እንደ ወደድኋችሁ ____________________________ትዋደዱ ዘንድ ____________________________ ይህች ናት።____________________________ ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ____________________________ፍቅር ለማንም የለውም።

እንደገና ይህንን ጥቅስ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉት። አንድ ሰው በምን ዓይነት ሁኔታ ነፍሱን ለወዳጆቹ መስጠት እንደሚችል እስኪ አስቡ። በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ለወዳጃችሁ ነፍሳችሁን ለመስጠት የሚያስችል እድል ገጥሟችሁ ከሆነ ገጠመኞቻችሁን ፃፏቸው።

## <u>ምዕራፍ 4</u>

## ትምህርት

ኢየሱስ ትምህርቱን ከ14-16 ባሉት ምዕራፎችም ይቀጥላል።

1. እርሱ የተናገራቸው ነገር፤ እርሱ ________________ ይለምናል፤ _______________ከእነርሱ ጋር እንዲኖር ሌላ _______________ ይሰጣቸዋል (ዮሐንስ 14:16-17)።
2. እርሱ የተናገራቸው ነገር የእርሱን ደቀ መዛሙርት ________________ ቢጠላቸው አስቀድሞ ____________ እንደጠላ እንዲያውቁ (ዮሐንስ 15:18 ቀጥሎ) ተናገራቸው።
3. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሚያስተምራቸውን ትምህርት ያጠቃለለው እነርሱ ስለእርሱ እንደሚያዝኑ ነገር ግን የእነርሱ ______________________ወደ ______________ እንደሚለወጥ ተናገራቸው (ዮሐንስ 16:20 ቀጥሎ) ።

4. ከዚያም ይህንን ትምህርት ለምን እንዳስተማራቸው ነገራቸው እንዲህም አለ (ዮሐንስ 16:33): "በእኔ ሳላችሁ ______________እንዲሆንላችሁ ይህንን ______________። በዓለም ሳላችሁ ______________ አለባችሁ፤ ነገር ግን ______________ እኔ __________አሸንፌዋለሁ።

## ትምህርት

ዮሐንስ 17 የኢየሱስን የሊቀ ካህንነት ፀሎት የያዘ ነው።

1. ከ1-5 ባሉ ቁጥሮች ኢየሱስ ስለራሱ ነው የፀለየው። ኢየሱስ በፀሎቱ ውስጥ ስለራሱ የፀለየው ነገር ምንድነው?

   ሀ. ቁጥር 2?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

   ለ. በቁጥር 3 የዘላለምን ህይወት ትርጉም ሲሰጠው እንዲህ አለ:

   "______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________"

2. በቁጥር 6-19 ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ፀለየ። ለእነርሱ በፀለየው ፀሎት ውስጥ ኢየሱስ ምንን አጠቃለለ?

   ሀ. ቁጥር 11: "ቅዱስ አባት፤

   ______________________________________________________________________"

   ለ.ቁጥር 15: "______________________________________________________

   ______________________________________________________________________"

   ሐ.ቁጥር 17:

   "____________________________________________________________."

3. በቁጥር 20-26 ውስጥ ኢየሱስ ለሁሉም አማኞች ፀለየ። ኢየሱስ ገና ለሚያምኑ አማኞች ምን ብሎ ፀለየ?

   ሀ. ቁጥር 21ሀ:

   "______________________________________________________________________"

   ለ. ቁጥር 21ለ:

   "______________________________________________________________________"

   ሐ. ቁጥር 23:

   "______________________________________________________________________"

   መ. ቁጥር 24: "አባት ሆይ______________________________________________

   ______________________________________________________________________"

**የማሰላሰል ጥያቄ**

ኢየሱስ በይሁዳ ተላልፎ በሚሰጥበት እና ወዳጁ ጴጥሮስ በሚክደው ሌሊት ለራሱ እና ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ፀለየ፤በነጋታው ወስደውት እንዲሞት በመስቀል ላይ ሰቀሉት፤ አሰቃዩት እርሱ ግን በፅናት መከራውን ተቀበለ። እርሱ የነበረበት ሁኔታ ምን እንደሚመስል እስኪ አስቡት? በዚያው ምሽት የፀለየው ፀሎት ለእኔ እና ለእናንተም ነው እንዲሁም በእኛ ምስክርነት በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ነው። እስኪ ይህንን ፀሎት አስቡት? ኢየሱስ በሰማይ ወዳለው አባቱ ሲፀልይ እኔን እና እናንተን እያሰበ ነው። እርሱ እና አባቱ አንድ እንደሆኑ እኛም አንድ እንድንሆን አባቱም ጠየቀ። እርሱ በእኛ እንዲሆን ጠየቀ። እስኪ ይህንን ፀሎት አስቡት? ይህንን ስታሰላስሉ ምን ዓይነት ሃሳብ ወደ አዕምሮአችሁ መጣ?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

# ትምህርት አራት

# ውሰዱና ብሉ…
# ውሰዱና ጠጡ

## ማቴዎስ 26:26-28 — አዲሱ ኪዳን

---

**የትምህርት 4 ቅኝት**


ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 4:  ማቴዎስ 26:26-28

- የጌታ እራት
- የቂጣ በዓል ትምህርት
- ለኃጢአት ይቅርታ
- በጎች ይበተናሉ
- ከቶ እኔ አልሰናከልም

## መግቢያ

ትምህርት 4 የሚጀምረው ኢየሱስ “ጌታን እራት” ሲመሰርት ነው፡፡ እርሱ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ይህ ስጋዬ ነው ውሰዱና ብሉት፤ ይህ ደሜ ነው ውሰዱና ጠጡት ብሎ የተናገራቸውን ቃላት በጥንቃቄ ስሟቸው፡፡ እርሱ ስለብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ በሚፈሰው ደሙ የሚሆን አዲስ ኪዳን እንደሆነ ተናገራቸው፡፡ የፋሲካን በዓል የማክበር እና ስለበዓሉ ለሚያስተምሩ አይሁዳን የኢየሱስ ንግግር ምን ዓይነት ትርጉም እንደሚሰጣቸው አስቡት፡፡

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት ሊሆን ስላለው ከባድ ነገር ሊነግራቸው ነው፡፡ እነርሱ ደግሞ እርሱ የነገራቸውን ነገር ማመን አልፈለጉም፡፡ በዚህን ጊዜ እነርሱ የጠየቁት በመደነቅ “እኔ እሆንን ?” በማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ያሉት ነገር “በፍፁም!” ክህደት! ሊሆን አይችልም፤ ኢየሱስ የተናገራቸውን እውነት ነው ብሎ ለመቀበል አልቻሉም፡፡ ውድ ጴጥሮስ፤ደፋሩ እና ፈጣኑ ጴጥሮስ እንዲህ አለ፤ “ሁሉም በአንተ…”

እኛም ተመሳሳይ ነገር ቢገጥም በድፍረት የምንለው ነገር፤ “እኔ በፍፁም” የዚህን ዓይነት እምነት የጎደለውን ነገር አናደርግም ነው፡፡ እነርሱ …. እኔ ግን በፍፁም ብሎ በሚፎክር ሰው ላይ የኢየሱስ ዓይኖች ትኩር ብሎ እንደሚመለከት እና እንደማይደዋቸው ማስታወስን አትርሱ፡፡ እርሱ በፍቅር “ይህ ስለአንተ/አንቺ ኃጢአት በፈሰሰ ደሜ የሆነ አዲስ ኪዳን ነው” በማለት አይኖቻችንን ይመለከታል፡፡

## ትምህርት 4

**ምዕራፍ 1**

### *መግቢያ*

ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት በበላበት ጊዜ በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ሆነ፡፡ ይህንን ክስተት ሐዋሪያው ዮሐንስ በወንጌሉ ውስጥ አልጠቀሰውም ይሁን እንጂ በሌሎቹ ሶስቱ ወንጌላት ውስጥ ተጠቅሷል: ማቴዎስ 26፤ ማርቆስ 14 እና ሉቃስ 22 ፡፡ በዚያን ወቅት ምን እንደሆነ ማወቅ፤ያንን ክስተት በጣም ጠቃሚ እንዲሆን ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ እንከልሳለን፤ እንዲሁም ይህ ክስተት ለእኔ እና ለእናንተ ይህወታት ምን ጠቀሜታ እንዳለው ልንረዳ ይገባናል፡፡

ይህ ክስተት በተለምዶ "ቅዱስ ቁርባን" ይባላል፤ትክክለኛ መጠሪያው ግን "የጌታ እራት" ይባላል፡፡ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን በመሰዊያ ላይ የሚሰውት መስዋዕት እንደሆነ ያስባሉ፡፡ እነዚህ አባባሎች ሁሉ የሚናገሩት ኢየሱስ በተያዘበት ምሽት ከደቀ መዛሙርት ጋር ስለበላው ምግብ ነው፡፡ በነጋታው ኢየሱስ የሚሰቀልበት እና የሚሞትበት ስለሆነ ይህ ምሽት እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የሚበላው ምግብ/እራት/ የመጨረሻው ነው፡፡

በዚያን የፋሲካ ምሽት በኢየሩሳሌም ምን እንደሆነ አስቀድመን እንመልከት፡፡

**የቤት *ሥራ*** : *ማቴዎስ* 26:26-28 አንብቡት፡፡

- በዚህን እራት ላይ ኢየሱስ የተጠቀማቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች፡ ዳቦው እና ወይን ናቸው
- ዳቦው የተጋገረው ያለእርሾ ነው፡፡
- ወይኑ ደግሞ ከወይን ፍሬ የተጠመቀ ነው፡፡

### ትምህርት

ኢየሱስ "የጌታ እራትን" ሲመሰርት "ውሰዱና ብሉት" እና "ውሰዱና ጠጡ" ብሎ የተናገረውን ነገር መረዳት እንድንችል የተወሰኑ ቃላትን እና ሃረጎችን እንመለከታለን፡፡ አንዱ ሃረግ "የቂጣ በዓል እና ፋሲካ" የሚለው በማቴዎስ 26:17 የሚገኝ ነው፡፡ እርግጠኝነት ተጓዳኝ ምንባብ ያለው መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚኖራችሁ ነው፡፡ የቁጥር 17 ማጣቀሻ የሚገኘው በኦሪት ዘፀአት 12:17-20፤ 33-34 ፡ 39፡፡ የቂጣ በዓል ስለ ዳቦው አዘገጃጀት ብዙ ይነግረናል፡፡

***መልመጃ***: ዳቦው ፤ የእርሱ ስጋ (ዘፀአት 12)

1. እስራኤላውያን ምንን ሊያከብሩ ነው (ቁጥር 17ሀ)?

______________________________

2. ይህ የአንድ ጊዜ ብቻ ክብረ - በዓል አይደለም። ምን እንዲያደርጉ ነው የታዘዙት (ቁጥር 17ሐ)?

______________________________

3. ስለዳቦው ምንድነው የተነገረን (ቁጥር 18)?

______________________________

4. ስለእርሾውስ ምን ተነገረን (ቁጥር 19-20)?

______________________________

**መልመጃ**: ወይን፤ የእርሱ ደም

1. ማቴዎስ 26:28 ውስጥ ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ወይንን ሰጥቶ "ይህ ደሜ ነው" አለ። በመጀመሪያው የፋሲካ በዓል ደም ወሳኝ ስፍራ ነበረው (በኦሪት ዘፀአት 12:1-11)። ስለሚታረደው እንስሳ የተሰጠው *መመሪያ* ምንድነው (በኦሪት ዘፀአት 12:5)?

______________________________

2. ስለ እንስሳው ደም የተሰጠው *መመሪያ*ስ ምን ነበር (ቁጥር 7)?

______________________________

3. በዚያን ምሽት ስለሚሆነው ነገር እግዚአብሔር ምን ተናገረ (ቁጥር 12)?

______________________________

4. እስራኤላውያን በሚኖሩባቸው ቤቶች ላይ ደሙ ምልክት ይሆናል። ከደሙ የተነሳ እግዚአብሔር ለህዝቡ የገባው የተስፋ ቃል ምንድነው (ቁጥር 13)?

______________________________

## ምዕራፍ 2

### ትምህርት

የቂጣ በዓል እና ፋሲካ የተገናኙ ናቸው። በእስራኤላውያን ዘንድ ስጋና ዳቦ ዋና ምግቦች ናቸው። በበኦሪት ዘፀአት ውስጥ ስለ ምግብ ዝግጅት እግዚአብሔር ለህዝቡ *መመሪያ*ን ሲሰጥ እንመለከታለን። የእንስሳቱን ደም እና የቂጣውን አዘገጃጀት አስመልክቶ ለእስራኤላውያን አዲስ ሃሳብ ነው ይሁን እንጂ ከእግዚአብሔር አንፃር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። እነዚህ አዳዲስ ሃሳቦች ስለ ፋሲካ ዋናው መልዕክት ያም ኢየሱስ ተላልፎ በተሰጠበት እና በተያዘበት ምሽት ስለተመሰረተው የጌታ እራት ፤ "አዲሱ ኪዳን" እንድንረዳ ይረዱናል (ማቴዎስ 26:28).

የሞት መልዓክ በግብፅ ምድር ያለውን የሰውንም ሆነ የእንስሳትን የበኩር ልጅ ሁሉ እየገደለ በአለፈ ጊዜ የበግ ደም በበራቸው መቃን ላይ የቀቡትን እግዚአብሔርን ህዝብ ብቻ ነው ያዳነው (ዘፀአት 12:23)። በተመሳሳይ መልኩ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ በመስቀል ላይ ለእኛ ኃጢአት ሲል ደሙን አፈሰሰ። የእርሱ ደም እኛን የሚሸፍን ሲሆን በእምነት ከተቀበልነው እኛን ከዘላለም ኩነኔ ያድነናል። የእርሱ ደም በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ህይወትን እና ድነትን ይሰጣል። በዕብራውያን 9:22 ላይ ደም ሳይፈስ የኃጢአት ይቅርታ እንደሌለ አሰርግጦ ይነግረናል። የእርሱ ሞት ለእኛ ነፃነትን እና ሰላምን ይሰጠናል። በግብፅ ምድር በእነ ሙሴ ሰመን እንደሆነ ሁሉ ዛሬም የሞት መልዓክ በክርስቶስ የሆኑትን ያልፋቸዋል።

እራኤላውያን በግብፅ ምድር በባርነት ሲኖሩ ጌታ አርነት እንዳወጣቸው ታሪኩን ተመልክተናል። የኢየሱስ መከራ ፣ ሞት እና ትንሳኤ ለእኛ ምን እንዳደረገ ማለትም በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ ህይወትን እና ድነትን ለዘላለም እንደሚሰጥ አውቀናል። የእራኤላውያን እኛ የእኛ ድነት የተከናወነው በደም መስዋዕት ነው። አሮጌው ኪዳን የእንስሳት ደም መስዋዕት ስፈልግ አዲሱ ኪዳን ግን የተከናወነው በእንስሳት መስዋዕት እና ደም ሳይሆን በራሱ ኢየሱስ ደም ነው።

አሁን ደግሞ ተመልሰን ወደ ኢየሩሳሌም፣ ኢየሱስ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት የፋሲካን እራት ወደ በሉበት ክፍል እንሂድ። በአራት ዘፀአት በነበረን ጥናት ውስጥ እንደተመለከትነው ዓይነት ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት የሰጣቸው ዳቦ የተጋገረው ያለእርሾ በተዘጋጀ ቡኮ ነው። ዳቦው ደግሞ የእርሱ ስጋ ነው (ማቴዎስ 26:26) ።

ከዚያም ኢየሱስ ፅዋን አንስቶ አመስግኖ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። የእርሱ ትዕዛዝ ሁሉም ከፅዋው እንዲጠጡ ነው። “ከወይን የተዘጋጀው መጠጥ” አዲሱ ኪዳን የተመሰረተበት ደሙ ነው…

1. ______________________________________________
2. ______________________________________________ (ማቴዎስ 26:28)

ከአሁን በኋላ ለኃጢአት ስርየት የእንስሳት መስዋዕት እና ደም አያስፈልግም ምክንያቱ ኢየሱስ ህጉ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈልገውን መስዋዕት ስለፈፀመው ነው። እርሱ የመጣው ህጉ የሚፈልገውን የመጨረሻውን መስዋዕት፣ የራሱን ደም በማፍሰስ ለማሟላት ነው። የእርሱ ደም ለእኛ ድነታችን ነው! *ማስታወሻ:* ለሰፊ ጥናት ዕብራውያን 9:11-28 አንብቡት።

በዚህ ትምህርት ስለ መጨረሻው ኢየሱስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ስለበላው የፋሲካ እራት ተምረናል። በ1ቆሮንቶስ 11:24-25 ላይ ቅዱስ ጳውሎስ የሚነግረን፣ “ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት

በዚያች ሌሊት ________________________ አንሥቶ አመሰገነ፥ ________________________፤ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ ________________________ነው፤ ይህን ________________________ አድርጉት አለ።” እንደዚሁም ከእራት “በኋላ ________________________አንሥቶ። ይህ ጽዋ ________________________የሚሆን ________________________ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ________________________አድርጉት አለ።”

ኢየሱስ ይህ ምግብ አዲሱን ኪዳን እንደመሰረተው እና የእርሱም ደም የመጨረሻው መስዋዕት ሆኖ ለሚያምኑበት ሁሉ ለኃጢአት ይቅርታ የተከፈለ ዋጋ ሆኖ እንደሚፈስስ ተናገራቸው።

## <u>ምዕራፍ 3</u>

**ክለሳ**:

1. የጌታን እራት የመሰረተው ማነው?

   ________________________________________________

   ማቴዎስ 26:26 ተመልከቱ

2. ኢየሱስ የተጠቀመባቸው የሚታዩ ነገሮች ምንድነው? __________________ እና

   ________________

   ማቴዎስ 26፡ 29 ይመልከቱ

3. የአዲሱ ኪዳን ጠቀሜታ ምንድነው?

   ________________________________________________

   ማቴዎስ 26:28

### ትምህርት

እራኤላውያን እግዚአብሔር ከግብፅ ምድር በባርነት ከሚኖሩበት ኖሮ ነፃ ያወጣቸውን እያሰቡ በየአመቱ የፋሲካን በዓል ያከብሩታል (ኦሪት ዘፀአት 1-14) ፤ የእግዚአብሔር ህዝብ የፋሲካ በዓል የሚያከብሩት ነፃ ያወጣቸው አምላካቸው እግዚአብሔር የአዘዘውን ምግብ በመብላት ነው (በኦሪት ዘፀአት 12)። በዓሉ የሚከበርበት ምግብ የሚያጠቃልለው ቂጣ፤ እርሾ ያልገባበት ቂጣ እና የፋሲካ የበግ ጠቦት፤ ጠቦቱ ደግሞ እንከን የሌለበት ሲሆን ደሙ በእያንዳንዱ ሰው ቤት በር መቃን ላይ እንደመከላከያ ሆኖ ይቀባል። በየዓመቱ እራኤላውያን የፋሲካን በዓል የሚያከብሩት እና ምግቡንም የሚበሉት እግዚአብሔር እንዴት አድርጎ ከግብፅ የባርነት ምድር ነፃ እናደወጣቸው እና ወደ እስራኤል ምድር በነፃነት እንዲኖሩ እንዳመጣቸው በማሰብ ነው። በየዓመቱ ያልቦካ ቂጣ እና ደሙ በበር መቃን ላይ የተቀባው ጠቦት ስጋ ይበላል፤ ይህንን በማድረጋቸው እስራኤላውያኑ የመጀመሪያው ፋሲካ ምግብ ተሳታፊ ይሆናሉ ማለት ነው። ፋሲካ የሚያስተላልፈው መልዕክት ቅድመ አያቶቻችን የተለማመዱት አርነት እና ነፃነት ይህ

ትውልድም እየኖረው ያለው ያንኑ አርነት እና ነፃነት ነው የሚል ነው። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን በግብፅ ምድር የተከናወነውን የህዝቡን አርነት እና ነፃነት በየዘመኑ የሚኖረው ትውልድ ህያው በሆነ መንገድ እንዲኖረው የሚያደርገው በዚሁ መንገድ ነው።

አሁን ደግሞ በፋሲካ በዓል ምግብ እየበሉ ባሉበት ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ባሉበት አዲስን ነገር መሰረተ፤ አዲስ ኪዳን። ይህ ኪዳን የፋሲካን ምግብ የሚተካ ነው። ኢየሱስ እነርሱን የሚጋብዘው ከኃጢአት ባርነት ቅዱስ የሆነውን ምግብ (ቂጣውን እና ወይኑን) በመመገብ አርነት እንዲወጡ እንዲሳተፉ ነው። ይህ አዲሱ ኪዳን የተሰጠው ለእራኤላውያን ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ፤ እኔን እና እናንተን ጨምሮ ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ ከዚህ ቅዱስ ማዕድ ለሚሳተፉ ሁሉ ከኃጢአት ባርነት ነጣ እንዲወጡ የሚያደርግ ነው። ያልቦካው ቂጣ የክርስቶስን ስጋ ይሰጠናል። ደሙ ደግሞ የበግ ጠቦት ደም አይደለም ነገር ግን የኢየሱስ፤ የእግዚአብሔር በግ ደም ነው። ወይኑን በወሰድን ጊዜ ሁሉ ከደሙ እንካፈላለን። በየማህበረ ምዕመናኖቻችን "በጌታ እራት" ፐሮግራም ላይ በተሳተፍን ጊዜ ሁሉ እርሱ እኛን አርነት በአወጣን ተግባር ላይ እንሳተፋለን።

**ጠንካራ ጥያቄ**

ምግብ ለህይወት አስፈላጊ ነው፤ ነገር ግን አንድ ሰው ምግቡን በልቶ፤ የተበላው ምግብ ደግሞ ወደ ሆዱ ገብቶ ከአልተፈጨ እና ወደ ሰውነቱ ካልገባ ያ ለሰውነት አስፈላጊ የሆነ ምግብ ስራውን የሚሰራ ይመስላችኋል? አንድ ሰው ምግብ ካልበላ በስጋው እንደሚሞት እናውቃለን። ኢየሱስ የሚታየውን ዳቦ እና ወይንን በመጠቀም "የጌታ እራትን" መሰረተ። ለስጋችን ምግብ አስፈላጊ እና ወሳኝ ከሆነ ለመንፈሳዊ ህይወታችን ደግሞ መንፈሳዊ ምግብ ምን ያህል አስፈላጊ ይሆናን?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

1. ኢየሱስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር የበላውን የመጨረሻውን የፋሲካን እራት ስታስቡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስላሳየው ታላቅ ፍቅር ምን ትማራላችሁ?

   ____________________________________________________________

**ማስታወስ**

ኤርምያስ 31:3 እና 34 ሁለቱ ቁጥሮች በአዲሱ ኪዳን ውስጥ ስለተጠቀሰው ታላቅ መፅናናት ተስፋን የሚሰጡ ናቸው። እነዚህን ቁጥሮች ፃፏቸው እና ምን ዓይነት ትርጉም እንዳላቸው እርስ በእርሳችሁ ተነጋገሩ፤

1. ኤርምያስ 31:3 ________________________________________________

   ____________________________________________________________"

2. ይህ ቁጥር ለእኔ ምን ማለት ነው?

   ____________________________________________________________

3. ኤርምያስ 31:34 — "______________________________________________

____________________________________________________"

4. ይህ ቁጥር ለእኔ ምን ማለት ነው?

____________________________________________________

እነዚህን ጥቅሶች በአዕምሮአችሁ ያዟቸው። ጥቅሶቹን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉና እግዚአብሔር በዘላለም ፍቅሩ ኃጢአታችሁን እንዴት ይቅር እንዳለ እና እንደወደዳችሁ እንዲሁም የቀደመውን ኃጢአታችሁን እንደማያስታውሰው በተደጋጋሚ ለራሳችሁ ተናገሩ! ይህ የአዲሱ ኪዳን ተስፋ ቃል ነው! ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር የገባልንን በረከት በእምነት ስንቀበል በረከቱን እንካፈላለን።.

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ ለአንተ የምሰጠው ነገር ቢኖር ምስጋና እና ውዳሴን ብቻ ነው። አንተ ስጋህን እና ደምህን ለኃጢአታችን ስርየት ስትል ስጋህን እና ደምህን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መስዋዕት አድርገህ ሰጥተሃል። ከአንተ የተነሳ ኃጢአቴን ይቅር ተብያለሁኝ። በቀደመው ኃጢአቴ የሚከሰኝ ምንም ነገር የለም። ከአንተ የተነሳ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ተቀባይነትን እና ዘላለማዊ ፍቅሩን አግኝቻለሁኝ። በአንተ ስጋና ደም አዲሱን ኪዳን ስትመሰርት በስጋህ እና ደምህ የኃጢአት ይቅርታን እንድንቀበል ፤ ከአባትህ ጋር እንድንታረቅ እና የዘላለም ህይወት እንዲኖረን አንተ ለተከታዮችህ ስጋህን እና ደምህን እንድንካፈል አዝዘሃል።

____________________________________________________

____________________________________________________

____________________________________________________

**ምዕራፍ 4**

**ትምህርት**

እስከዚህ ድረስ በነበረን ጥናት ስለ *እግዚአብሔር's ፍቅር ፤ስለእኛ ህይወት* እና ኢየሱስ እንደ ንጉስ ክብር ወደ ኢየሩሳሌም እንደገባ ተመልክተናል። ኢየሱስ የእርሱን ደቀ መዛሙርት እግር እንዳጠበ ተመልክተናል ፤ " እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቼአችኋለሁ" ብሎ ሲናገር ሰምተነዋል። የደቀ መዛሙርቱን እግር አጥቦ ሲጨርስ ለኃጢአታችን ስርየት በሚፈሰው ደሙ የሚሆነውን አዲሱን ኪዳን መሰረተ። ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ያሳለፈውን ጊዜ ያተቃለለው በሊቀ ካህንነቱ ፀሎት ነው። ይህንን ፀሎት የፀለየው ለራሱ፤ ለእራሱ ደቀ መዛሙርት እንዲሁም ለእኔ እና ለእናንተም ጭምር ነው።

ወደ ደብረ ዘይት ተራራ ለመሄድ ያሉበትን ክፍል ከመልቀቃቸው በፊት ኢየሱስ አንድ የሚረብሻውን አዲስ ነገር ነገራቸው፤ ክፍሉን ለቅቆ የሄደው ደቀ መዝሙሩ ይሁዳ አሳልፎ ለሚገድሉት ሰዎች እንደሚሰጠው ነገራቸው።

**የቤት *ሥራ*** : *ማቴዎስ* 26:31-35 *እና ማርቆስ* 14:27 *አንብቡት*

***መልመጃ***:

1. በማቴዎስ 26:31ሀ የተናገረው ነገር ምንድነው?

   ____________________________________________________________

2. በነቢዩ ዘካርያስ የተነገሩ የትንቢት ቃላት ምንድናቸው (ቁጥር 31ለ)?

   ____________________________________________________________

   *ማስታወሻ* : ዘካርያስ 13:7 ተመልከቱ። "እረኛ" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ስለ ኢየሱስ ሲሆን "በጎቹ" ደግሞ ደቀመዛሙርቱ ናቸው።

3. ለእነርሱ ኢየሱስ የገባላቸው ቃል ምንድነው (ቁጥር 32)?

   ____________________________________________________________

4. የጴጥሮስ ቀጥተኛ ንግግር ምን ነበር (ቁጥር 33)?

   ____________________________________________________________

5. ከዚያም ምንም እንኳን ጴጥሮስ በኢየሱስ እና በሌሎች ፊት እንደማይከዳው በልበ ሙሉነት ቢናገርም ኢየሱስ ግን ጴጥሮስ እንደሚከዳው ተናገረ (ቁጥር 34):

   ____________________________________________________________

6. ጴጥሮስ ኢየሱስ ስለእርሱ የተናገረውን ነገር ለማመን አልፈለገም። እርሱ ግን ምን ብሎ ተናገረ (ቁጥር 35ሀ)?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

   *ማስታወሻ:* በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ የምናነበው ነገር ጴጥሮስ ኢየሱስን ከከዳው በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስን እንደተመለከተው ነው። አንድ መጠየቅ ያለብን ነገር ኢየሱስ ጴጥሮስን ሲመለከተው ምን ዓይነት መልዕክት እንዳስተላለፈ ነው። ኢየሱስ ለጴጥሮስ የፀለየው ፀሎት ላይ በመመስረት (ሉቃስ 22:32) እርሱ ጴጥሮስን ሲመለከት ያስተላለፈው መልዕክት ግሳፄን ነው ወይስ ርህራሄን?

7. ስለሌሎቹ የተነገረን ነገር ምንድነው (ቁጥር 35ለ)?

   ________________________________________

## ማሰላሰል

ምንም መናገር የምንችለው ነገር የለም። ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ሲከራከር አንመለከተውም። እርሱ ግን ሊሆን ያለውን እውነት ነገራት። ከኢየሱስ እና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀምጣችሁ እንደሆነ አድርጋችሁ እስቲ አስቡ። ሁሉም አንድ ነገር ሰሙ። የሰሙት እውነት ሁሉን ዝምታ ውስጥ ከተታቸው። ሁሉም የሰሙትን ነገር ማመን አልቻሉም ይሁን እንጂ ኢየሱስ እንደማይቀልድ ግን ጠንቅቀው ያውቃሉ። እርሱ በእነርሱ እያላገጠ ወይንም እያፌዘ አይደለም።

1. ደቀ መዛሙርቱ ከነበሩበት ክፍል ሲወጡ ኢየሱስ የተሳሳተ መሆኑን ለማረጋገጥ በማሰብ ይሆን?
2. ጴጥሮስ ስለሁኔታው እየደጋገመ በዝምታ ተውጦ "እኔ በፍፁም አላደርገውም" እያለ የሚያጉመተምት አይመስላችሁም?
3. ክፍሉን ስትለቅቁ በአዕምሮአችሁ ውስጥ ምን ዓይነት ሃሳብ የሚመላለስ ይመስላችኋል?

## ትግበራ

1. ሁላችንም የተናገርነው ነገር፤ "በፍፁም አላደርገውም" በማለት ነው። እስኪ " እኔ አላደርገውም …" ያላችሁበትን ጊዜ አስታውሱ

 ______________________________________________________________

 ______________________________________________________________

2. "እኔ በፍፁም አላደርገውም …" ያላችሁበት ምክንያት ምንድነው ?

 ______________________________________________________________

3. ሌሎች ሰዎች እንደዚያ ስትሉ ሰምቷችሁ ይሆን? እነርሱ ከእናንተ ሃሳብ ጋር በመስማማት እኛም በፍፁም አናደርገውም ብለው ይሆን? በክፍሉ ውስጥ የነበረው የሰው መንፈስ ምን ይመስል ነበር?

 ______________________________________________________________

4. ኢየሱስን የካዳችሁበትን ጊዜ ታስታውሳላችሁ? እርሱን እንድትክዱት ያደረጋችሁት ነገር ምንድነው?

 ______________________________________________________________

## ፀሎት

ኦ ጌታ ሆይ እኔም እንደ ጴጥሮስ "ይህንን በፍፁም አላደርገው!" እንዳልኩኝ ታውቃለህ። ይሁን እንጂ ቃሌን አጥፌ ያደረኩትን ሁሉ አንተ ታውቃለህ። በልቤ ውስጥ ፀፀት ሞልቷል። እነዚህ ፀፀቶች እኔን ምርኮኛቸው አድርገውኛል። ከዚህም የተነሳ አንተ እንድኖር የምትፈልገውን ዓይነት ኑሮ መኖር አልቻልኩም። ጌታ ኢየሱስ ሆይ የተለመደውን መልካምነትህን እና ምህረትህን አብዛልኝ። ማረኝ። አንተን በሙሉ ልቤ ማገልገል የምችልበትን አቅም ስለሰጠኸኝ እና ግንኙነታችንን ስላደስህ

አመሰግንሃለሁ፡፡ እኔን ወደ አንተ የፊቅር ህብረት ስለጋበዝከኝ አመሰግንሃለሁኝ፡፡ ጌታ ሆይ እኔን ይቅር እንዳልከኝ ሁሉ እኔም እኔን " በፍፁም አላደርገውም" ብለውኝ ግን የበደሉኝን ሁል ይቅር እንድል እርዳኝ፡፡

---

# ትምህርት አምስት

# እኔ ነኝ

## ማቴዎስ 26 እና ዮሐንስ 18 — ፀሎት፤ እስር፤ክስ፤ ክህደት

---

**የትምህርት 5 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 5: ማቴዎስ 26 እና ዮሐንስ 18

- ኢየሱስ በአትክልቱ ስፍራ
- ኢየሱስ ታሰረ
- ኢሳያስ 53:1-12
- ኢየሱስ በሐና ፤በቀያፋ እና በአይሁድ ሸንጎ ፊት
- የጴጥሮስ ክህደት

## መግቢያ

ይህ ትምህርት የሚጀምረው ኢየሱስ እና የእርሱ ደቀ መዛሙርት በጌተሰማኒ የአትክልት ሆነው ስለሆነው ክስተት ነው። የሚጠብቀውን መከራ እና ስቃይ እያሰበ በተለይም ደግሞ አባቱ እንደሚተወው ሲያውቅ የኢየሱስ ልብ ተጨንቋል። ታሪኩ የሚጀምረው አሳልፎ የሚሰጠው ሰው እየቀረበ ሲመጣ ነው። ኢየሱስ ብቻውን ቀርቷል። የደቀ መዛሙርቱ እርሱን ትቶ መሸሽ፤ የወታደሮቹ ግርፋት እና ማሰቃየት እንዲሁም የወዳጁ የጴጥሮስ ክህደት ሁሉም የእርሱ መከራ አካላት ናቸው።
እስቲ በአትኩሮት ሁኔታውን እንከታተል። ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ከመፈፀም አንፃር በቅዱሳን መፃህፍት ስለእርሱ የተፃፈውን እንዴት እንደተረዳው እና እንዴት ሲጠቅስ እንደነበረ ተመልከቱ። ኢየሱስ "እኔ ነኝ" ኢየሱስ "እኔ ነኝ" ብሎ ሊያስሩት ለመጡት ወታደሮች ሲናገራቸው " ወደ ኋላቸው እንዲሸሹ እና እንዲወድቁ" ያደረጋቸው ነገር ምንድነው? በዚህን ወቅት ሁኔታውን የተቆጣጠረው ማን እንደሆነ አስተውሉ።

ኢየሱስ ሐና እና ቀያፋ ወዳሉበት ስፍራ ተወሰደ። ሁሉም በእርሱ ላይ ስህተትን ለማግኘት እየጣረ ነው። በእርሱ ላይ በሃሰት የሚመሰክርን ሰው ይፈልጉ ነበር። ኢየሱስ እየተተፋበት እና እየተሰቃየ ነው፤ በፍርድ ቤቱ እና በአካባቢው እየተከናወነ ያለው ነገር ምንድነው?

በዚያን ሌሊት "እኔ በፍፁም ..." ብሎ በፎከረው በጴጥሮስ እና በሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ምን እየሆነ እንደሆነ አስቲ አስቡት። የኢየሱስ ዓይኖች ትኩር ብለው የጴጥሮስ ዓይኖች ሲመለከቱ ጴጥሮስ በድንገት ምርር ብሎ አለቀሰ።

## ትምህርት 5

**ምዕራፍ 1**

***መግቢያ***

*ሊታምን የማይችል ነገርን ሊያደርግ እንደሚችል ጴጥሮስ አሁን ተረድቷል። እርሱ የራሱን ጌታ፤ወዳጅ እና አስተማሪውን ኢየሱስን ክዶታል። ይሁን እንጂ ጴጥሮስ ኢየሱስ ስለእርሱ የተናገረውን አበክሮ አልቀበልም ብሎታል። በአዳራሹ የነበሩ ሰዎች ወጥተው እየሄዱ ነው፤በዚያን ወቅት "እኔ በፍፁም አልክህድህ" ብሎ የተናገረው ነገር በጴጥሮስ አዕምሮ ውስጥ እያቃጨለ ነው።*

*የማቴዎስ ወንጌል እንደሚነግረን ኢየሱስ ስለጴጥሮስ የተናገረው ነገር እርሱ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው የመጨረሻው ነገር ነው። በደቀ መዛሙርት አዕምሮ ውስጥ ምን ዓይነት ነገር እየተመላለሰ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ከእነርሱ አንዱ ጌታቸውን እና መምህራቸውን አሳልፎ እንደሚሰጥ አውቀዋል። ደቀ መዛሙርት ሁሉም ኢየሱስን ጥለውት እንደሚሸሹ እና እንደሚበተኑ፤ ብቻውን እንደሚተውት፤ አለት የሆነው ጴጥሮስ ደግሞ አንዴ ብቻ ሳይሆን ሶስት ጊዜ እንደሚክዳው አውቀዋል። ከኢየሱስ ጋር በመሆን የነበሩበት ክፍል ለቅቀው በሌሊት መንዛቸውን ቀጠሉ።*

***የቤት ሥራ*** : *ማቴዎስ* 26:36-46 *አንብቡት። ለጥናታችን እንዲረዳን በዋናነት ማቴዎስ በጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ኢየሱስ የነበረውን ሁኔታ የዘገበውን እናያለን በተጨማሪም ከማርቆስ፤ ከሉቃስ ፤እና ከዮሐንስ ወንጌላት ስለጌተሰማኒ አትክልት ስፍራ የዘገቡትንም እንመለከታለን።*

- *በጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ኢየሱስ ምን እያደረገ ነው?*
- *ደቀ መዛሙርትስ ምን እያደረጉ ነው?*
- *ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ግድ ይለው የነበረው ነገር ምንድነው?*

***መልመጃ***:

1. *ኢየሱስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ወዴት ነው የሄደው* (*ቁጥር* 36*ሀ*)?

   ________________________________________

   *ይህ የአትክልት ስፍራ የሚገኘው የት ነው* (*ዮሐንስ* 18:1; *ሉቃስ* 22:39)?

   ________________________________________________________________

   *ማስታወሻ: አሁን ካርታችሁን የምትጠቀሙበት እና ስለካርታ አጠቃቀም ያለችሁን እውቀት የምታዳብሩበት ጊዜ ነው። በተለምዶ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የመጨረሻውን እራት የበላበት በኢየሩሳሌም ምስራቃዊ ክፍል ሲሆን በተለይም አካባቢው መንፈሳውያን ወይንም በአይሁድ እምነት ውስጥ መናኞች* (Essene) *የሚበዙበት ነው ። ከእራት በኋላ ኢየሱስ ከእርሱ*

ደቀ መዛሙርት ጋር በከተማዋ ሰሜን ምስራቅ አቅጣጫ ወደ ሚገኘው የደብረ ዘይት ተራራ ሄደ። ከዚያም በፅዮን ተራራ ላይ ከተመሰረተችው ኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ከኢየሩሳሌም ግንብ ውጭ የምስራቅ አቅጣጫን ይዘው ወደ ቄድሮን ሸለቆ ይወርዳሉ። ወደ ሸለቆው ከደረሱ በኋላ ከሸለቆው ይወጡና ወደ ደብረ ዘይት ተራራ እና ወደ ጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ወደ ላይ ይወጣሉ።

2. ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 36ለ)?

__________________________________________________________

3. ኢየሱስ ወደ አትክልት ስፍራ ይዟቸው የሄደው እነማንን ነው (ማቴዎስ 26:37)?

__________________________________________________________

4. የኢየሱስን ስሜት ለመግለፅ ማቴዎስ እና ማርቆስ ምን ዓይነት ቃላትን ነው የተጠቀመው?

   ሀ. ማቴዎስ 26:37፤ 38ለ

   ________________________________________________

   ለ. ማርቆስ 14:33፤ 34

   __________________________________________________

5. ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ለወሰዳቸው ለሶስቱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ የሰጣቸው መመሪያ ምንድነው (ቁጥር 38ለ)?

__________________________________________________________

በሉቃስ 22:40 ኢየሱስ በጣም ግልፅ በሆነ መንገድ ነው የተናገራቸው። ስለምንድነው እንዲፀልዩ የተናገራቸው?

__________________________________________________________

6. ኢየሱስ ትቷቸው ለብቻው ሊፀልይ ሄደ። በማቴዎስ 26:39 መሰረት አባቱን የጠየቀው ነገር ምንድነው?

   ሀ.____________________________________________________

   ለ. ____________________________________________________

7. ኢየሱስ ሲፀልይ ሁኔታው እንዴት እንደነበር ሉቃስ እንዴት ነው የዘገበው (ሉቃስ 22:43-44)?

__________________________________________________________

__________________________________________________________

8. ኢየሱስ ከፀለየ በኋላ ወደ እርሱ ደቀ መዛሙርት ተመለሰ። እንደ ማቴዎስ 26:40ሀ ዘገባ መሰረት ምንድነው ያላቸው ?

__________________________________________________________

9. ኢየሱስ ጴጥሮስን ምንድነው ያለው (ቁጥር 40ለ)?

__________________________________________________________

10. ኢየሱስ ለምንድነው ጴጥሮስን እየተመለከተው የፀለየው (ቁጥር 41)?

________________________________________________________________

ኢየሱስ: “ወደ ፈተና ______________ ትገባ ________________፤ መንፈስስ ____________ ስጋ ግን ______________ነው” ብሎ ተናገረ።

11. በቁጥር 42 መሰረት ኢየሱስ መን አደረገ?

________________________________________________________________

በዚህን ጊዜ የእርሱ ፀሎት ምን ነበር?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

12. ቀጥሎ ወደ ደቀ መዛሙርት ሲመጣ ኢየሱስ ምን ሆነው አገኛቸው (ቁጥር 43)?

________________________________________________________________

13. ከዚያም ትቶአቸው ሄደና... ____________________________________________

________________________________________________________(ቁጥር 44)።

14. ኢየሱስ በዚህን ጊዜ ሲመለስ (ቁጥር 45-46)...

ሀ. ምንድነው የነገራቸው?

________________________________________________________________

ለ. ምንድነው የገለፀላቸው?

________________________________________________________________

ሐ. ከዚያም ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?

________________________________________________________________

<u>**ምዕራፍ 2**</u>

**ትምህርት**

ኢየሱስ መከራውን የጀመረው በጥልቅ ስቃይ እና ሃዘን ነው። “ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች።” እነዚህን ቃላት መረዳት በእርግጥ ይከብዳል፤ ይሁን እንጂ የስቃዩን እጅግ ከባድነት እና የመከራውን ብዛት የሚያሳያይ ነው። የኢየሱስ ልብ በመሪር ሃዘን ሊመታ ነው። ሉቃስ ይህንን ሲገልፅ “በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ” አለ። የእርሱን ፀሎት ስንሰማ ስለ ኢየሱስ የመከራ መጠን በቂ መረዳትን ማግኘት እንችላለን “...ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ (ማቴዎስ 26:39) ።” ይህ ፅዋ ምንድነው? ኢሳያስ 51:17 የሚናገረን ስለ “ እግዚአብሔር ______________ነው።” ኢየሱስ ከዓለም ኃጢአት የተነሳ የእግዚአብሔርን ሙሉ ቁጣ በራሱ ላይ ሊቀበል ነው።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ከእግዚአብሔር ቁጣ ኃጢአተኞችን ለማዳን ከሆነ ለምን አባቱን ይህች ፅዋ ከእኔ ትለፍ ብሎ ጠየቀ? አንድ ማስታወስ ያለብን ነገር ኢየሱሰ የእግዚአብሔር ልጅ (መለኮት) እና ፍፁም ሰው መሆኑን ነው። ማንም ሰው መቋቋም የማይችለውን የእርሱን ቁጣ እግዚአብሔር በልጁ ላይ አደረገ። ኢየሱስ በጣም አስፈሪ ነገር ከፊት ለፊቱ ተደቅኖበታል። ከሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአት የተነሳ የነደደውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለመቀበል ኢየሱስ እየተዘጋጀ ነው። አባቱ እግዚአብሔር ብቻውን ሊተወው ነው። የሚጠብቀው የመከራ ፅዋ እጅግ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ምንም እንኳን ይህንን የመከራ ፅዋ ላለመውሰድ ቢፈተንም እርሱ ግን በትህትና በፀሎቱ "የአንተ ፈቃድ እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን" በማለት ራሱን ለአባቱ ፈቃድ አስገዛ። ኢየሱስ ዮሐንስ 6:38 "_______________ ____________________ለማድረግ አይደለም እንጂ _____________________ፈቃድ ______________ ከሰማይ____________።" አለ። ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ላለማድረግ አላወላወለም። ይልቁንም ሰዓቱን ተመልክቶ "ሰዓቱ ደርሷል! እንሂድ!" አላቸው።

***መግቢያ***

ኢየሱስ የእርሱን ፀሎት ጊዜ እንደጨረሰ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱን ወደ ሚጠብቁበት ስፍራ ሄደ። ከዚያም እርሱን አሳልፎ የሚሰጠው መጣ። ኢየሱስ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ ተላልፎ የሚሰጥበት ሰዓት እንደደረሰ አወቀ (ማቴዎስ 26:45) ። አሁን እንቅስቃሴው ሊጀምር ነው። እስኪ ወደ አትክልት ስፍራው ሰዎቹ ኢየሱስን ሊያስሩት ሲመጡ ሁኔታው ምን ሊመስል እንደሚችል አስቡት።

**የቤት *ሥራ*** : ማቴዎስ 26:47-56 አንብቡት። ሌሎች የምንመለከታቸው ጥቅሶች ማርቆስ 14:43-50፤ ሉቃስ 22:57-54ሀ፤እና ዮሐንስ 18:2-12 ናቸው።

***መልመጃ***: ከማቴዎስ 26 እንጀምር።

1. ማነው የመጣው (ቁጥር 47)? _____________________________

   *ማስታወሻ* : ዮሐንስ የሚነግረን ይሁዳ ኢየሱስ ከእርሱ ደቀ መዛሙርት ጋር የት እንደሚገኝ ማወቁን (ዮሐንስ 18:2) ነው።
2. ከራሱ ጋር የወሰደው ማንን ነው?

   _____________________________________________________________
3. ሰዎቹ _________________እና __________________የያዙ ሲሆን፤ ይዘውት የነበረው የጦር መሳሪያ እንደ ዮሐንስ 18:3ሐ?

   _______________________________________________________________
4. ማነው የላካቸው?

   ________________________________________________________________________

5. አሳልፎ የሚሰጠው ሰው የሰጠው ምልክት ምን ነበር (ቁጥር 48)?

______________________________________________

6. ዮሐንስ ታሪኩን መተረኩን ይቀጥላል፡፡ ኢየሱስ ሰዎቹ ያመጡትን መጥሪያ ሊቀበል ነው፡፡ ሰዎቹን የጠየቀው ጥያቄ ምንድነው (ዮሐንስ 18:4)?

______________________________________________

7. የእነርሱ መልስ ምን ነበር (ቁጥር 5ሀ)?

______________________________________________

8. ኢየሱስ ምን ነበር የተናገራቸው (ቁጥር 5)?

______________________________________________

9. ኢየሱስ እርሱ ማን እንደሆነ ሲነግራቸው ምን ሆነ (ቁጥር 6)?

______________________________________________

10. በቁጥር 7 እና 8ሀ የቃላት ልውውጡ ቀጥሏል፡፡

ሀ. ኢየሱስ ምን አለ?

______________________________________________

ለ. የእነርሱ መልስ ምን ነበር?

______________________________________________

11. ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀም ጓጉቷል፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ በዮሐንስ 6:39 ላይ የፃፈው እና በዮሐንስ 18:9ለ ላይ የደገመው ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

12. እንደማቴዎስ 26:50 ዘገባ ከይሁዳ ጋር የመጡት ሰዎች ወደ ፊት ቀረቡ፤ኢየሱስን ያዙትና አሰሩት፡፡ ቀጥሎ ምን ሆነ (ቁጥር 51)?

______________________________________________

*ማስታወሻ:* በሉቃስ እና በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ እንደተነገረን ስምኦን ጴጥሮስ ኢየሱስን ይከተለው ነበር፡፡

13. የኢየሱስ ትዕዛዝ ምን ነበር (ቁጥር 52ሀ)?

______________________________________________

ኢየሱስ ለጴጥሮስ የነገረው ነገር ምንድነው (ቁጥር 52ለ)?

______________________________________________

"እንደዚህ____________________ ይገባል የሚሉ ____________________ እንዴት ይፈፃማሉ" በማለት ኢየሱስ ራሱን ለቃሉ ስልጣን አስገዛ (ቁጥር 54)፡፡"

14. ኢየሱስ ለተሰበሰበው ህዝብ ተናገረ፡፡ እነርሱን የጠየቀው ነገር ምንድነው?

______________________________________________

በየቀኑ ህዝቡን እያስተማረ በቤተ መቅደስ ነበር፡፡ እነርሱ እርሱን በዚያ አላሰሩትም፡፡ ኢየሱስ ሰዎቹ በግልፅ እንዲያውቁ የፈለገው ነገር ምንድነው ቁጥር 56ሀ?

---

እንደገና ኢየሱስ ህዝቡ እንዲያውቁ የፈለገው ነገር የእግዚአብሔር ቃል፤ የነቢያቱ ትንቢት እየተፈፀመ መሆኑን እንዲያውቁ ነው፡፡

15. ኢየሱስ ታሰረ፡፡ ሁሉም ደቀ መዛሙርት ምን አደረጉ (ቁጥር 56ለ)?

<u>ምዕራፍ 3</u>

**ማሰላሰል**

1. ህዝቡ ይሁዳን ተከትለው ኢየሱስን ለማሰር ወደ አትክልት ስፍራ መጡ፡፡ ወታደሮች እና ባለስልጣናቱም አብረዋቸው መጥተዋል፡፡ እነርሱ የተላኩት ከሊቀ ካህናቱ እና ከህዝቡ ሽማግሌዎች ነው፡፡ እነርሱ የመጡት ጋሻ እና ጦር ታጥቀው ነው፡፡ እነርሱ ችቦና ፋና ይዘው ነበር፡፡ እነርሱ ወደ እርሱ የመጡት በስልጣን ነበር ይሁን እንጂ ኢየሱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ እኔ ነኝ ሲላቸው እነርሱ "ወደ ኋላ ሸሽተው ወደቁ" ፡፡ እነዚህን ሰዎች ስልጣንን ሰጥተው የላኳቸው እንደማንኛውም ሰው ሰዎች ናቸው፡፡ ኢየሱስ በእዚያ የተገኘው በእግዚአብሔር ቃል ስልጣን የአባቱን ፈቃድ ሊፈፅም ነው፡፡
2. ራሳችሁን ታሪኩ እየተፈፀመ ባለበት ቦታ እንዳለ ሰው አድርጋችሁ ስታስቡ ከማን ጋር ነው የምትሰለፉት?
    - ሀ. ከይሁዳ ጋር፤ ኢየሱስን በመሳም አሳልፎ ለመስጠት…
    - ለ. ከወታደሮቹ ጋር፤ ኢየሱስን ለማሰር በመዘጋጀት…
    - ሐ. ከጴጥሮስ ጋር፤ ለኢየሱስ ለመዋጋት በመዘጋጀት…
    - መ. ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ጋር፤ እርሱን ትቶ ለመበታተን…
3. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ውስጥ በአደረጋችሁ ምርጫ ደስተኛ ናችሁ? የመረጣችሁን ምርጫ እንድትመርጡ ያደረጋችሁ ነገር ምንድነው?

---

**በጥልቀት መመልከት**

ከነቢያቱ አንዱ የሆነው ነቢዩ ኢሳያስ ስለ መሲሁ ኢየሱስ የተነበየውን እንድታነቡ ትበረታታላችሁ፡፡ ኢሳያስ 53:1-12 አንብቡት፡፡ በዚህ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ቀሪው ክፍል የምንመለከተው ነገር ስለ *እግዚአብሔር ፍቅር* እና *የእኛ ህይወት* ሲሆን ኢየሱስ እንዴት አድርጎ ራሱን በእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ስር እንዳደረገ እንደገና እንድትመለከቱ ትበረታታላችሁ፡፡ ነቢያቱ አስቀድመው የተናገሩት ይፈፀም ዘንድ እንዴት ለአባቱ ፈቃድ ለመታዘዝ እንደመረጠ በጥንቃቄ ተመልከቱ፡፡

መሲሁ ኢየሱስ ፤ መሲህ ማለት በእብራይስት ቋንቋ የተቀባው ማለት ነው (ኢሳያስ 61:1 ፤ ሉቃስ 4:18)። ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ በግሪክ ቋንቋ ክርስቶስ ማለት የተቀባ ማለት ነው!

**ትግበራ**

ኢየሱስን ለመያዝ የመጡ ሰዎች ከባለስልጣናት እና ከህዝቡ ሽማግሌዎች ስልጣን ተሰጥቷቸው ነው። ኢየሱስ ደግሞ የተላከው ከአባቱ ተልኮ ሲሆን አባቱም እርሱን ለእርሱ ቃል ተገዢ እንዲሆን አደረገው። እኔንስ ማነው የላከኝ?

1. በማን ስልጣን ስራ ሆኜ ነው የሰማዩ አባቴን ፈቃድ መፈፀም የምችለው?

   ______________________________________________

2. በዚህ ስልጣን ስር መሆኔ ለህይወቴ ምን ዓይነት ለውጥ ያመጣል?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

**መግቢያ**

የኢየሱስ ክስ ቀልድ ይመስላል። ከጌተሰማኒ ታስሮ ወደ ቤተ መቅደስ መሪዎች፤ የከተማው ባለስልጣናት እና ሮማውያን ገዢዎች ዘንድ ተወሰደ። ሊቀ ካህኑ እና ፈሪሳውያን ኢየሱስ እንዲገደል በእጅጉ ፈልገዋል። እኔ እግዚአብሔር አለምን ለማዳን እልክላችኋለሁ ብሎ ቃል የገባው እና እስራኤል ለዘመናት ሲጠብቁት የነበረው መሲሁ ነኝ የሚለውን ይህንን ሰው ከአሁን በኋላ መታገስ አልቻሉም። ወደ መስቀል የሚደረገው ጉዞ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የቆሙበት ስፍራ ተመዝግቦ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ነው።

**የቤት *ሥራ*** : ዮሐንስ 18:12-13፤ 19-24 አንብቡት።

***መልመጃ***:

1. ወታደሮቹ እና የአይሁድ ባለስልጣናት በመጀመሪያ ኢየሱስን ወዴት ነው የወሰዱት (ዮሐንስ 18:13) ____________________
2. በዚህ ቁጥር ላይ ስለ ሐና የተነገረን ነገር ምንድነው?

   ______________________________________________

3. ስለ ቀያፋስ የተነገረን ነገር ምንድነው?

   ______________________________________________

   ቀያፋ በዮሐንስ 11:49-52 የተነበየው እና ዮሐንስ 18:14 የተጠቀሰው ነገር ምንድነው?

   ______________________________________________

4. አሁን ወደ ዮሐንስ 18:19 ተሻገሩ። ኢየሱስ በሊቀ ካህኑ ሐና እየተጠየቀ ነው። እርሱ ኢየሱስን ስለምንድነው የጠየቀው (ቁጥር 19)?

ሀ.________________________________________

ለ.________________________________________

5. በአጭሩ ኢየሱስ እንዴት ነው የመለሰው (ቁጥር 20-21)?

   ________________________________________________________________________

6. የባለስልጣናቱስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 22)?

   ________________________________________________________________________

7. ኢየሱስ እንዴት ነው የመለሰው (ቁጥር 23)?

   ________________________________________________________________________

8. በእነርሱ ጥያቄ መሰረት ምንም ነገር እንዳልተፈፀመ በተረዱ ጊዜ ሐና ኢየሱስን ወዴት ነው የላከው (ቁጥር 24)?

   _______________________________________________________________

<u>ምዕራፍ 4</u>

***መግቢያ***

*ምንም እንኳን አንድን ነገር መገመት ለአዕምሮ አስቸጋሪ ቢሆንም ኢየሱስ በተያዘበት ሌሊት የእርሱ ክስ ምን ሊሆን እንደሚችል በአዕምሮአችሁ ገምቱ፡፡ ሉቃስ የሚነግረን ነገር እነርሱ ሲመጡ ______________________ ሆኖ ነበር፡፡ እዚህ ጋ ማስታወስ የሚገባችሁ ነገር የኢየሱስ የክስ ሂደት ሰዓታት በተራዘሙ ቁጥር በወታደሮች እጅ የሚደርስበት መከራ እየጨመረ መሄዱን ነው፡፡*

***የቤት ሥራ*** : *ማቴዎስ* 26:57-68 *አንብቡት፡፡ ሌላ ማንበብ ያለባችሁ ክፍሎች ማርቆስ* 14:53-65 *እና ሉቃስ* 22:63-71

***መልመጃ***:

1. ኢየሱስ የት ነው የተወሰደው (ማቴዎስ 26:57)?

   _______________________________________________

2. በዚያ የተሰባሰቡት ሰዎች እነማን ናቸው?

   _______________________________________________________

   *ማስታወሻ: ጴጥሮስ በቅርብ ርቀት ላይ ሆኖ ሁኔታውን እንደሚከታተል ነው፡፡ በዚህ ትምህርት ውስጥ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንመለከታለን፡፡*

3. ሊቀ ካህናቱ እና የአይሁድ ሸንጎ የሚፈልጉት ነገር ምንድነው (ቁጥር 59)? _______________________ ሁሉ _________________ኢየሱስ _________________ምስክር ይፈልጉ ነበር፡፡

*ማስታወሻ፡ የአይሁድ ሸንጎ ሊቀ ካህናትን፤ መምህራን ወይንም ፀሃፍትን እና የህዝቡን ሽማግሌዎችን ያጠቃለለ ነው። ይህ የአይሁድ ሸንጎ በዋናነት የይሁዳን ምድር የሚያስተዳድር ሲሆን እነርሱ ደግሞ በተራቸው ፈፁማዊ ለሆነው ለሮማውያን አገዛዝ መገዛት አለባቸው።*

4. እነርሱ ምን አገኙ (ቁጥር 60)?

   ______________________________________________________

5. ሁለቱ የሐሰት ምስክሮች ምን ብለው ተናገሩ (ቁጥር 61)? ________________________

   ______________________________________________________

   አውዱን ስናነበው እውነቱ ምን ነበር (ዮሐንስ 2:19-21)? ________________

   ______________________________________________________

6. ሊቀ ካህኑ ኢየሱስ ለቀረበበት ክስ መልስ እንዲሰጥ ፈልጓል (ቁጥር 62)። ኢየሱስ ምን ብሎ ተናገረ (ቁጥር 63)?

   ______________________________________________________

   ጥቂት ጊዜ ውሰዱና ኢሳያስ 53 አንብቡ። በዚህ ጥቅስ መሰረት ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት ቆሞ በውሸት ተከሰሰ፤ ስለ መሲሁ ኢሳያስ እንዴት ነው የገለፀው ቁጥር 7? ___________

   ______________________________________________________

7. ሊቀ ካህኑ ከኢየሱስ መስማት የፈለገው ነገር ምንድነው ማቴዎስ 26:63?

   ______________________________________________________

8. እውነቱ ግን ሊቀ ካህኑ የፈለገው ነገር ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ፤ መሲሁ መሆን አለመሆኑን ለመስማት ነበር። እንግዲህ ኢየሱስ እኔ ክርስቶስ ነኝ ብሎ ከመለሰለት እራሱን አምላክ አደረገ ብለው አምላክን በመሳደብ ክስ ሊከሱት ለዚህም ጥፋት ደግሞ ______________ ሊፈርዱበት ነው (ቁጥር 66)።

9. የኢየሱስ መልስ ምን ነበር (ቁጥር 64)? ____________________________፤ነገር ግን እላችኋለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በሃይል ቀኝ ሲቀመጥ

   ____________________________________________ታያላችሁ አለው።"

   *ቀያፋ አሁን የሚበቃውን ነገር ሰማ። እርሱ እና አብረውት ያሉት በኢየሱስ ላይ መሰወድ ያለበትን ነገር ቀድመው ወስነዋል። እነርሱ የኢሱስ ንግግር እውነተኛ ሳይሆን እግዚአብሔርን መሳደብ እንደሆነ አምነዋል። ቀያፋ ለኢየሱስ ንግግር የተሰማውን ስሜት የገለፀው እንዴት ነው* (ቁጥር 65)?

   ______________________________________________________

10. እነርሱ ኢየሱስ ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት። በእርሱ ላይ የፈፀሙት የጭካኔ ተግባራት ምንድናቸው (ቁጥር 67-68)?

______________________________________________________________

ማርቆስ እና ሉቃስ ስለእነዚህ የወታደሮች የጭካኔ ተግባራት በተጨማሪ ይገልፃሉ።

**ማሰላሰል**

1. ቀያፋ ኢየሱስ "በህያው አምላክ በእግዚአብሔር ስም" እያማለው በዚያ በነበሩት ሰዎች ፊት ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንዲነግረው ሲጠይቀው ተመለከታችሁት? ምናልባት እናንተም ኢየሱስን ተመሳሳይ ጥያቄ እየጠየቃችሁት ይሆናል። ኢየሱስ ለሰጣችሁ መልስ የእናንተ ምላሽ ምንድነው?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

2. ኢየሱስ ለእኔ እና ለእናንተ "እኔ ክርስቶስ፤ የህያው አምላክ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ" ብሎ ሲናገረን እናምነዋለን?

   _____________________________________________________________________

እርሱ ይህንን ነገር ማለቱ እና እናንተ በእርሱ ቃል ማመናችሁ በእናንተ ህይወት ላይ ምን ዓይነት ለውጥን ያመጣል?

________________________________________________________________________

_________________________________________________________________________

**በጥልቀት መመልከት**

ኢየሱስ ምርመራ እየተደረገበት በነበረበት ጊዜ ጴጥሮስ በፍርድ ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ነበር። ይኸው ጴጥሮስ እራሱ ነው አንደኛ እና ሁለተኛውን የጴጥሮስን መልዕክት የፃፈው። 1 ጴጥሮስ 2:20ለ-23ሀ ድረስ ያለውን ክፍል ከፍታችሁ አንብቡት። ጴጥሮስ ይህንን ፃፈው በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለነበሩት አዳዲስ ክርስቲያኖች እንዲሁም ለእኔ እና ለእናንተ ነው።

1. " ነገር ግን መልካም ________________ መከራን ስትቀበሉ ________________ ፥ ይህ ነገር ________________ ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ________________ ደግሞ ፍለጋውን ________________ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ ________________ ተቀብሎአልና።እርሱም ________________ አላደረገም፥ ________________ በአፉ አልተገኘበትም፤ ________________ መልሶ አልተሳደበም ________________ ሲቀበል አልዛተም፥" በማለት ፅፎልናል።

   ቁጥር 22ን ሐዋሪያው ጴጥሮስ የወሰደው ከትንቢተ ኢሳያስ ነው። (ኢሳያስ 53:9) — "__________________አላደረገም ነበር፤ __________ ተንኮል __________________ ነበር።"

2. በተጨማሪም ጴጥሮስ በቁጥር 23 ላይ "ሲሰድቡት ምልሶ ________________ መከራን ሲቀበል________________ ፤ ነገር ግን ________________ ለሚፈርደው ______________________ አሳልፎ ____________________፤" በማለት ፅፏል።

**የትግበራ ጥያቄ**

ክርስቶስ ምን ጥፋት ሳያጠፋ መከራን ተቀበለ። እርሱ ለእኛ ምሳሌ በመሆን የእርሱን ፈለግ እንድንከተል ጠርቶናል። የእርሱን መንገድ መከተል በአንድ ሰው ህይወት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖ ምንድነው? የእርሱ ጥሪ በእኔ እና በእኔ ህይወት ላይ የሚያመጣው ለውጥ ይኖራል?

________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

<u>ምዕራፍ 5</u>

**መልመጃ**: የኢየሱስን ክስ ከመመልከታችን በፊት በቅድሚያ በሊቀ ካህኑ ጊቢ በሚገኘው ፍርድ ቤት ውስጥ ምን እየተከናወነ እንደሆነ እንመለከታለን።.

1. ማቴዎስ 26:58፤ ማርቆስ 14:54 እና ሉቃስ 22:54 ስለ ጴጥሮስ የሚነግሩን ነገር ምንድነው?

   ________________________________________________________________________

2. ዮሐንስ 18:15 እና 16 ተጨማሪ መረጃን ይሰጡናል። ዮሐንስ ስለዚህ ጉዳይ የሚነግረን ነገር ምንድነው?

   ሀ. እነዚህ ሌሎች ደቀ መዛሙርት እነማን ናቸው?

   ____________________________________________________________

   ለ. ዮሐንስ ማንን ነው የሚያውቀው?

   ____________________________________________________________________

   ሐ. ይህ ደግሞ ሊቀ ካህኑ ሐና እና ሌሎች ባለስልጣናት፤ፈሪሳውያን፤እና ሊቀ ካህናቱ ወደ ተሰባሰቡበት በሊቀ ካህኑ ጊቢ ውስጥ ወደ ሚገኘው ፍርድ ቤት እንዲገባ እድልን ሰጠው። ግን ጴጥሮስስ? ጴጥሮስ የት ነው እየጠበቀ ያለው ?

   ____________________________________________________________________

   መ. ጴጥሮስ እንዴት አድርጎ ነው ወደ ፍርድ ቤቱ የገባው (ቁጥር 16)? ______________

   ____________________________________________________________________

3. አሁን ጴጥሮስ ከሌሎች ሰዎች ጋር በፍርድ ቤቱ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ይገኛል። ዮሐንስ 18:18 ይህንን ክስተት እንዲህ በማለት ይገልፀዋል:

   "________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________"

4. በእርግጠኝነት ጴጥሮስ ወደ ፍርድ ቤቱ እንዲገባ የፈቀደችው በረኛይቱ ልጅ ጴጥሮስን የጠየቀችው ነገር ምንድነው (ዮሐንስ 18:17ሀ)?

________________________________________________________________

ሀ. የጴጥሮስ ምላሽ (ቁጥር 17ለ)?

"____________________________________________________."

ለ. ሉቃስ 22:55 የሚነግረን ጴጥሮስ እሳት አንድደው ከተቀመጡ ሰዎች ጋር ተቀምጦ ነበር፤ ልጅቱም በእሳቱ ብርሃን ጴጥሮስን ትኩር ብላ ተመልክታ (ቁጥር 56), "______________________________________" አለች።

ሐ. ጴጥሮስ፤"__________________________________________________________" ብሎ መለሰላት።

መ. በማቴዎስ 26:70 እርሱ ከገሊላው ኢየሱስ ጋር እንደነበር ሲነገረው ጴጥሮስ ግን በሰዎች ሁሉ ፊት ካደ።

"____________________________________________________________."

ሠ. ማርቆስ 14:68 ጴጥሮስ የናዝሬቱ ኢየሱስን አላውቀውም ብሎ ካደ ይለናል፤ "____________________________________________________________" ወደ ውጭ ወደ ደጅ ወጣ።

5. ኢየሱስ ጴጥሮስ ሶስት ጊዜ እንደሚክዳው አሰቀድሞ ተናግሯል። ስለ ሁለቱ ጊዚያት የሚከተሉት ክፍሎች ምን ይነግሩናል?

ሀ. ማቴዎስ 26:71-74ሀ

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ለ. ማርቆስ 14:69-71

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ሐ. ሉቃስ 22:58-60

________________________________________________________________

________________________________________________________________

መ. ዮሐንስ 18:25-27ሀ)

________________________________________________________________

________________________________________________________________

6. ከዚያም አውራ ዶሮው ጮኸ። ኢየሱስ አስቀድሞ የተናገረው ለጴጥሮስ እውን ሆነ። እርሱም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አስታወሰ (ማቴዎስ 26:75ሀ):

"______________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________"

7. እናም ጴጥሮስ (ቁጥር 75ለ)...

   ________________________________________________________________

8. ሉቃስ በዚህ ላይ የሚጨምረው ነገር አለ።. ሉቃስ 22:61 የሚነግረን ነገር ልክ አውራ ዶሮው እንደጮኸ፤" ጌታም ________________ ብሎ _________________ ተመለከተው፤ጴጥሮስም _____________________________________________________________________ትዝ አለው።"

**የማሰላሰል ጥያቄ**: ኢየሱስ ጴጥሮስን የተመለከተው እና ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት የግሳጼ ነው ወይስ የርህራሄ ነው? ቁጥር 61 የሚነገረው፤ "ጴጥሮስም ____________________________________________________________________ትዝ አለው።"

ስለ ኢየሱስ መመልከት የህ የሚነግረን ነገር ምን አለ?

________________________________________________________________________________

2 ቆሮንቶስ 7:10 ተመልከቱ። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

________________________________________________________________________________

<u>**ምዕራፍ 6**</u>

**ማሰላሰል**

1. ሁኔታ ለጴጥሮስ እንዴት አስደንጋጭ ነው። ከሰዓታት በፊት እኔ በፍፁም አልክድህም ብሎ በልበ ሙሉነት ተናግሮ ነበር፤ ይሁን እንጂ ከጥቂት ሰዓታት በኂላ በፍፁም አላደርገውም ብሎ የፎከረውን ነገር አደረገው። እርሱ ኢየሱስ፤ጌታውን፤ "አንተ ክርስቶስ ___________________________________________________" ብሎ ያወጀውን (ማቴዎስ 16:16) አላውቀውም ብሎ ካደው። እርሱ አንድ ጊዜ ብቻ አይደለም ሶስት ጊዜ ነው የካደው!
2. ኢየሱስ ወደ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ እንደተመለከተው ተፅፏል። ጴጥሮስ ኢየሱስ የናገረውን ነገር አስታወሰ። ጴጥሮስ የኢየሱስን ዓይኖች መመልከቱ ወደ መሪር ለቅሶና እና በአደረገው ነገር እንዲፀፀት አደረገው። በፍፁም ያልከዳውን እና ስለእርሱ ሲል ሊሰዋ የተጋጀውን መከራን እየጠቀበለለት ያለውን ኢየሱስን ጴጥሮስ ከዳው። ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።
3. በዚያን ሌሊት ብቻውን ሆኖ የእርሱን ለኃጢአት ያለውን ዝንባሌ ተጋፈጠው። የጴጥሮስ ሃዘን እርሱ ከፈፀመው ነገር ይመልጣል። የእርሱ የክህደት ቃላት የእርሱን የልቡን ሁኔታ የሚገልጡ ናቸው። እርሱም በኃጢአት የተፀነሰ ነው። ከፍቅር የተነሳ ወደ መስቀል እየሄደ ካለው ውጭ በምንም መንገድ ጴጥሮስ ድነትን እንደመያገኝ አወቀ።

4. ያለጥርጥር ጴጥሮስ ኢየሱስ የተናገረውን ነገር ዘስታውሷል (ማቴዎስ 26:41) ደቀ መዛሙርቱ ተኝተው በአገኛቸው ጊዜ: "__________________________________________-________________________________________________________________." ከዚያም ቀጥሎ "___________________________________________________________________" አለው። ጌታ፤ ጴጥሮስ መልካምን የማድረግ ፍላጎት እንዳለውና እንዲሁም የፈተናንም ሃይል ደግሞ ያውቃል። ኢየሱስ ለጴጥሮስ የእርሱ እምነት እንዳይጠፋ እንደፀለየለት ተናግሮታል። በዚያን ሌሊት ጴጥሮስ በሃዘን እና በእፍረት ተሞልቶ በነበረበት ወቅት ምን ዓይነት ሃይል ነው የተሰጠው፤ ይህንን ስለሚያውቅ ነው ኢየሱስ የጴጥሮስ እምነት እንዳይጠፋ የፀለየለት?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

**ትግበራ**

1. ከአንድ ሰው በልበ ሙሉነት እና በድፍረት የተነገረ ቃልን ሰምቶ ሊሆን ይቻላል ተብሎ የማይታሰብን ስህተት ይፈፅማል ብሎ ማሰብ ከባድ ነው። እኛም እንደ ጴጥሮስ "እነዚህ ሁሉ _______________________እንኳን እኔ አልክድህም !" ብለን አውጀን ይሆናል። እናንተ የራሳችሁን ሃሳብ በክፍቱ ቦታ ላይ ሙሉት። "ምንም እንኳን ሁሉም ሰው የአንተን ክብር የሚነካ ነገር ቢናገሩም ፤ እኔ ግን አላደርገውም!" "ምንም እንኳን ሁሉም ሰው አለቃቸውን መጥፎ ነገር ቢናገሩም፤ እኔ ግን አላደርገውም!"
2. በአሁኑ ሰዓት ምን ዓይነት ሃሳብ ነው በአዕምሮአችሁ የሚመላለሰው?

   ________________________________________________________________________
3. ከባድ ሊሆን ይችላል ፤ቢሆንም ግን ሳታምኑበት ያደረጋችሁን እስቲ ጊዜ ወስዳችሁ አስታውሱ:

   ሀ. የአደረጋችሁትን ነገር ተቀበሉት። ትንሽ እረፍት ውሰዱ።

   ለ. እነማን ናቸው በነገሩ ውስጥ የተሳተፉት? ምን ዓይነት ቃላት ናቸው የተነገሩት፤ ምንስ ዓይነት እርምጃዎች ናቸው የተወሰዱት?

   __________________________________________________________________

   __________________________________________________________________

   ሐ. ያስከተለውስ ውጤት ምን ነበር?

   __________________________________________________________________

   መ. በፍፁም አላደርገውም ብላችሁ የፎከራችሁትን ነገር ስታደርጉት የተሰማችሁ ስሜት ምን ነበር ?

   __________________________________________________________________

**ማስታወስ**

*ታሪኩ እኛን በአደረግነው ነገር ራሳችንን ይቅርታ ማድረግ እንደማንችል አድርጎ ወይንም እግዚአብሔር በፍፁም ይቅር እንደማይለን አድርገን ያለተስፋ በጭንቀት ወጥሮን አይተወንም፡፡* 2 *ቆሮንቶስ* 7:10 *ለእያንዳንዳችን የእግዚአብሔር የምስራች ይነግረናል! "እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ* _________________________________________________________________::"

*ይህንን ጥቅስ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉት እና በአዕምሮአችሁ ሸምድዳችሁ ለመያዝ ሞክሩት፡፡ ንስሐ ወደ ድነት እና መልካም ጤንነት ይመራል! እውነተኛ ፀፀት እግዚአብሔር የእርሱን የይቅርታ ቃላት እንዲናገረን ያደርጋል፤ እንዲሁም የሰራነው በደል በእኛ እና በእግዚአብሔር መካከል ግድግዳ ሆኖ እንዳይለያየን ያደርጋል፡፡*

**ፀሎት**

*ጌታ ኢየሱስ ሆይ እንደ ጴጥሮስ እኔም አልክድህም ብዬ ማሰብ እጅግ ከባድ ነው፡፡ ይህንን በፍፁም እንደማላደርገው ማመን እፈልጋለሁኝ፡፡ በታማኝነት ህይወቴን ስፈትሸው እኔ በሃሳቤ፤በቃል እና በተግባር በአንተ ላይ ኃጢአትን ሰርቻለሁኝ፡፡ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን እና ስፍራን ለማግኘት ስል አንተን በሰዎች ፊት ክጃላሁኝ፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ ይቅር በለኝ፡፡ እውነተኛ ፀፀት ድነትን እንደሚያመጣ የተናገርከውን የአንተን ቃል ታምኜ ንስሃ እገባለሁኝ፡፡ የአንተን ፅድቅ ሳይሆን የዚህን አለም ነገሮችን የሚጠማውን ማንነቴን ፈውስልኝ፡፡ ኃጢአቴን ይቅር ስለሚለው እና በደሌን ስለሚደመስሰው፤ አንተ እኔን በፍቅር ስለምትመለከተኝ መመልከት አመሰግንሃለሁኝ፡፡*

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

____________________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# ስቀሉት

## ማቴዎስ 27 እና ሉቃስ 23 — በጲላጦስ ተፈረደበት

### የትምህርት 6 ቅኝት

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 6: ማቴዎስ 27 እና ሉቃስ 23

- ይሁዳ ፧ ያለ ተስፋ
- ጲላጦስን የገጠመው ችግር
- ኢየሱስ በሄሮድስ ፊት
- የህዝቡ ምርጫ
- በርባን ተፈታ

## መግቢያ

ነገሮች በፍጥነት እየሆኑ ነው። ሊቀ ካህናቱ እና የህዝቡ ሽማግሌዎች ኢየሱስ በፍጥነት እንዲገደል ይፈልጋሉ። ሄሮድስ ደግሞ ኢየሱስ የሆነ ምህታዊ ተዓምር ሲሰራ ማየት ይፈልጋል። የሆነ ምህታዊ ተዓምር ስራ። ጲላጦስ በበኩሉ ኢየሱስ እንዲፈታ ይፈልጋል። ይህ ክርስቶስ፤ የእግዚአብሔር ልጅ፤የአይሁድ ንጉስ ስለተባከው ሰው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማናቸውም አያውቁም።

አሁን አንድ አደገኛ ወንጀለኛ ሊገለጥ ነው። እርሱ ማነው? ከየት ነው የመጣው? ምንድነው ያደረገው? ለምንድነው የታሰረው? በእነዚህ ነገሮች ሁሉ የእርሱ ድርሻ ምንድነው? ስለዚህ ሰው ያላችሁን ሃሳብ ቶሎ ብላችሁ አታቋርጡ። የእርሱ በነፃ ከእስራቱ መፈታቱን እና የእናንተንም ሁኔታ እስቲ አስቡት። ሰውዬውን የተለያየ ጥያቄዎች እንደጠየቃችሁት ሁሉ ራሳችሁንም: እኔ ማን ነኝ? ምንድነው ያደረግሁት? በዚህ ሁሉ ውስጥ የእኔ ድርሻ ምንድነው?

የኢየሱስን መሞት አጥብቀው ከሚፈልጉ ሰዎች ውጭ ሌሎቹ ሰዎች ምን እንደሚሆን እና ምን እንደሚያደርጉት እርግጠኛ አይደሉም። ጲላጦስ ኢየሱስ እንዲሰቀል አሳልፎ እስከሰጠው ጊዜ ድረስ ሰዎቹ ቁጣቸውን እና ጩኸታውን አላቆሙም ነበር።

## ትምህርት 6

**ምዕራፍ 1**

***መግቢያ***

*በትምህርት 5 ላይ ስለ ጴጥሮስ ክህደት፤ ጌታን እንዴት እንደካደው እና ከዚያ ምርር ብሎ እንዳለቀሰ ተመልክተናል። ኢየሱስን አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ምን ደረሰበት? ስለእርሱ በመጨረሻ የሰማነው በአትክልቱ ስፍራ ኢየሱስን በመሳም አሳልፎ ሲሰጠው ነው። በይሁዳ ላይ ምን እንደደረሰበት ማቴዎስ ብቻ ነው የዘገበው። (ማስታወሻ : ቅዱስ ሉቃስ በሐዋሪያት ስራ 1:15-20 ላይ አጭር መግለጫን ሰጥቶናል ) ።*

**የቤት *ሥራ*** : *ማቴዎስ* 27:1-10 *አንብቡት*

- *ይሁዳ የአመነው ነገር ምንድነው?*
- *የእርሱ ተባባሪ የነበረ ሰዎች ምን አደረጉ?*
- *ይሁዳ ምን ዓይነት እርምጃን ወሰደ?*

***መልመጃ***:

1. *ስለ ሊቀ ካህናቱ እና የህዝቡ ሽማግሌዎች የተነገረን ነገር ምንድነው* (*ቁጥር* 1)?

   ________________________________________________________________

2. *አስረውም፤ለገዢው*____________________________________________*አሳልፈው*

   ______________ (*ቁጥር* 2)።

3. *አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንዲፀፀት ያደረገው ነገር ምንድነው* (*ቁጥር* 3*ሀ*)?

   ________________________________________________________________

4. *ሃሳቡን እንዲቀይር ያደረገው ነገር ምንድነው። ምን አደረገ?*

   ____________________________________________ (*ቁጥር* 3*ለ*)። *ብሩን ለማን ነው የመለሰው?*

   ________________________________________________________________

5. *ይሁዳ ምን ብሎ ተናገራቸው* (*ቁጥር* 4*ሀ*)?

   ________________________________________________________________

6. *ሊቀ ካህናቱ እና የህዝቡ ሽማግሌዎች ኢየሱስን አሳልፎ በሰጠው በይሁዳ ጉዳይ ሃላፊነቱን አለወሰዱም። የእነርሱ ምላሽ ምን ነበር?*

   ________________________________________________________________

7. *ይሁዳ ምን አደረገ* (*ቁጥር* 5)?

ሀ. ____________________________________________

ለ. ____________________________________________

ሐ. ____________________________________________

8. ሊቀ ካህናቱ ገንዘቡን አንስተው በብሩ የሆነ ነገር ለማድረግ ሄዱ። ለምንድነው ገንዘቡን ወደ መባ ያልጨመሩት (ቁጥር 6)?

____________________________________________

ገንዘቡን እንዴት ሊጠቀሙበት ወሰኑ (ቁጥር 7)?

____________________________________________

9. የቀብር ቦታው ስሙ ምን ያባላል (ቁጥር 8)?

____________________________________________

10. ሌላ ትንቢት በማቴዎስ 27:9-10 ተፈፅሟል። ኤርምያስ ምንድነው ያለው?

____________________________________________

**ማሰላሰል**

1. ይሁዳ ስለ ኢየሱስ እውነት ነው ብሎ ያመነበትን ነገር ሲከተል የነበረ ሰው ነው። እርሱ ኢየሱስ መሲሁ፤ እግዚአብሔር ወደ ዓለም ሊልክ ቃል የገባው ሰው እንደሆነ ሲሆን ይሁን እንጂ ስለመሲሁ ያለው አመለካከት እንደ አብዛኛው አይሁዳዊ መሲሁ እንደ ሃይለኛ የፖለቲካ መሪ ጨቋኙን የሮማውያንን ገዢዎችን በሃይል ፤ በጦርነት አስወግዶ እስራኤልን እንደሚገዛ ነው። ኢየሱስ ምድራዊውን መንግስት ቢያቋቋም ኖሮ ይሁዳ በዚህ መንግስት ውስጥ ቁልፍ የሆነ ስልጣንን እንደሚይዝ ተስፋ አደርጎ ነበር። ይሁን እንጂ ኢየሱስ የሚናገረው ልዩ ስለሆነ ከዚህ ምድር ስላልሆነ መንግስት ነው።
2. በዮሐንስ 12:4-6 ውስጥ ስለይሁዳ ሌላ ነገር እናያለን። ይሁዳ በተወሰነ ደረጃ የገንዘብ አስተዳደር ችሎታ ያለው ነው ለዚም ነው ለደቀ መዛሙርት ዘቃቤ ንዋይ ሆኖ የተሾመው። እነዚህ ቁጥሮች ስለይሁዳ ልብ እና ባህሪይ ምን የሚገልጠው ነገር አለ?

____________________________________________

____________________________________________

3. ይህ የሚያስዝን ነገር ነው። ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ ሰጠ ከዚያም ኢየሱስ እጆቹ እና እግሮቹ በሚስማር ተቸንክረው በመስቀል ላይ ተሰቀለ። የይሁዳ ሞት ራስን ማጥፋት ነው። ምህረት የለሹ እንጨት ላይ ራሱን ሰቅሎ ገደለ። በሌብነት እና በግብዝነት፤ በማታለል እና በክህደት የተሞላው ህይወቱ በዘላለም ህይወት ተስፋ የተሞላ አልነበረም። ነገር ግን በሌሎች ሰዎች ዘንድ ታላቅ መስሎ እንዲታይ ያደረገው ነገር የህይወቱን ተስፋ እና ህልም በሙሉ አጠፋበት። ያለ ተስፋ፤ ያለ ንስሃ እና ያለ ይቅርታ ሞተ፤ ለዘላለም ሞት እና ስቃይ ዳግም እድል ላያገኝ እራሱን ገደለ።

4. አስቲ ለአጭር ጊዜ በጴጥሮስ እና ይሁዳ መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከቱ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ያላቸው እምነት ምን ነበር፧ እርሱ ማነው ፧ ለምንስ መጣ?

| ጥቅሶች | ጴጥሮስ |
|---|---|
| ማቴዎስ 16:15-16 | |
| ዮሐንስ 6:68 | |
| ዮሐንስ 6:69 | |

| ጥቅሶች | ይሁዳ |
|---|---|
| ዮሐንስ 6:63ለ-64 | |
| ዮሐንስ 6:70-71 | |
| ዮሐንስ 8:44-47 | |
| ዮሐንስ 12:6 | |

**ማሰላሰል**

2 ቆሮንቶስ 7:10 ለመከለስ እስኪ አጭር ጊዜ ውሰዱ፡፡ እነዚህ ቃላት ስለ ጴጥሮስ እና ይሁዳ ልዩነት ምን የሚነግሩን ነገር አለ? ሁለቱ ከኢየሱስ ጋር ስለአላቸው ግንኙነት የሚነግረን ነገር ምንድነው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ! እኔም እንደ ጴጥሮስ “አንተ የዘላለም ህይወት ቃል አለህ” በማለት አውጃለሁ፡፡ የአንተ መንፈስ ቅዱስ አንተ ኢየሱስ ቅዱሱ እግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ እንዳምን አስችሎኛል፡፡ እንደ ጴጥሮስ እኔም አንተ “ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ” እንደሆንክ አውጃለሁ፡፡ እኔም ልክ እንደ ጴጥሮስ በሰማያዊው አባቴ ነገሮች ተገልጠውልኛ፡፡ ይህንን ሳስብ እንዴት ያለ አስደናቂ መፅናናትን ነው የሚሰጡኝ ! ምንም እንኳን የምናገረው እና የማደርገው ነገር ክፉዎች እና አንተን የማያስደስት ቢሆንም የምኖረው ኑሮ ግን በአንተ ፍቅር እና ይቅርታ ነው፡፡ ለዚህ ታላቅ ውለታህ ምስጋናዬን እና ውዳሴዬን አቀርባለሁኝ፡፡

## ምዕራፍ 2

### መግቢያ

በሊቀ ካህ ሐና እና በየአይሁድ ሸንጎ ፊት በእርሱ ላይ የሚደረግበትን ምርመራ ኢየሱስ ጨረሰ። እርሱ ተደበደበ፤በጥፊ ተመታ፤አላገጡበት፤ፊቱን በጨርቅ ሸፈኑት እንዲሁም ተፉበት። በእርሱ ላይ ምስክሮች በሃሰት መሰከሩበት። አምላክን በመሳደብ ተከሰሰ፤ከዚያም የሞት ፍርድ ተፈረደበት። በማለዳ ሁሉም ባሉበት፤ የአይሁድን ሸንጎ ጨምሮ በተገኙበት ውሳኔው ተወሰነ (ማርቆስ 15:1) ። አስረውት ለጵላጦስ አሳልፈው ሰጡት (ሉቃስ 23:1)። በዚህን ጊዜ ሊሆን ይችላል ኢየሱስ የካደውን ወዳጁን ጴጥሮስን የተመለከተው።

ኢየሱስ ሌሊቱን በሙሉ የክሱን ሂደት ሲያካሂዱ እርሱን ሲያንገላቱት፤ ሲያላግጡበት፤ ሲደበድቡት፤ ሲያሰቃዩት እንደነበር ስታነቡ ያለጥርጥር ከደረሰበት መከራ እና ስቃይ ብዛት የተነሳ ተዳክሞ እንደነበረ መገመት አያቅትም። የመጨረሻውን የፋሲካ እራት ከበላበት ክፍል ወደ ኢየሩሳሌም ደቡባዊ ምዕራብ ክፍል ከዚያም ወደ ጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ የተጓዘው በእግሩ ነበር። እርሱን የያዙት ወታደሮች ያመጡት የቀያፋ ቤት ወደ ሚገኝበት መልሰው የከተማዋ ደቡባዊ ምዕራብ ክፍል ነው። ከዚያም መልሰው እርሱን ወደ ጲላጦስ ቤተ መንግስት ወሰዱት።

ጥናታችንን ከመቀጠላችን በፊት የምናነሳው አንድ ጠቃሚ ጉዳይ አለ። እያንዳንዱ ወንጌላት (ማቴዎስ፤ ማርቆስ፤ ሉቃስ ፤ እና ዮሐንስ) የእየሱስን የክስ ሂደት፤ የእርሱን መከራ እና የእርሱን ሞት ጠቅሰዋል። ማስታወስ ያለብን ነገር እያንዳንዱ የወንጌል ፀሃፊ ወንጌሉን የፃፈው የተለያዩ ተደራሾችን ለመድረስ ከያዙት ዓላማ አንፃር ያንንን ዓላማ ለማሳካት ነው። ጥናታችንን የሉቃስ ወንጌልን መሰረት አድርገን እንቀጥላለን።

**የቤት *ሥራ*** : ሉቃስ 23:1-7 አንብቡት።

- ቀጥሎ ኢየሱስ ወዴት ነው የተላከው?
- በእርሱ ላይ የተመሰረቱት ክሶች ምንድናቸው?
- የጵላጦስ ድምዳሜ ምን ነበር?

*መልመጃ*:

1. ጉባኤው ኢየሱስን ወዴት ነው የወሰዱት (ቁጥር 1)? ____________________

ጲላጦስ ኢየሱስ በነበረበት ዘመን እና ከዚያም በኋላ ከ26 ዓ.ም. እስከ 36 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ይሁዳን ይገዛ የነበረ ሮማዊ አገረ ገዢ ነው። ስለ እርሱ ብዙ የምናውቀው ነገር የለም ነገር ግን በዚያን ጊዜ ይሁዳን እንዲያስተዳደር በሮማውያን መሾም ብዙም የሚፈለግ ስራ አይደለም። አንድ የምናውቀው ነገር ከእርሱ ውሳኔ የተነሳ ሁከት ቢነሳ የጵላጦስ የፖለቲካ ስልጣን አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል። ይህንን በአዕምሮአችን ይዘን ጥናታችንን እንቀጥል...

2. በኢየሱስ ላይ ክሶች ተመስርተዋል። ምን ብለው ነው የከሰሱት (ቁጥር 2)?

   ሀ.________________________________________________________

   ለ. ________________________________________________________

   ሐ.________________________________________________________

3. ጲላጦስ ኢየሱስን የጠየቀው ነገር ምንድነው (ቁጥር 3)?

   ______________________________________________________

   ኢየሱስ የሰጠው መልስ፤

   "__________________________________________________________________."

4. ለኢየሱስ ከሳሾች ጲላጦስ የነገራው ነገር ምንድነው (ቁጥር 4)?

   ___________________________________________________________________________

5. ህዝቡ ምን እንዲሆን ነው አጥብቀው የጠየቁት (ቁጥር 5)?

   "__________________________________________________________________________

   ___________________________________________________________________________"

6. አሁን ጲላጦስ ማወቅ የፈለገው ነገር ምንድነው (ቁጥር 6)?

   ___________________________________________________________________________

7. ጲላጦስ ከዚህ ከባድ ሁኔታ አንፃር ተወጣጥሯል። ኢየሱስ __________________________ መሆኑን በአወቀ ጊዜ ጲላጦስ ምን አደረገ (ቁጥር 7)?

   ___________________________________________________________________________

   ኢየሱስ መጀመሪያ ወደ የሐና ከዚያም ወደ ቀያፋ እንደተወሰደ አውቋል። እነዚያ ከቀያፋ ጋር የተሰባሰቡት ሰዎች ኢየሱስ እግዚአብሔርን ሰድቧል በሚል ምክንያት እንዲሞት ወስነዋል። ሊቀ ካህናቱ እና ሌሎች የአይሁድ ባለስልጣናት እርሱን የመግደል መብት አልነበራቸውም ከዚህም የተነሳ ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። ጲላጦስ ኢየሱስን ከመረመረው በኋላ ወደ ሄሮድስ እንደላከው የፃፈው ሉቃስ ብቻ ነው።

8. በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ሄሮድስ ከገሊላ መጥቶ ኢየሩሳሌምን እየጎበኘ የነበረው ፋሲካን ሊያከብር ነው። የእርሱ ቤተ መንግስት የሚገኘው ከቀያፋ ቤት ብዙም ሳይርቅ በኢየሩሳሌም ምራባዊ ክፍል ነው።

ሀ.ለኢየሱስ የሄሮድስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 8ሀ)?

______________________________________________

ለ. ለምን (ቁጥር 8ለ)?

______________________________________________

ሐ. ለምን (ቁጥር 8ሐ)?

______________________________________________

9. ቁጥር 9: ሄሮድስ

______________________________________________

ግን ኢየሱስ

______________________________________________

10. ቁጥር 10: ሊቀ ካህናቱ እና መምህራኑ

______________________________________________

11. ቁጥር 11ሀ: ሄሮድስ እና የእርሱ ወታደሮች

______________________________________________

ቁጥር 11ለ: ከዚያም ____________________ መልሶ __________ሰደደው።

12. በሄሮድስ እና በጲላጦስ መካከል ስለነበረው ነገር ምን የምናውቀው ነገር አለ ቁጥር 12?

______________________________________________

<u>ምዕራፍ 3</u>

**ማሰላሰል**

1. በኢየሱስ ላይ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በእርግጠኝነት የሚያውቅ የለም። እርሱን መግደል የሚፈልጉ ሰዎች እርሱን የመግደል ስልጣን የላቸውም። ስልጣን ያለው ሰው ደግሞ እርሱን የሚገድልበትን ምንም ዓይነት ምክንያት አላገኘም። ምንም ማድረግ አንችልም ነገር ግን ይህንን ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን: በኢየሱስ ላይ ምን አድርጌ ይሆን ? __________

______________________________________________

እርሱን ከሚገድሉት ጋር ተባብሬ ቢሆን፤ ይህንን ያደረኩበት ምክንያት…

ሀ. ስራሱ ማንነት ስላለው እውቀት?

______________________________________________

ለ. በትምህርቱ ንስሐ ግባ/ቢ ስለሚለኝ?

______________________________________________

ሐ. ሕይቴን ከተቆጣጠረው ነገር አንፃር እርሱ ስለማይመቸኝ?

---

እንደገና በኢየሱስ ላይ ያደረኩት ነገር ምንድነው?

---

2. ሄሮድስ ኢየሱስን በማየቱ ተደስቷል። እርሱ የተወሰነ ምህታታዊ ተዓምራትን ለማየት ጓጉቷል። እርሱ ስለኢየሱስ ከሰማው አንፃር የተወሰነ ተዓምራትን ለማየት ተስፋ አድርጎ ነበር። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ዝም ከማለቱ የተነሳ ሄሮድስ የጠበቀውን ነገር አልተመለከተም። በእርግጠኝነት ኢየሱስ ተዓምራትን እንዲያሳየው አልሞከረም ይሆናል። እኔስ እንዴት ነኝ? እኔ ሄሮድስ ነኝ? ኢየሱስ ለእኔ የሚያደርገውን ነገር ለማየት እፈልጋለሁኝ? ለእኔ ምን ዓይነት ተዓምራት እንዲሰራልኝ ነው የምፈልገው? አዲስ ስራ? ዘመናዊ መኪና? ፈውስ? ልጅ ማርገዝ? በእርሱ ከማመኔ በፊት የምጠይቀው ተዓምራት ምንድናቸው?

---

---

ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእኔ አዳኝ እና የተቤዤን ነው ብዬ በእምነት ከመቀበል በፊት በእግዚአብሔር ሃይል ምህታታዊ ተዓምርን ብቻ እድጠብቅ ያደረገኝ ነገር ምንድነው?

---

---

3. የኢየሱስ ከሳሾች በከፍተኛ ሁኔታ ሁከት እየፈጠሩ ነው። እርሱ እንዲሞት በብርቱ ስለፈለጉ ሁከት መፍጠራቸውን ቀጥለዋል። እኔ በምን መልኩ ነው ከእርሱ ከሳሾች ጋር የምመሳሰለው? በኢየሱስ ተናድጄበታለሁ? እኔን ትቶኛል? እኔ የፈለግሁትን ነገር አላደረገም ይሆንን? ለምንድነው እኔን የሚያናድደኝ? ለምንድነው ለእርሱ ያለኝን ሃሳብ መቀየር ያልቻልኩኝ? ለእኔ ያለውን የእርሱ ታላቅ ፍቅር እንዳልረዳ አንቆ የያዘኝ እና አላንቀሳቅስ ብሎ ያሰረኝ ነገር ምንድነው ?

---

---

4. ሄሮድስ እና የእርሱ ወታደሮች በእርሱ ላይ ቀለዱበት። የሚያምር ካባ አልብሰውት፤ ከአላገጡበት እና ከቀለዱበት በኂላ የአይሁድ ንጉሱ የተባለውን ኢየሱስን ወደ ጲላጦስ መልሰው ላኩት። እኔስ በኢየሱስ ላይ ቀልጄበት ይሆን? ኢየሱስ የእኔ ቀልድ ማሟሟቂያ አድርጌ ይሆንን? በእርሱ ላይ የማይሆን አስተያየት እንድሰጥ፤ እንዳላግጥበት እና እንድቀልድበት ፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነውን እርሱን ከማምለክ ይልቅ ቆንጆ ካባ አልብሼው እንዳሾፍበት ያደረገኝ ነገር ምንድነው?

---

______________________________________________________________________

**ፀሎት**

በኢየሱስ ላይ ስላደረጋችሁት ነገር ጊዜ ወስዳችሁ ንስሃ ግቡ። ወደ ጌታ በትህትና ቅረቡ እና ስለ እናንተ ሲል በጲላጦስ እጅ መከራን ስለተቀበለ እርሱን እያመሰገናችሁ በኃጢአታችሁ ደግሞ ንስሃ ግቡ።

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ከዚያም የእግዚአብሔርን የምስራች ቃልን በጥንቃቄ እያደመጣችሁ በተመስጦ ሆናችሁ ይህንን ክፍል አንብቡት፤ 1 ዮሐንስ 1:9,

"______________________________________________________________________

______________________________________________________________________"

**<u>ምዕራፍ 4</u>**

***መግቢያ***:

ኢየሱስ ወደ ጲላጦስ ተመልሶ ተወሰደ። ችግሩ እንደገና ወደ ጲላጦስ እጆች ተመለሰ። ይህ ኢየሱስ የተባለውን ሰው እርሱ ምን ያደርግ ይሆን? ሌሎቹ በኢየሱስ ላይ ያደረጉትን አውቀናል። አሁን የራሱን ባህሪይ ለመግለፅ ተራው የጲላጦስ ነው።

**የቤት *ሥራ*** : ሉቃስ 23:13-25 አንብቡት

- ጲላጦስ እነማንን ነው የሰበሰበው?
- ህዝቡ ማን እንዲፈታላቸው ነው ግድ ያሉት?
- ጲላጦስ ኢየሱስን ምን ሊያደርገው ነው?
- የጲላጦስ ውሳኔ ምን ነበር?

***መልመጃ***:

1. ጲላጦስ እነማንን ነው የሰበሰበው (ቁጥር 13)?

   ______________________________________

2. ምንድነው የነገራቸው?

   *ሀ.*ቁጥር 14*ሀ*:

   ______________________________________________________

ለ. ቁጥር 14ለ:

_______________________________________________

ሐ. ቁጥር 14ሐ:

_______________________________________________

3. ጲላጦስ  ስለ ሄሮድስ ምን አለ (ቁጥር 15ሀ)?

   _______________________________

4. ጲላጦስ ስለ ኢየሱስ ምን አለ (ቁጥር 15ለ)?

   _______________________________

5. ለእነዚህ ሰዎች ጲላጦስ ምን እንደሚያደርግ ነው የነገረው (ቁጥር 16)?

   _______________________________________________

*ማስታወሻ:* የሮማውያ ቅጣት እጅግ ዘግናኝ ነው፤ አንዳንድ ጊዜ እስረኛው የተወሰነበት ቅጣት ከመፈፀሙ በፊት የሚሞት ሁኔታ አለ፡፡ ቅጣቱም ከባድ የሆነ ድብደባን እና ግርፋትን ያጠቃለለ ነው፡፡

**ትምህርት**

በዚያን ዘመን በነበረው ልማድ መሰረት የፋሲካ በዓል ሲከበር ህዝቡ የሚመርጠው እስረኛ በነፃ ይለቀቃል (ማቴዎስ 27:15 ቀጥሎ) ፡፡ እንደ ማቴዎስ 27:17  ጲላጦስ ለህዝቡ እንዲፈታላቸው ያቀረበው ምርጫ ____________ ወይንም ____________ እንዲፈታላቸው ነው፡፡

በማቴዎስ 27:16 እና በሉቃስ  23:19 መሰረት ስለ በርባን የምናውቀው ነገር ምንድነው?

_______________________________________________

**መልመጃ**:

1. ሊቀ ካህናቱ እና የህዝቡ ሽማግሌዎች ህዝቡን አባበሏቸው (ማቴዎስ 27:20) ፡፡  ከሁለት አንዱ የትኛውን እንዲፈታላቸው እንደሚፈልጉ ህዝቡን ጲላጦስ ሲጠይቃቸው ህዝቡ የሰጡት ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 21)?

   _______________________________________________

2. ነገር ግን በሉቃስ  23:20 ላይ የምንመለከተው ነገር ጲላጦስ ኢየሱስን ለመፍታት እንደፈለገ ነው፡፡ ከዚያስ ህዝቡ ምን አደረጉ? _______________________________

   _______________________________________________

3. ህዝቡ ምን እያለ ነው ሲጮሁ የነበረው (ቁጥር 21)?

   _______________________________________________

4. በክሱ ሂደት ላይ ስለነበረው ስለዚህ ልዩ ክስተት ማቴዎስ ብቻ ነው የዘገበው። ማቴዎስ 27:19 አንብቡት። ምን ተፈጠረ?

______________________________________________

መልዕክቱ የሚለው ምንድነው?

______________________________________________

5. ለሶስተኛ ጊዜ ጲላጦስ ለህዝቡ ተናገረ (ቁጥር 4፤ 14፤ 22) ። እነርሱን የጠየቀው ነገር ምንድነው (ሉቃስ 23:22)?

______________________________________________

ስለ ኢየሱስ ምን ተናገረ?______________________________________________

ህዝቡ የፈለገው ነገር ምንድነው (ቁጥር 23)?

______________________________________________

6. የጲላጦስ የመጨረሻው ውሳኔ ምን ነበር (ቁጥር 23)?

______________________________________________

7. በህዝቡ ጥያቄ መሰረት ____________________ፈታላቸው (ቁጥር 26) ኢየሱስ ግን____________________ እንዲሰቀል __________________ሰጠ።

8. በሚከተሉት ጥቅሶች ውስጥ ስለ ጲላጦስ ምን የምናውቀው ነገር አለ?

ሀ.ማርቆስ 15:15

______________________________________________

ለ. ዮሐንስ 19:12-13

______________________________________________

ሐ.ማቴዎስ 27:24-26

______________________________________________

9. በማቴዎስ 27:27-31 ውስጥ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስ ላይ ስላደረጉት ነገር ነገር ምንድነው የተፃፈው?

ሀ. ምንድነው ያለበሱት?

______________________________________________

ለ. እንዴት ነው ያጎሳቆሉት?

______________________________________________

______________________________________________

10. ቁጥር 31 ላይ : "____________________በኋላ ____________________ ልብስ ገፈፉት፤ ልብሱንም አለበሱት ____________________ወሰዱት።" ነቢዩ ኢሳያስ ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር ምንድነው ያለው ? ኢሳያስ 53:7

“_______________________________________________________________

_______________________________________________________________”

## ምዕራፍ 5

**ማሰላሰል**

በዝርፊያ እና በግድያ ወንጀል ተከስሶ እና ተፈርዶበት በወህኒ ቤት እያለ ከእስሩ ስለተፈታው ሰው አስተያየት ሳንሰጥ ወይንም ጉዳዩን ሳንመለከት የክርስቶስ መከራ ላይ ብቻ አተኩሮ መቀጠሉ ቀላል ሊሆን ይቻላል፡፡ ማቴዎስ በርባንን የገለጠው አደገኛ እስረኛ እንደሆነ ነው፡፡

ህዝቡ ጲላጦስን "ስቀለው፤ ስቀለው " ያሉ ይጮሁበት ነበር፡፡ በግልፅ እንደሚታወቀው በርባን የታሰረበት እስር ቤት የሚገኘው ህዝቡ ከሚጮሁበት እና ሁካታ ከሚፈጥሩበት ቦታ በቅርብ ርቀት ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ እርሱ ህዝቡ ጲላጦስን ደጋግሞ ይጠይቅ የነበረውን ጥያቄ በግልፅ ሊሰማው አልቻለም ይሆናል፡፡ እርሱ በአገር መክዳት እና በግዲያ ወንጀል ነው የታሰረው፡፡ በዚህ ጥፋቱ ደግሞ የሚጠብቀው የሞት ፍርድ ነው፡፡

ጲላጦስ "ከሁለቱ የትኛውን እንድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁ?" ብሎ ህዝቡን ጠየቀ፡፡ ህዝቡም፤ "በርባን!" እያሉ ይጮሁ ነበር፡፡ ጲላጦስ ቀጥሎ ህዝቡን የጠየቀው ጥያቄ: " ይህንን ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስ ምን ላድርገው?" በማለት ነበር፡፡ ህዝቡም *"ስቀለው"* እያሉ ሲጮሁ ፤ ጲላጦስ "ለምን? ምን የፈፀመው ጥፋት አለ?" ብሎ መጠየቅ ነበረበት፡፡ ህዝቡ ግን በታላቅ ድምፅ *"ስቀለው"* እያሉ መጮሃቸውን ቀጠሉ፡፡

ጥቂት ጊዜን ውሰዱና እራሳችሁን በእስር ቤቱ ውስጥ እንዳላችሁ አድርጋችሁ አስቡ፡፡ አንተ/ቺ በርባን ነህ/ሽ፡፡ ስማችሁን በእርሱ ስም ቦታ አስገቡና ጥያቄውን መልሱ፡-

- ምን እያሰባችሁ ነው?

  _______________________________________________

- በእናንተ ላይ ምን ሊሆን ነው?

  _______________________________________________

ለአጠፋችሁት ጥፋት በህጉ መሰረት እንደምትቀጡ በእርግጠኝነት ታውቃላችሁ፤ ቅጣቱ ደግሞ ሞት ነው!

ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ታሪኩን ማሰላሰላችሁን ቀጥሉ፡፡ የወህኒ ቤት ጠባቂው መጥቶ በርባንን ከእስር ቤት መፈታቱን ሲነግረው እና ህዝቡ ደግሞ ኢየሱስ በእርሱ ምትክ እንዲሰቀል እንደፈለገ ሲያውቅ በርባን ምን ዓይነት ስሜት ሊሰማው እንደሚችል እስቲ ገምቱ፡፡ ይህ ሊታመን የማይችል ነው?

ኢየሱስ በምትኩ የሞተለት የመጀመሪያው ሰው በርባን ነው። ኢየሱስ ለእርሱ ኃጢአት እና ለመላው ዓለም ኃጢአት ነው የሞተው።

ነቢዩ ኢሳያስ ኢየሱስ በእኛ ምትክ መከራን እንደሚቀበል ተናግሯል (ኢሳያስ 53:4-5) ። እነዚህን ጥቅሶች ፃፏቸውና ኢየሱስ እንዴት ስለ እኔ እና የእናንተ ኃጢአት እንደተሰቃየ አጥኑ:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እውነት ነው፤ ኢየሱስ የእኛን በደል እና መተላለፋችንን ተቀበለ። ስለ እኛ መተላለፍ እርሱ ቆሰለ። እርሱ ስለ እኛ በደል ደቀቀ፤ በእኛ ላይ ሰላም የመጣው እርሱ በእኛ ምትክ ስለቆሰለ ነው፡ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን።

አንዴ ከእስር ከተፈታ በኂላ ምን እንዳደረገ የምናውቀው ነገር የለም። በርቀት በስውር ስፍራ ሆኖ በእርሱ ምትክ በመስቀል ላይ በሚስማር ተቸንክሮ የተሰቀለውን ኢየሱስን እየተመለከተው ይሆንን? , "እርሱ እየሞተ ያለው በእኔ ምትክ" ነው ብሎ ተናግሮ ይሆን? ኢየሱስ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ወይንም እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በርባን ያውቅ ይሆን? ይህ በእርሱ ላይ የሚያመጣው ለውጥ አለን? በእርግጥ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱን በትክክል አናውቅም ነገር ግን አንድ መገመት የምንችለው ነገር የእርሱ ህይወት እንደሚለወጥ እና ተስፋው እንደሚለመልም ነው። በዚያ ሌሊት እርሱ ወዴት ሄደ? እንደተፈታ ለማን ይሆን ቀድሞ የተናገረው?

በርባን ከሰራው ጥፋት የተነሳ ከሚጠብቀው ቅጣት እና ፍርድ ነፃ እንደወጣ ሁሉ እኔ እና እናንተም ካለፈው ጥፋታችን በኢየሱስ ነፃ ወጥተናል። እኛ ነፃ ወጥተናል። እኛ አሁን የምንኖረው ኑሮ በተስፋ የተሞላ ነው፤ ያም የዘላለም ህይወት ተስፋ ነው፤ለዘላለም ከእርሱ ጋር የመኖር ተስፋ ! ኢየሱስ ኃጢአታችንን ስለተሸከመ በእግዚአብሔር ፊት የምንቆመው በባዶነት አይደለም ነገር ግን እኛን ይቅር ተብላችኂል ብሎ የተናገረንን የእርሱን ቃል ይዘን ነው! አሁን ማንኛውም ፍጥረት እኛን በክርስቶስ ኢየሱስ የእኛ ጌታ የእኛ ከሆነው ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም (ሮሜ 8:39).

**የትግበራ ጥያቄዎች**: እኔ እና እናንተ ኢየሱስ በእኛ በበደለኞች እና በኃጢአተኞች ምትክ ስለሞተልን ከእስራታችን ነፃ ወጥተናል።

1. እኔ ምንድነው የማደርገው? ከእስራቴ ነፃ መውጣቴ በህይወቴ ላይ የሚያመጣው ተጨባጭ ለውጥ ምንድነው? በነፃ መውጣቴ ደስተኛ ነኝ? ያለፈውን ነገር ረስቼ አዲስን ህይወት ሁልጊዜ ለመኖር ዝግጁ ነኝ? ስለ እኔ ነፃነት ያለኝ ምላሽ ምንድነው? ከሞት አመለጥኩኝ!
2. በእኔ ምትክ የሞተውን ማወቅ እፈልጋለሁኝ። እኔ እርሱን ማወቅ የምችለው…

ሀ.________________________________________________________________________

ለ.________________________________________________________________________

ሐ.________________________________________________________________________

## ትምህርት ሰባት

# አባት ሆይ ይቅር በላቸው

### ዮሐንስ 18፤ 19 እና ሉቃስ 23 — ታላቅ ፍቅር

---

**የትምህርት 7 ቅኝት**

ቅኝት

መግቢያ

ትምህርት 7: ዮሐንስ 18 ፤ 19 እና ሉቃስ 23

- ኢየሱስ ንጉሱ
- ሆሳዕና እና አሁን ስቀለው
- ኢየሱስ ጥፋት የለበትም ተባለ
- የቀራኒዮ መንገድ
- አስበኝ
- ምቹ ጊዜ

## *መግቢያ*

ኢየሱስ እንዲሰቀል ጲላጦስ አሳልፎ ሰጠ። የጲላጦስን ውሳኔ ተከትሎ ኢየሱስ ወደ ቀራኒዮ ተጓዘ። ጲላጦስ ኢየሱስ ምንም ዓይነት ጥፋት እንደሌለበት አውቋል፤ ይሁን እንጂ ጲላጦስ የህዝቡን ሁከት በመፍራ እና ኢየሱስን በነፃ ቢለቅቀው ሊከተል የሚችለውን ፖለቲካዊ ቀውስን በማሰብ፤ ከእውነት ይልቅ ህዝብን እና ስልጣኑ እንዳይነካበት ከዚህ ንፁህ ሰው ደም ነፃ ነኝ በማለት እጁን ታጥቦ አሳልፎ እንዲሰቀል ሰጠ።

ኢየሱስ በመስቀል ላይ እጆቹ እና እግሮቹ በሚስማር ተቸንክረው እያለ፤ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁም እና ይቅር በላቸው" ብሎ ሲፀልይ ለሚሰማው ሰው እጅግ የሚያስደንቅ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላም አለ። ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እያለ አብረውት ከተሰቀሉት ወንጀለኞች ጋር ያደረገውን ንግግር በጥንቃቄ እንድታዳምጡ ትበረታታላችሁ። ኢየሱስ አንዱ ወንጀለኛ ቢቀልድበት እና ቢያሾፍበትም እንኳን ሌላኛውን ወንጀለኛ ከእርሱ ጋር ወደ ገነት እንዲሄድ የጋበዘው ነው።

እነዚያ እያላገጡበት ያሉ ሰዎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከተሰቀለበት ከወረደ ክርስቶስ መሆኑን እንደሚያረጋግጡ ነቅ። ኢየሱስ እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ በመስቀል ላይ ነው ተሰቅሎ ነው የቆየው፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞት ደግሞ ለመሲሁ፤ በእግዚአብሔር ለተቀባው ዓላማውን የሚፈፅምበት የመጨረሻው መንገድ ነው። የእርሱ ሞት ማለት የዛላለም ህይወትን የምናገኝበት እና ከእርሱ ጋር ለዘላለም የምንኖርበት ነው!

# ትምህርት 7

**ምዕራፍ 1**

***መግቢያ***

ኢየሱስ ምድራዊ ህይወቱ ሁሉ ሰዎች ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር። በማቴዎስ 2:2 ውስጥ እንደተዘገበው ሰብዓ ሰገል ከምስራቅ ወደ ኢየሩሳሌም በመምጣት "የተወለደው የአይሁድ ንጉስ ወዴት ነው?" ብለው ጠየቁ። እነርሱ ለማየት የሚፈልጉት ንጉስ ምድራዊ ንጉስ አይደለም (ዮሐንስ 18:36) ነገር ግን እርሱ ነቢያቶች አስቀድመው ይመጣል ብለው የተነበዩለት ክርስቶስ ፤ መሲሁ ነው። የአይሁድ ህዝብ ሲጠብቁት የነበረው ንጉስ እነርሱን ከጠላቶቻቸው እጅ በተለይም ከሮማውያን የሃይል አገዛዝ ነፃ የሚያወጣቸው እና እስራኤልን የሚገዛ ነው። ሰብዓ ሰገል ወደ ኢየሩሳሌም የመጡት በደስታ የተወለደውን የአይሁድን ንጉስ ሊሰግዱለት ነው። ነገር ግን ንጉስ ሄሮድስ ታላቁ ስለመሲሁ፤ስለተወለደው የአይሁድ ንጉስ ሲሰማ እንዴት ነው የሆነው (ማቴዎስ 2:3 ፤ 8፤ 13ለ፤ 16)?

___

በዮሐንስ 1:49 ናትናኤል ምን በማለት ነው ያወጀው። ስለኢየሱስ እርሱ ምንድነው ያለው?

___

**የቤት ሥራ** : ዮሐንስ 18:33-19:16 አንብቡት።

***መልመጃ***:

1. ኢየሱስ በእርግጥ የእስራኤል ንጉስ ነው! አሁን ሮማዊው አስተዳደሪ የሆነው ጲላጦስ ኢየሱስን የጠየቀው ጥያቄ አይሁድ እግዚአብሔርን መሳደብ ያሉት ጉዳይ በሞት የሚያስቀጣ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ ነው። ጥያቄው ምን ነበር (ዮሐንስ 18:33)?

   ___

2. ስለእርሱ መንግስት ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምንድነው፤ ቁጥር 36?

   ___

3. ከዚያም ጲላጦስ "የአይሁድ ____________ ነህን (ቁጥር 37)!" ብሎ ጠየቀው።

   ሀ.ኢየሱስ መልሶ፤ "____________________ትላለህ" አለው።

ለ.ኢየሱስ ለጲላጦስ እርሱ ንጉስ ሆኖ የመጣው ለ________________________ እንደሆነ ተናገረ።

ሐ. በ38 ውስጥ ሰዎች ዛሬም የሚጠይቁትን ጥያቄ ጲላጦስ ጠየቀ። ጥያቄውም:

______________________________________________________________________

4. በቁጥር 38 ላይ ጲላጦስ ለአይሁድ እንዲህ አላቸው፤ "________________________________________."
5. የጲላጦስ ወታደሮች ኢየሱስን የንጉስ የሚያምር ቀይ ልብስ በማልበስ እና የእሾህ አክሊል ደፍተውበት፤ "__________________________________________________ (ዮሐንስ 19:3)" አሉት።
6. ጲላጦስ እንደገና ወደ አይሁድ በመምጣት (ቁጥር 4) "______________________________ ____________________________________________________________________"አላቸው።
7. ሊቀ ካህናቱ እና የእነርሱ ባለስልጣናት ኢየሱስ የሚያምረውን ቀይ ልብስ ለብሶ እና የእሾህ አክሊል ተደርጎለት ሲመለከቱ "______________________________! __________________________!" እያሉ ሲጮሁ ነበር።
8. ቁጥር 6ለ: ጲላጦስ አስረግጦ ደጋግሞ የተናገረው ነገር: "________________________________________________________________________" የሚል ነበር።
9. ነገር ግን አይሁዶች የጲላጦስ ደካማ ጎን አገኙ። ምን እያሉ ነበር ሲጮሁ የነበረው (ቁጥር 12)?

______________________________________________________________________

10. ጲላጦስ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው። በፍርድ ወንበር ላይ ተቀምጦ፤ "__________________________________________________ (ቁጥር 14ለ)" አለ።
11. እነርሱ ግን"______________________________________________________(ቁጥር 15)" እያሉ ይጮሁ ነበር።
12. ጲላጦስም "______________________________________________________________?" ብሎ ጠየቃቸው።
13. የካህናት አለቆች "______________________________________________________________" ብለው መለሱለት።
14. ጲላጦስ ለህዝቡ ሃሳብ በመገዛት ኢየሱስን _________________________ አሳልፎ ሰጣቸው (ቁጥር 16)።

__ምዕራፍ 2__

**ማሰላሰል**

ለምድነው ህዝቡ እየዘመሩ "በጌታ ስም የሚመጣ ንጉስ የተባረከ ነው፤በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር " እያሉ ከዘመሩ በኂላ የአይሁድ ባለስልጣናት ኢየሱስን ለመግደል የፈለጉት (ሉቃስ 19:38)!" ምንድነው የተፈጠረው ችግር? ህዝቡ ለምንድነው ሃሳባቸውን ሊቀይሩ የቻሉት? ህዝቡ ሃሳባቸውን የቀየሩት "በጌታ ስም የሚመጣ ንጉስ የተባረከ ነው" ብለው የዘመሩት ተታልለው እንደሆነና እርሱ የአይሁድ ንጉስ እንዳልሆነ ስላረጋገጡ ነው? እርሱ ሲፈፅማቸው የነበሩት ተዓምራት አዕምሮአቸውን ስለአሳወረው የእርሱን ትክክለኛ ማንነት ማየት ስላልቻሉ ይሆንን? ወይንም በወቅቱ በተፈጠረው ግርግር እና በህዝቡ ጩሁት ተይዘው፤ ወይንም ህዝቡን ፈርተው... ይሆን።

ከዚያም በተጨማሪ አሁን ደግሞ ለየት ያለ ህዝብ ነው በአሁኑ ጊዜ ያለው... ከፋሲካ በዓል ቀደም ብሎ አንድ ሰው እንደ ንጉስ ሆኖ በብዙ ህዝብ ታጅቦ እየተዘመረለት ወደ ኢየሩሳሌም ገብቷል። ሄሮድስ የታላቁ ሄሮድስ ልጅ የፋሲካን በዓል ለማክበር የራሱን አካባቢ ከሚያስታድርበት ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቷል። ያለጥርጥር እርሱ የመጣው በወታደሮቹ እና በፈረሶቹ ታጅቦ ነው። ጲላጦስ ደግሞ ቂሳሪያ ከሚገኘው ቤተ መንግስቱ ወደ ኢየሩሳሌም የተጓዘው በእራሱ ወታደሮች የፋሲካ በዓል አከባበር በሰላም እንዲጠናቀቅ ለመጠበቅ ነው። የእርሱ በኢየሩሳሌም መገኘት ለአይሁዳውያን የሚያስተላልፈው መልዕክት እነርሱ የሚኖሩት በሮማውያን ሃይል እና ስልጣን ስር እንደሆኑ ነው።

"ስቀሉት! ስቀሉት!" እያሉ ህዝቡ እንዲጮሁ ያደረገው ማነው? በእዚህ ላይ የእናንተ አስተያየት ምንድነው:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ትግበራ**

1. እናንተ ከህዝቡ መካከል ብትኖሩ ኖሮ ምን እያላችሁ ትጮሁ ነበር?

   ______________________________________________________

2. ለምን?

   ______________________________________________________

   ______________________________________________________

**ማሰላሰል**

ኢየሱስ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ በጲላጦስ ተረጋግጧል። "ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም..." ጲላጦስ አይሁድ ኢየሱስን ንጉሳቸው የማደርጉት ከሆነ እርሱን በነፃ ሊለቅቀው ፈልጓል። አሁን ጲላጦስ በሁለት

ነገስታት መካከል አንዱን መምረጥ አለበት። ኢየሱስ ፣የአይሁድን ንጉስ ወይንም ቄሳር የሮማውያንን ንጉስ መምረጥ አለበት። ጲላጦስ ግን ቄሳርን መረጠ። ቄሳር ምድራቱን ያደኸየና ህዝቡን ሲጮቅን የነበረ ነው። ስለ እውነት የመሰከረውን እና የተትረፈረፈ ህይወትን (ዮሐንስ 10:10) የሰጣቸውን ኢየሱስን ግን አልፈለጉትም ። ጲላጦስ የተሳሳተ ውሳኔን አድርጓል። እርሱ ትክክለኛ ያልሆነውን ንጉስ ገደለው።

**ትግበራ**

1. ትክክለኛ ያልሆነውን ንጉስ ማነው? ማንን ነው እናንተ ወደ ህይወታችሁ ጋብዛችሁ በልባችሁ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ሃሳባችሁን እና ፈቃዳችሁን እንዲገዛ የፈቀዳችሁት?

   ________________________________________________________________

2. ጊዜ ውሰዱና ንጉሳችሁን ማንነት ግለጡና አስረዱ:

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

3. ለእናንተ ንጉሳችሁ ምኑ ነው እንደ ንጉስ የማረካችሁ?

   ________________________________________________________________

**ማስታወስ**

ጲላጦስ በእርሱ ላይ ምንም ጥፋት አላገኘሁበትም ብሎ ሲናገር እውነት ነው የተናገረው። እርሱ ኢየሱስን የሚገድልበትን ምንም ምክንያት አላገኘም። ኢየሱስ ፍፁም የሆነ እግዚአብሔር ልጅ ነው፤ እርሱ ሰው ሆኖ ወደ ምድር የመጣው የእኛ ምትክ ሆኖ በእኛ ፈንታ ስለእኛ ሊሞት ነው። "ልጁም ______________________________ደም____________

ሁሉ____________________ (1 ዮሐንስ 1:7ለ)። ይህንን ጥቅስ በቃላችሁ በደንብ ከአላወቃችሁ አሁን ለመያዝ ሞክሩ። በእነዚህ ጥቂት ቃላት ውስጥ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ደም ነፍሳችንን ከኃጢአት ሁሉ እንደሚያነፃን ዋስትናን ይሰጠናል። እኛ ታጥበን ከኃጢአታችን የነፃነው የዓለም ኃጢአት በአስወገደው የእግዚአብሔር በግ (ዮሐንስ 1:29) በሆነው በኢየሱስ ደም ታጥበን ነው.

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ! አንተ በእኔ ኃጢአት ምክንያት ተሰቃይተሃል፤ ተዋርደሃል። አንተ ከጲላጦስ ጎን ቆመህ እያለህ እኛ ሁላችን ከህዝቡ ጋር ሆነን "ስቀሉት ስቀሉት" እያልን ስንጮህ ነበር። ምንም እንኳን በአይኔ ልቦና የምመለከተው ብዙ ነገሮች ቢኖሩም እኔ ግን ለአንተ የምሰጠው ነገር ምስጋናን እና ውዳሴን ነው። የአንተ ዘላለማዊ ፍቅር ለእኔ እና ከህዝቡ ጋር ሆነው ሲጮሁ ለነበሩ ሁሉ ነው። ከማንኛውም ሃጢያቴ የሚያነፃኝን ደምህን ስላፈሰስክልኝ አመሰግንሃለሁኝ። ከአንተ የተነሳ ኃጢአቴ ከእኔ ላይ ተወግዷል። ይህንን እውነት እንድረዳና ለነፈሴ እረፍትን እንድሰጣት በመንፈስህ እርዳኝ።

________________________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 3</u>

***መግቢያ***

ኢየሱስ በጌተሰማኒ አትክልት ስፍራ በወታደሮች ተይዞ ለሊቀ ካህናቱ፤ ከዚያም ለጲላጦስ ቀጥሎም ለሄሮድስ በመጨረሻም በድጋሚ ለጲላጦስ ተላልፎ ተሰጠ። አሁን ደግሞ ጲላጦስ ለህዝቡ ፈቃድ በመንበርከክ ኢየሱስን ህዝቡን ለማስደሰት ሲል እንዲሰቀል ለሮማውያን ወታደሮች እንዲሰቅሉት አሳልፎ ሰጠ። የኢየሱስ መሞት የማይቀር ጉዳይ ነው። እርሱ የራሱን መስቀል እንዲሸከም አስገደዱት። ወደ ጎልጎታ፤የራስ ቅል ተብሎ ወደ ሚታወቀው ስፍራ (ማርቆስ 15:22) መስቀል ተሸክሞ መንዝ ነበረበት።

የተወሰኑት ተከትለውታል። የተወሰኑት መስቀሎችን ተሸክመዋል። የተወሰኑት እንባቸውን እያፈሰሱ ያለቅሱ ነበር። የተወሰኑት የስድብ ናዳ ያወርዱበት ነበር። አንዱ ፀለየ። አንዱ ሰጠ። አንዱ ይቅር አለ። ይህንን ጥናት ማንበባችሁን ስቀጥሉ፤ራሳችሁን ከህዝቡ በካከል ታገኛላችሁ። መስቀልን አትፍሩት ነገር ግን ወደ መስቀሉ ቀርባችሁ ኢየሱስ የሚናገራችሁን የመጨረሻ ቃላት አድምጡ።

**የቤት *ሥራ***: እኛ በዋናነት ሉቃስ እና ዮሐንስ ስለኢየሱስ ስቅለት የዘገቡትን በዋናነት እንመለከታለን። ሉቃስ 23:26-43 እና ዮሐንስ 19:16ለ-27 አንብት።

*ማስታወሻ* : ስለ ኢየሱስ ስቅለት ወንጌላት በማቴዎስ 27:32-44 እና ማርቆስ 15:21-32 የዘገቡትን እንድታነቡ ትበረታታላችሁ።

**መልመጃ** (ከሉቃስ 23 የተወሰደ):

1. ወታደሮቹ ኢየሱስን እየወሰዱት ነው። በግልፅ እንደሚታወቀው ኢየሱስ በሮማውያን ወታደሮች ከደረሰበት ስቃይ፤ ድብደባ እና ግርፊያ የተነሳ ተዳክሟል። ማነው የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም የተገደደው (ቁጥር 26)? ________________________

   ስለእርሱ የተነገረን ነገር ምንድነው?

   ________________________________________________________

   ማርቆስ 15:21 የሚነግረን ስምዖን ____________________ እና ________________አባት እንደሆነ ነው። ከዚህ መረዳት የምችለው ነገር ስምዖን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደሆነ ነው። ስምዖን ከቀሬና ፤ ከአሁኑ ሊቢያ ነው የመጣው።

2. ስምዖን ኢየሱስን ሲከተለው ቁጥር 26 ውስጥ እንመለከታለን። በቁጥር 27 ላይ ማነው እርሱን የሚከተለው?

   ________________________________________________________________________

3. ኢየሱስ ብቻውን አይደለም የሚሰቀለው። ከእርሱ ጋር አብረው እየተወሰዱ ያሉት እነማን ናቸው (ቁጥር 32)?

_______________________________________________________________________

4. ____________________ ወደሚባል ስፍራ በደረሱ ጊዜ፤ በእዚያን እርሱን__________________አንዱን__________________ሁለተኛውንም__________________ ሰቀሉ (ቁጥር 33)።

5. ኢየሱስ በመጀመሪያ የተናገራቸው ቃላት ምንድናቸው (ቁጥር 34ሀ)?

_______________________________________________________________________

6. እርሱን የሰቀሉ ወታደሮቹስ ምን አደረጉ

_______________________________________________________________(ቁጥር 34ለ)

7. ህዝቡ ምን እያደረጉ ነበር (ቁጥር 35)?

_______________________________________________________________________

8. "...ህዝቡም ቆመው ______________________ ነበር። መኳንንቱ ደግሞ፤ "____________

_____________________________________________________________________" ነበር።

9. ወታደሮቹስ ምን አደረጉ? (ቁጥር 36)? ________________________________

ሆምጣጤ አምጥተው ______________________________________________________"

ነበር።

*ማስታወሻ* : የተፃፈው ፅሁፈት ስለየእርሱ ወንጀል የሚናገረው ነገር ምን አለ (ቁጥር 38)?

_______________________________________________________________________

10. በዚያ ከተሰቀሉት ወንጀለኞች መካከል አንዱ በእርሱ ላይ ሰደበው (ቁጥር 39)። ኢየሱስ ምን ብሎ ነው የሰደበው?

_______________________________________________________________________

11. ሌላው ወንጀለኛ ግን ________________________________________ አብሮት የተሰቀለውን ወንጀለኛ ተቆጣው (ቁጥር 40)። ምን እያለ ነው ሁለተኛውን ወንጀለኛ የገሰፀው (ቁጥርs 40-41)?

ሀ. አንተ

_______________________________________________________________________

ለ. እኛ

_______________________________________________________________________

ሐ. ይህ ግን

_______________________________________________________________________

12. ወደ ኢየሱስ ዘወር ብሎ፣ "______________________________________________

____________________________________________ (ቁጥር 42)" አለው።

13. ኢየሱስም፣"____________________________________________________ (ቁጥር 43)" አለው።

**<u>ምዕራፍ 4</u>**

**ማሰላሰል**

***ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል (ሉቃስ 23:26-43) ሊናስተውላቸው የሚገቡ በርካታ ነገሮችን ይዟል። በመጀመሪያ ጥቂት ነገሮችን እንመልከት እና ኢየሱስ ስለ እኛ የተሰቃየበትን እና የሞተበትን ፍቅሩን መረዳት እንድንችል እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲረዳን እንለምነው።***

1. ስምዖን ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ እንደተከተለው የተነገረን ሲሆን ከዚህ የምንረዳው ኢየሱ የተሰቃየው እና የሞተው እግዚአብሔር አብ ለእኛ ከአለው ፍቅሩ የተነሳ አንዲያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሳልፎ እንደሰጠው ነው። ስምዖን የኢየሱስን መስቀል ተሸክሞ ተከተለው። ኢየሱስ ስለራሱ አገልግሎት እና አሟሟት ከዚህ ቀደም ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ተናግሯቸው ነበር (ማቴዎስ 16:24-25)፣ ከዚህ ንግግሩ አንፃር አሁን እየደረሰበት ያለውን መከራና ሞት እንዴት ትረዳላችሁ?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

2. ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ጎልጎታ ሲሄድ በርካታ ሰዎች እርሱን ሲከተሉት ነበር፣ በተለይም ሴቶቹ እያለቀሱ ሲከተሉት እንደነበር። ኢየሱስ በነበረው አገልግሎት ሁሉ ሴቶች ሲያገለግሉት ነበር (ሉቃስ 8:2)። ወደጃቸው ኢየሱስ ላይ የተፈፀመውን ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ሲመለከቱ ምን ያህል እንደሚያዝኑ መገመት ትችላላችሁ። የእርሱ ሞት የማይቀር ጉዳይ ነው፣ ለእነርሱ ያለው የእርሱ ታላቅ ፍቅር ኢየሱስ መከራን እንዲቀበል እና እንዲሞት አደረገው።

3. የእርሱ መስቀልን አስመልክቶ እንኳን የተነገሩ ትንቢቶች ተፈፅመዋል። ኢሳያስ 53:12 ላይ የሚነግረን ነገር ምንድነው? የኢየሱስ መስቀል ከሁለቱ ወንጀለኞች መካከል መሆኑ ምን ዓይነት ትርጉም ይኖረዋል?______________________________________________

   ______________________________________________________________

4. ሉቃስ 4:1-13 የሚዘግበው ኢየሱስ በምድረ በዳ በዲያብሎስ የተፈተነበትን ታሪክ ነው። ታሪኩን አንብቡት እና በቁጥር 3፣ 6፣ እና 9 ላይ የተጠቀሱትን ፈተናዎችን ለዩአቸው። ዲያብሎስ "የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ…" የሚለውን ሀረግ ከሶስቱ በሁለቱ ፈተናዎች ላይ ይጠቀማል። ከዚያም በኋላ ዲያብሎስ ኢየሱስን በፈተናው ማሸነፍ በአልቻለ ጊዜ ቀጥር 13 እንደሚናገረው

(ዲያብሎስ) ______________ በጨረሰ ጊዜ ____________________ከእርሱ ____________።" በሉቃስ 23 ላይ ተመሳሳይ ቃላትን እንሰማለን...

ሀ. በገዢዎች (ቁጥር 35):

___________________________________________________________

ለ. በወታደሮች (ቁጥር 37):

_________________________________________________________

ሐ. በአንዱ ወንጀለኛ (ቁጥር 39):

_________________________________________________

በመስቀሉ አካባቢ የተሰባሰቡትን ሰዎች በመጠቀም ዲያብሎስ የእርሱን "ምቹ ጊዜ" በመጠቀም እንደገና ኢየሱስን "አንተ እኔ ነኝ የምትለው ሰው ከሆንክ፤ ይህንን ማድረግ የለብህም፤ የመጨረሻውን ታላቅ ተዓምራት በመስራት አንተ ክርስቶስ መሆንህን አሳየን። ራስህን አድን። ከመስቀል ውረድ። አንተ ክርስቶስ፤ መሲሁ፤የተቀባው፤ የአይሁድ ንጉስ መሆንህን አረጋግጥ ።" በማለት ይፈትነው ነበር። በመስቀል ላይ ያንን ታላቅ መከራ በመቀበል ላይ ያለው ኢየሱስ ለዲያብሎስ ፈተና ተጋላጭ ነበር። ከዮሐንስ 12:27 የምናገኘው ሃሳብ ምንድነው? ምን እንደሚሆን ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት እየነገራቸው ነበር። "አሁን___________________ታውካለች ምንስ እላለሁ ? አባት ሆይ _______________ አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ_________________መጣሁ። አባት ሆይ ________________ አክብረው።

**ማጠቃለያ**:

*ይህ የመጀመሪያው ትምህርት እየተጠናቀቀ ነው። ኢየሱስ ተሰቅሏል። በእርሱ ላይ ክፉ ነገርን ለአደረጉበት ፀለየ። ከእርሱ ጋር ለተሰቀለው ወንጀለኛ "ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" በማለት ተስፋን ሰጠው። የዚህን የክፍል አንድ ጥንት አጠናቅቀናል። የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ህይወት የሚለውን ጥናት ክፍል ሁለት በቅርቡ እንጀምራለን።*

*በዮሐንስ 15:13 " ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም" ተብሎ ተፅፏል። ኢየሱስ ለእኛ የእርሱ ወዳጆች ያደረገው ይህንን ነው። ታሪኩ አላበቃም። ታሪኩ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሰቀሉ አላበቃም። ታሪኩ የሚያበቃው ተወዳዳሪ በሌለው ታላቅ ዜና ነው ! የእግዚአብሔር ፍቅር የእኛ ህይወት የሚለውን ጥናት ክፍል ሁለት እንድታጠኑ ትበረታታላችሁ።*

**ተጨማሪ የክሮስ ኮኔክት ጥናቶች በነፃ ከድህረ ገፃችን ይገኛሉ።**

**የአገልግሎታችንን ድህረ ገፅ**: www.crosscm.org.

**አስተያየታችሁን መስማት እንፈልጋለን!**

**በዚህ አድራሻ እንገናኝ**s: admin@crosscm.org